# የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ግላዊ መረዳት ትንተና በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ

በ፡

ድርባ ሩሹ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናልዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

አማካሪ፡

አቶ ጥላሁን ተሊላ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናልዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

# የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ግላዊ መረዳት ትንተና በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ

በ፡

ድርባ ሩሹ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

መስከረም 2005 ዓ.ም

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የኔ መሆኑንና በጽሑፍ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ተዛማጅ ጽሑፎችና መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም ድርባ ሩሹ

ፊርማ ____________________

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናልዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

# የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ግላዊ መረዳት ትንተና በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ


በ፡

ድርባ ሩሹ


የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

<u>አማካሪ</u>

ስም ንጋሁን ተከለ ፊርማ ___________

<u>ፈታኝ (የውስጥ)</u>

ስም ፊቅርዮን ገብሬ ፊርማ ___________

<u>ፈታኝ (የውጪ)</u>

ስም ___________ ፊርማ ___________

<u>የትምህርት ክፍሉ ሊቀመንበር</u>

ስም ___________ ፊርማ ___________

## ምስጋና

አማካሪ በጠፋበት ሰዓት ውድ ጊዜአቸውን ሰውተው፣ በትዕግስት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ፅሁፌን በማረምና በማስተካከል ለረዱኝ አማካሪዬ አቶ ጥላሁን ተሊላ ምስጋናዬ ጥልቅ ነው።

ይህ ሥራ በእኔ የተሠራ ይሁን እንጂ በኦሮምኛ ልቦለዶች ላይ የመስራት ፍላጎቴን አይተው በዚሁ እንድቀጥልና አሁን የደረስኩበትን ደረጃ እንድደርስ ላደረጉኝ መምህር ዘሪሁን አስፋው ላቅ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል።

አንዳንድ ሃሳቦችንና የሚያስፈልጉኝን መፅሐፍት በመስጠት ሁሌ ከጎኔ ላልጠፋው ተፈሪ ንጉሴ ምስጋናዬ ይድረሰው።

መዝናናት እያማራት ልጆችንንና እኔን በመንከባከብ ብቻ ታቅባ፣ እኔ እንዳልቸገር እራሷን መስዋዕት በማድረግ ለዚህ ደረጃ ላበቃችኝ ውዱ ባለቤቴ ሀዊ የምንጊዜም ባለውለታዬ ነች።

ይህንን የምርምር ፅሁፌን ሳዘጋጅም ሆነ ከዚያ በፊት የማቴሪያል ድጋፍና ምክራቸው፣ በርታ አይዞህ ባይነታቸው ለአንድም ጊዜ ያልተለየኝ ቤተሰቦቼ አቶ ዋቅቶሌ ሁንዴ ፣ ወ/ሮ አስቴር ነጋሳ እና አቶ ነጋሳ ሁንዴ እንዲሁም መላው ቤተሠብ ለእኔ ዓላማ መሳካት ሲሉ የከፈሉትን መስዋዕት መቼም ከአእምሮዬ አይጠፋምና ኑሩልኝ እላለሁ።

የኤባንቱ ወረዳ ትምህርት ቢሮ ስላደረጋችሁልኝ ትብብር አመሰግናለሁ።

አንድም ቀን ሳትሰለቸኝ በእጅ የተጻፉትን ጽሁፎቼን በኮምፒተር በመጻፍ፣የፊደል ግድፈቶችን በማስተካከል ለረዳችኝ ወ/ሪት ፋሲካ ዘውዱ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳት።

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ....................................................................................... i

መታሰቢያ ....................................................................................... ii

ማውጫ ....................................................................................... iii

አጠቃሎ ....................................................................................... v

ምዕራፍ አንድ ....................................................................................... 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ....................................................................................... 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....................................................................................... 2

1.3. የጥናቱ ዓላማ ....................................................................................... 2

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ....................................................................................... 3

1.5. የአጠናን ዘዴ ....................................................................................... 4

1.6. የጥናቱ ወሰን (ገደብ) ....................................................................................... 5

1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ እርምጃዎች ....................................................................................... 5

ምዕራፍ ሁለት፡ ክለሳ ድርሳን ....................................................................................... 7

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ....................................................................................... 7

2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ....................................................................................... 14

2.2.1. የመረዳት ፅንሰ ሃሳብ ....................................................................................... 14

2.2.2 የውክልና ፅንሰ ሃሳብ ....................................................................................... 17

2.3. የእንስታዊያኑ ሃሳብ በሴቶች ላይ ....................................................................................... 20

2.3.1. እንስታዊነት እና ባህል ....................................................................................... 22

2.3.2. እንስታዊነት እና ሃይማኖት ....................................................................................... 23

2.4. ሴት ገፀባህሪያት በኪነጥበብ ስራዎች ውስጥ የሚሰጣቸው ውክልና ....................................................................................... 24

ምዕራፍ ሦስት፡ የመረጃ ትንተና ....................................................................................... 26

3. በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ግላዊ መረዳት (Self Perception of Major Female Characters in Isayas Hordafa's Novel) ....... 29

3.1. የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያቱ አጠቃላይ ስብእና ....................................................................................... 29

3.1.1. Hawwii -ሀዊ ....................................................................................... 31

3.1.2. Yeroon -የሮን ....................................................................................... 38

3.1.3. Siintolinnaa-ሲንቶሊና ........................................................ 44
3.2. በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ተመሳስሎ እና ልዩነት ........................................................ 48
3.2.1. የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያቱ ተመሳስሎ ........................................................ 48
3.2.1.1. ብቸኛ ሆኖ መወለድ ........................................................ 49
3.2.1.2. በስተርጅና መወለድ ........................................................ 50
3.2.1.3. ትዳር ........................................................ 51
3.2.2. የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያቱ ልዩነት ........................................................ 53
3.2.2.1. ሃይማኖት ........................................................ 54
3.2.2.2. የቤተሰቦቻቸው የኑሮ ሁኔታ ........................................................ 57
3.2.2.3. ከተውልድ ቦታቸው አኳያ ........................................................ 58
3.3. የኢሳያስ ሆርዶፋ ሴቶች ከማህበረ ባህላዊ አንፃር........................................................ 59
3.3.1. ማህበረሰቡ ለሴቶቹ ያለው አመለካከት ........................................................ 59
3.3.2. ሴቶቹ ለማህበረ ባህላቸው ያላቸው አመለካከት ........................................................ 64
3.4. ዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ከሌሎች ገፀባህሪያት ጋር ያላቸው ግንኙነት........................................................ 65
3.4.1 ሀዊ እና አማረ........................................................ 66
3.4.2. ሀዊ እና ሌሎች........................................................ 67
3.4.3. የሮን እና ሰለሞን ........................................................ 68
3.4.4. የሮን እና ሌሎች........................................................70
3.4.5. ሲንቶሊናና ሌሎች ........................................................ 71
3.5. በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ውክልና /Representation of major Female characters in Isayas Hordofa's Novel/ 74
ምዕራፍ አራት
ማጠቃለያ........................................................ 89
ዋቢ ፅሁፎች ........................................................ 94

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት "የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ግላዊ መረዳት በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ" (Self Perception of major female characters in Isayas Hordofa's Novels') በሚለው ርዕስ የቀረበ ሲሆን ሁለት ዓበይት ዓላማዎችን ይዞ የተነሳ ነው። ከነዚህም አንዱ የሴቶቹ አመለካከት ለማህበረ ባህላቸው የሚለው ጉዳይና ማህበረሰቡ ለሴቶቹ የሚሰጠውን ማህበረ ባህላዊ ደረጃ እንዲሁም ሴቶቹ ራሳቸው ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት እስከ ምን ድረስ ነው? የሚለው ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የእነዚህ ሴቶች ውክልና (representation) ከልቦለዶቹ አንፃር ቃኝቶ ያቀረበ ነው።

በሦስቱም ልቦለዶች ውስጥ ሴቶቹ የተመረጡበት ምክንያት እና እነዚህን ሴቶች እንደወካይ ገፀባህሪ አድርጎ መምረጥ ለልቦለዶች መልዕክት መጉላት የፈየደው ነገር ካለ የሚሉና እነዚህ ሴቶች የኦሮሞን ማህበረሰብ ወክለው ለመቅረባቸው ከታሪክና ከልቦለዶቹ ሃሳብ ተነስተን ትንታኔና ትርጓሜ የተሰጠበት ጥናት ነው።

እነዚህ ቆራጥና ጠንካራ ልበብሩህ ሴቶች ለወገናቸውና ለራሳቸው ነፃ መውጣት፣ በሰው ልጆች አዕምሮ ውስጥ የመቻቻልን፣ የእኩልነትንና የአንድነትን መንፈስ ለማስረፅ የመከራን ፅዋ የሚቀምሱ፣ እንደተለኮሰ ሻማ ለሰው የሚያበሩ፤ ለዛሬ ሳይሆን ለነገ የሚኖሩ እነዚህ ሴቶች በእውኑ ዓለም ለሚኖሩት ሰዎች ምሳሌነታቸው የላቀ፣ ሰናይ ምግባራቸው አስተማሪ፣ አርአያነታቸው ተጠቃሽ ሆኖ የቀረቡ ናቸው።

በሰው ልጆች እኩልነት፣ በፍቅርና በሰላም የሚያምኑ የእነዚህ ሴቶች መከራ ጠንሳሾች ከገዛ ዘመዶቻቸው መጀመሩ ደግሞ ነገሩን ያወሳስበዋል። ከዚህ በመነሳት ነገሩ ወደ ታሪክ የሚያመራ ቢሆንም ልቦለዶቹም በራሳቸው ታሪክ ቀመስነታቸው ጎልቶ ስለምታይ ወደ ታሪክም ጎራ እያለ አንዳንድ ነገሮችን ያነሳው ይህ ጥናት የይዘት ትንተናን መሰረት በማድረግ ነው። በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ ያሉት የወካይ ገፀባህሪያትን አጠቃላይ ስብእናቸውን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻቸው የእነርሱን ማንነት እና ምንነትን ለማሳየት ከእነርሱ ጋር ለተሳሉት ሌሎች ገፀባህሪያትም ያላቸውን አመለካከት እንዲሁም ሌሎች ገፀባህሪያት ስለ እነርሱ ያላቸውን አመለካከት ጠቁሞ የሚያልፍ ይህ ጥናት በአጠቃላይ የእነዚህ ሴቶች አተያይ፣ ለህይወት ያላቸውን መፈክር ቃኝቶ አቅርቧል። በዚህም እነዚህ ሴቶች ዛሬ ላለነው ትውልድ ያለፈውን ድፍን ጥላቻ ይዘን መጓዝ ሳይሆን ያለፈውን እንደ ታሪክ በመቁጠር ዛሬ ተቻችለንና ተከባብረን መኖር እንዳለብን የሚጠቁሙ መሆናቸው ተደርሶበታል።

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የኦሮምኛ ዕሁፋዊ ስነ ዕሁፍ አነሳስ ረዘም ያለው ታሪክ ያለ ቢሆንም ከደርግ ውድቀት ማግስት ጀምሮ አበባው መፈንዳት ለጀመረው እና አሁን አበባውን ማሸተት ለጀመርነው ትውልድ ከመጀመሪያው አፈሩን ኮትኩቶ ዘሩን በመዝራት ለእድገቱ የመሰረት ድንጋይ የጣለው ሰው ሸክ በክሪ ሳጰሎ (shaykh Bakrii Saphalo) ናቸው። እኚህ ታዋቂ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ከሃይማኖት ውጪ የኦሮምኛን ስነፅሁፍ የፃፉ ሰው በመባልም ይጠቀሳሉ፡ መሀመድ ሀሰን፤ 2003 በመጥቀስ (Asafaa, 2009:175) ላይ እንዳሰፈረው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ማለትም ከ1980ዎቹ መጀመሪያ እስከ ዛሬ ድረስ ወጥ በሆነ መንገድ ባይሆንም የኦሮምኛ ስነ ዕሁፍ በልቦለድ፣ በግጥም፣ በድራማ፣ እንዲሁም በጋዜጦች ላይ ሲፃፍ ነበር፤ እየተፃፈም ይገኛል።[1]

የእድገቱ ሂደትና የህትመቱ ሁኔታ ከብዛት እና ከተከታታይነት አኳያ ሲታይ አንዳንዴ ዝቅ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከፍ እያለ ዛሬ ላይ ይድረስ እንጂ ገና ከመጀመሪያው ለስነፅሁፍ እድገት መሳካት ደፋ ቀና እያሉ ለዛሬ ካደረሱት አንጋፋ ደራሲዎች መካከል ጋዲሳ ብሩ፣ ዳባ ወዬሳ፣ ኩምሳ ቡራዩ፣ ኢሳያስ ሆርዶፋ፣ ተጠቃሾች ናቸው። ከነዚህም ውስጥ ኢሳያስ ሆርዶፋ ለኦሮምኛ ስነፅሁፍ ዕድገት ጉልህ አስተዋፅኦ ካበረከቱት መካከል በልቦለድ ብቻ ሳይሆን በድራማም ጭምር የሚጠቀስ ሰው ነው። ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ውስጥ በሚሰራበት ጊዜ እንደ "Fooziyaa" (ፎዚያ)፣ "wajjin Duunaa" (አብረን እናልፋለን) በኋላ 'ህዊ'፣ "Gudii Sadii" (ሶስት ጉዶች)፣ "Dura Hafe" (መጀመሪያ ቀረ)፣ "Raajii Waatilee" (አግራሞታዊ ጥጃ)፣ "kan Facaasan haamu" (የዘሩትን ያጭዳሉ)፣ "Warqee koo" (የእኔ ወርቅ) እና utuu (ቢሆን ኖሮ) የሚሉትን ድራማዎች አበርክቷል (Hawwii, 1995:5)።

ከነዚህም ውጪ ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሶስት ልቦለዶችን ዕፎ ወደ ህዝቡ ያደረሰው ኢሳያስ አሁንም አራተኛ መፅሐፍ በማዘጋጀት ላይ እንደሆነ በኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር በታተመውና ትልቅ አድናቆትን ባገኘው የፈጠራ ሥራው *Yoomi Laataa*? (መቼ ይሆን?) ላይ ጠቁሟል (*Yoomi Laataa*?፣ 2003፡4)።

---

[1] በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሱ የዘመን አቆጣጠሮች ዓ.ም. የሚል ካልታከለባቸው በስተቀር እንደዚሁ የሚቀመጡ ከሆነ እ.አ.አ. መሆናቸው ነው።

አሁንም ቢሆን የኦሮምኛ ልቦለዶች በቁጥርም ሆነ በአፃፃፍ ረገድ ብዙም እንዳልተራመዱ የሚታወቅ ነው። ለዚህም የተማረው የቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ብሎም ለስነፅሁፍ ቅርበት ያላቸው ሰዎች ከጅምሩ ልቦለዶቹን አንብበው አንዳንድ ስነፅሁፋዊ ትንተና ቢሰጡበት ለቋንቋው እድገት ብሎም ለስነፅሁፉ ማደግ ከመጀመሪያው መሰረቱን ማሳመር ስለሆነ ጠቃሚታው የጎላ ነው ብዬ ስላመንኩኝ ከዚህ ላይ አተኮርኩኝ። ከዚህም በተጨማሪ ኢሳያስ ሆርዶፋ በሦስቱም ልቦለዶቹ ውስጥ ሴቶችን ወካይ ገፀባህሪያት አድርጎ ማቅረቡ በልቦለዶቹ ላይ እንዳተኩር ገፋፍቶኛል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የስነፅሁፍ መመዘኛ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ በተፃፉት ልቦለዶች ላይ ስነፅሁፋዊ ትንተና ማካሄድ ለስነፅሁፉ እድገት አስተዋፅኦ እንዳለው እሙን ነው። በአንድ ልቦለድ ላይ ጥናት በሚካሄድበት ጊዜ በተለይም በኦሮምኛ ልቦለዶች ላይ እምብዛም ሂስ ስላልተሰራበት በጅምሩ አንዳንድ የአነባብ ስልቶችን ወይም የመተንተኛ መንገዶችን ማስተዋወቅ ለቋንቋ እድገት ብሎም በስነፅሁፍ በኩል ያለው ጠቀሜታ አጠያያቂ አይሆንም። ይህ ጥናት በማካሂድባቸው በደራሲ ኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ላይ አጥኚው እስከሚያውቀው ድረስ ሶስቱንም ልቦለዶች በአንድነት ያነሳ አጥኝ አላጋጠመውም፤ ነገር ግን አንዳንድ አጥኚዎች ከሌሎች ርዕስ ጉዳዮች ጋር እግረ መንገዳቸውን በነካ ነካ ያነሱ አልጠፉም። ከዚህም የተነሳ እነዚህ ልቦለዶች አንድ ላይ ቢጠኑና ከተያዘው ርዕስ አንፃርም ስነፅሁፋዊ ትንተና ቢደረግባቸው ለስነፅሁፉ እድገት ብሎም ለሌሎች ተመራማሪዎች የሚሰጠው ጥቅም የላቀ ይሆናል ከሚል ነው።

- በሌላ በኩል ደግሞ ደራሲና ጋዜጠኛ ኢሳያስ ሆርዶፋ በልቦለዶቹ ውስጥ እስከ አሁን ለምን ሴቶችን ዋና ገፀባህሪ አድርጎ ይስላል? የሚለው ነገር ልቦለዶቹ ላይ እንዳተኩር አድርጎኛል። በይበልጥ ደግሞ በሶስቱም ልቦለዶች ውስጥ የሴቶቹ ጎልቶ መታየት እነርሱ ላይ እንዳተኩር አድርጎኛል።
- የእነዚህ ሴቶች እንደወካይ ገፀባህሪ መመረጥ ለልቦለዶቹ የፈየደው ነገር አለን? ወይስ ለምን ሴቶች? የሚል በአእምሮዬ ይመላለስ ስለነበር ነው።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያትን ግላዊ መረዳት መተንተን ነው።

ዝርዝር ዓላማዎች፡-

- በደራሲው እስካሁን በታተሙ ሶስቱም ልቦለዶች ውስጥ ዋና ዋና ገፀባህሪያቱ የሚወክሉትን ትውልድ፣ ዘመንና የዘመን መንፈስ ማሳየት፡-
- ገፀባህሪያቱ ከተቀረፁባቸው መቼቶች አንፃር ስለ ራሳቸው ያላቸው ግላዊ እይታ ማሳየት፡-
- በድርሰቱ ታሪክ ውስጥ ለሴቶቹ የሰጠውን ማህበረ ባህላዊ ደረጃ መፈተሽ፡-
- ሴቶቹ ስለ ደራሲው እምነት፣ ፍላጎት እና አመለካከት ሊጠቁሙን የሚያስችሏቸውን እውነታዎች ማመላከት
- ሴቶቹ የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ጉልህ ነጥቦች ማውጣት፡-
- ሴቶቹ በሶስቱም ልቦለዶች ውስጥ እንደ ወካይ ገፀባህሪ የተመረጡበትን ምክንያት መግለፅ፡-

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ላይ የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ግላዊ መረዳት (self perception of major female characters) በማጥናት በኩል የመጀመሪያ ስራ እንደመሆኑ የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል የሚል እምነት አለኝ።

- የሴቶች ግላዊ መረዳት በኦሮምኛ ልቦለዶች ላይ በአማርኛ ቋንቋ በማቅረብ የመጀመሪያ ጥናት እንደመሆኑ መጠን ለተለያዩ አጥኚዎች እና የስነፅሁፍ ባለሙያዎች እንደ አንድ የመተንተኛ መንገድ ማሳያ ሊወሰድ ይችላል ተብሎ ይገመታል።
- የኦሮምኛ ልቦለዶች በአሁኑ ሰዓት "የመርማሪ ያለህ!" እያሉ በሚጮሁበት ጊዜ ትልቅ እና ረቂቅ ግለሰባዊ፣ ማህበራዊና ታሪካዊ እውነታዎችን ፈልፍሎ ለማውጣት የሚያስችሉ አዳዲስ አቀራረቦችን ለማወቅ እንደ አንድ መንገድ ከፋች ሊያግዝ ይችላል ተብሎ ይገመታል።
- የኦሮምኛ ስነጽሁፋዊ ስራዎችን በትክክል ማንበብ እና በወጉ ለመረዳት የሚያስችሉ አማራጭ የንባብ እና የመተንተኛ ስልቶችን (approaches) ያስተዋውቃል
- የኦሮሚያን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ታሪካዊ ገጽታዎችን ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች ጥሩ ፋይዳ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ።
- በኢትዮጵያ ቋንቋችና ስነፅሁፍ ጥናት ውስጥ አንድ ተጨማሪ ምዕራፍ ይከፍታል የሚል ግምት አለኝ።

- ቋንቋውን ለማያውቁ የስነፅሁፍ ምሁራን፣ ለአፋን ኦሮሞ ተማሪዎች እንዲሁም ለስነ ፅሁፍ ቅርበት ላላቸው በሙሉ እንደ አንድ ማጣቀሻ ሊወሰድ ይችላል የሚል ግምት አለኝ።

## 1.5. የአጠናን ዘዴ

የሚጠናው ርእሰ ጉዳይ በቤተመፃህፍት ውስጥ የተገደበ በመሆኑ፣ በቤተመፃህፍት ውስጥ ለሚደረግ ምርምር ስለ ገፀባህሪያት ማንነትና ምንነት፣ አይነቶች፣ የአሳሳል ዘዴ፣ የገፀባህሪያት ግላዊ መረዳት እንዲሁም በዚህ ዙሪያ ሰፊ ጥናት ያደረጉ ምሁራን የሰጡዋቸውን ሃሳቦች ከመፃህፍትና ከተለያዩ መዛግብት እንዲሁም የተለያዩ ጆርናሎችንም ጭምር ለማሰስ ተሞክሯል። ጥናቱን በተጨማሪ መረጃ ለማጠናከርም ቀደም ሲል በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶችን እና በተለያዩ ሴሚናሮች ላይ የቀረቡትን ጥናቶች ለማየት ተሞክሯል። ከቤተ መፃህፍት ምርምሩ በኋላ ወደ ተመረጡ ልቦለዶች በመመለስ ጥልቅ ንባብ ተደርጎበታል። ወደ ትንተና ከመግባቱ በፊት ለግንዛቤ እንዲያመች የልቦለዶቹ የመቼት ትውውቅ ተደርጎል። ትንተናውንም በልቦለዶቹ የህትመት ዘመን ቅደም ተከተል ለማድረግ የተሞከረ ነው። ወደ ይዘት ትንተና የሚያጋድለው ይህ ጥናት ዋና ገፀባህሪያቱ ራሳቸውን እንዴት እንደሚያዩ፣ የሴቶቹን ውክልና (Representation) እና የሴቶቹን ሁኔታ ከማህበረ ባህላቸው አኳያ ለመመልከት የትንታኔና የትርጓሜ (analysis and interpretation) አካሄድን ተከትሏል። ለትንተናው እንዲያመች ከተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚሄዱ ማስረጃዎች እንዳስፈላጊነቱ ከሶስቱም ልቦለዶች እየተፈራረቁ ተጠቅሰዋል። ስለዚህ ለጥናቱ የተመረጡትን ልቦለዶች በጥልቀት በማንበብ ጥናታዊ ፅሁፉን አጠናክሮ ማቅረብ ነው። ለዚህም ከልቦለዶቹ የወጡትን ቃላት፣ ሀረጋትና ዐረፍተ ነገራት በነፃ ትርጉም ወደ አማርኛ በማምጣት ጥናቱን ለማደራጀት ተችሏል።

በኢሳያስ ሆርዶፋ የኦሮምኛ ልቦለዶች ውስጥ የወካይ ገፀባህሪያትን ግላዊ መረዳት እና ውክልና ለመመርመር ዓላማው አድርጎ የተነሳው ይህ ጥናት በአራት ምዕራፎች ተከፋፍሎ ቀርቧል። የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ ፋይዳ፣ የአጠናን ዘዴ፣ የጥናቱ ወሰን እና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች የተገለፀበትና የተብራራበት ክፍል ይዟል። ሁለተኛው ምዕራፍ፣ ከለላ ድርሳነ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት እና ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት የተገለፀበት ክፍል ሲሆን በንድፈ ሃሳባዊ ቅኝቱ ስር የግላዊ መረዳት እና የውክልና

(representation) ፅንሰ ሃሳቦች እንዲሁም የእንስታዊያኑን ሃሳብ በመጠኑ የተቃኙበትና የተብራሩበት ክፍል ነው። ሶስተኛው ምዕራፍ የጥናቱን ሰፊውን አካል የያዘ ነው።

ይኸውም የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ግላዊ መረዳት በሚል ሴቶቹ ለማህበረ ባህላቸው፣ ማህበረ ባህሉ ለሴቶቹ የሚሰጠውን ማህበረባህላዊ ደረጃ፣ በአጠቃላይ ሴቶቹ ለህይወት ያላቸው አመለካከት እና አጠቃላይ ስብእናቸው በሶስቱም ልቦለዶች ውስጥ በጠቋሚ ቃላት፣ ሀረጋትና ዐረፍተ ነገራት መሪነት ሰፊ ትንታኔ የተሰጠበት ክፍል ነው።

በዚሁ ንኡስ ምዕራፍ ስር የሴቶቹ ውክልና (representation) የታየበት ክፍል ሲሆን እዚህ ስር ፍካሬያዊ ትንታኔ የተሠጠበት ክፍል ነው። ትንታኔ ሲደረግም ሶስቱን ልቦለዶች በተናጠል ለየብቻ እንደየአስፈላጊነቱ ደግሞ አንድ ላይ በማዳበል የታየበት ነው። የመጨረሻው ምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ሲሆን ጠቅላላ የጥናቱ ጨመቅ ምን እንደሆነ የተገለፀበትና የሥራውን ጠቅላላ ሂደት ጠቅለል ተድርጎ የተቀመጠበት ክፍል ነው።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን (ገደብ)

ጥናቱ ካሉት የልቦለድ አለባዊያን መካከል በዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ግላዊ መረዳት እና ውክልና ላይ ብቻ ያተኩራል። በልቦለዶቹ ውስጥ የሚገኙት የሶስቱንም ሴቶች ሁኔታ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ከነ ሁኔታቸው መተንተን ላይ የተገደበ ነው። በሌሎች ገፀባህሪያትና የልቦለድ አለባዊያን ላይ ትንተና ለመስጠት ያላቀድኩት ጥናቱ እንዳይንዛዛና ወሰን እንዳያጣ ከሚል ስጋት ነው።

## 1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ እርምጃዎች

በጥናቱ ወቅት ከገጠሙኝ ችግሮች መካከል ዋነኛው በሴት ገፀባሪያት ግላዊ መረዳት ላይ የተሰሩ ንድፈ ሃሳባዊ መረጃ ሊሰጡና የአተናተን ስልት ሊያሳዩ የሚችሉ ጥናቶችን ማግኘት አለመቻሉ ነው። እንዲሁም የውክልናንና የመረዳትን (representation and perception) ፅንሰ ሃሳቦች የሚያስረዱ በቂ ፅሁፎች አለመኖራቸው ሌላው ችግር ነበር። ለነዚህ ችግሮች በተቻለ መጠን በተገኙት ነገሮች ለማሟላት ተሞክሯል።

ሌላው በጥናቱ ወቅት ካጋጠሙኝ ነገሮች ውስጥ አንድ ቀን በቤተ መፃህፍት ያገኘሁትን የጥናት ፅሁፍ (ቲሲስ) እቤት ገብቼ እንደገና ስመለከተው ያልተሟሉ ጉዳዮች መኖራቸው ሲታወቃኝ ያንኑ የጥናት ፅሁፍ ተመልሼ ማግኘት አለመቻሌ ነው። ዛሬ የተነበበ የጥናት ፅሁፍ አንዳንዴ ከቤተመፃህፍት ውስጥ ጠፍቶ ያድራል። እሂም አንዱ ችግር ነበር። ለዚህም ለሚመለከተው አካል አሳውቆ ከመተው ውጪ የሚደረግ ነገር የለም።

## ምዕራፍ ሁለት፡ ክለሳ ድርሳን

በዚህ የክለሳ ድርሳን (Literature Review) ክፍል ውስጥ የተዛማጅ ስራዎች ቅኝትና ንድፈ ሃሳባዊ ጥቂምታዎች በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

### 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

አብዛኞቹ የሴት ገፀባህሪያትን ሁኔታ በአማርኛም ሆነ በኦሮምኛ እንዲሁም በውጪ ቋንቋ የፈጠራ ሥራዎች ውስጥ ያላቸውን ገፅታ የሚጠቁሙ ጥናታዊ ፅሁፎች የቀረቡት ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ሲሆኑ ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪና ለተለያዩ ሴሚናሮች የቀረቡት ግን በጣም ውስን ናቸው ። ለፒኤችዲ በዚህ ዙሪያ የተሰራ አጥኚው እስከሚያውቀው ድረስ አንድም አልተገኘም። ይህም ሆኖ የሴት ገፀባህሪያት ግላዊ መረዳትን (self perception of female characters) በቀጥታ የተመለከተ ጥናት በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርትም ሆነ በውጪ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል እንዲሁም በኦሮምኛ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የተደረጉ ጥናቶች ባለመኖራቸው የደራሲውን ሥራዎች በተመለከተ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት አይኖርም። ነገር ግን የደራሲውን ሥራዎች በሌላ መንገድ ያነሱትንና እግረመንገዳቸውን ከደራሲው ሥራዎች ውስጥ አንድ ወይም ሁለት የፈጠራ ሥራዎቹን ለተነሱለት ዓላማ ግብ መችነት የተጠቀሙትን አጥኝዎች ሳልጠቅስ አላልፍም። ያም ሆኖ ግን በሌሎች ደራሲዎች በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ ሥራዎች ውስጥ የሴቶችን ሁኔታ በስነፅሁፍ ውስጥ ከተለያዩ እይታ አንፃር የተመለከቱ ጥናቶች ተገኝተዋል። በአንድ ነጠላ ጉዳይም ቢሆን መመሳሰል ነውና ተቃኝተዋል።

በተዛማጅ ጥናት ሊጠቀሱ ይችላሉ ያልኳቸው ሥራዎችን በየትምህርት ክፍሎቹ በመመደብ አቀርባለሁ።

### ሀ. በኦሮምኛ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረቡ

የመጀመሪያው ጥናት "Haala Fayyadama Bifoota Yoomessaa Asoosamoota Hawwii fi Yeroon Siif Haadhiistu." (የመቼት አጠቃቀም መልኮች በሀዊ እና የሮን ሲፍ ሃዲስቱ ልቦለዶች ውስጥ) በሚል ርዕስ በ2002 በረመዳን ሞሃመድ ሳኒ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ የቀረበው ጥናት በሁለቱም ልቦለዶች ውስጥ የመቼት አጠቃቀም መልኮች ምን ይመስላል? የሚለውን ጉዳይ አላማው አድርጎ የተነሳ ሲሆን ሥራውንም በአራት ምዕራፎች ከፋፍሎ አቅርቧል።

በተለይ በምዕራፍ ሦስት የተለያዩ የመቼት መልኮችን ከልቦለዶቹ አንዳንድ ሃሳብ እያጣቀሰ ያብራራበት ሁኔታ ይታያል። "ማጠቃለያ እና ግኝት" በማለት በምዕራፍ አራት ስር ያስቀመጠው በሁለቱም ልቦለዶች ውስጥ ምድራዊ መቼት (Geographical Setting) የሚባለው የመቼት መልክ በይበልጥ እንደሚዘወተር ገልጿል፤ ነገር ግን ሶስቱም የመቼት መልኮች ማለትም ታሪካዊ መቼት (historical setting)መልክአምድራዊ መቼት (Geographcial setting) እና አካባቢያዊ የመቼት መልኮች (physical environment) እንደተንፀባረቁ በማመላከት ጥናቱን አጠናቋል።

ሁለተኛው ጥናት በ2009 በደገመኝ ኮንቼ ቶላ "xiinxala mala Barreeffama Asoosamoota Hawwii fi Yeroon siif Haadhiistu." (የአፃፃፍ ስልት በሀዊ እና የሮን ሲፍ ሃዲስቱ ልቦለዶች ውስጥ) የሚል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ የቀረበ ሲሆን በአራት ምዕራፎች ተከፋፍሎ ቀርቧል። ደገመኝ ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው የልቦለዶቹን የአፃፃፍ ስልት ማመላከት የሚል ሆኖ በዚህም ረገድ ያለውን ጠንካራና ደካማ ጎን ለመማመላከት እንደሆነ ይገልፃል። በአራተኛው ምዕራፍ ማጠቃለያና የመፍትኼ ሃሳብ በሚል ርዕስ ስር ልቦለዶቹ ጠንካራም ደካማም ጎን እንዳላቸው ጠቁሟል። ጠንካራ ያሰኛቸው በቃላት አጠቃቀም፣ በምልስቱ እና የማነፃፀሪያ ቃላት በአግባቡ በመጠቀሙ ነው ይላል። ነገር ግን ድክመት ብሎ ያለውን አላሳየንም።

ሌላው "Xiinxala Gooban galeessa Asoosama *Yoomi Laataa*? Keessatti" (የዋና ገፀባህሪ ትንተና በዮም ላታ? ልቦለድ ውስጥ) በሚል ርዕስ በ2011 በአህመድ አብዲ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ የቀረበ ጥናት ነው። ይህ ጥናት ከርዕሱ ሲታይ የልቦለዱን አንድ ዋና ገፀባህሪ የሚያይ ይመስላል። ከምን አኳያ? የሚለውን ጥያቄ ባይመልስም በውስጡ አራት ገፀባህሪያትን አንስቶ ከውስጣዊና ውጫዊ፣ የገፀባህሪያቱን ቀጣይነት እና ተአማኒነታቸውን የተነተነው አህመድ በመጨረሻው ምዕራፍ ከነዚህ አኳያ እንደሚተነትን ይናገራል። ሲንቶሊናን እንደ አንድ ዋና ገፀባህሪ ያነሳው ይህ ጥናት ዓላማ ብሎ የተነሳበት ጉዳይ እና የሠራው ሥራ አይገናኝም። እንዲሁም በርዕሱ ላይ መሰረታዊ ማስተካከያ የሚፈልግ ጥናት ነው።

## ለ. በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡ

ለድህረ ምረቃ ትምህርት መረሃ ግብር የቀረበው የጥላሁን ተሊላ ጥናት "የኦሮምኛ ሥነፅሁፍ ፊር" በሚል በ1998 የቀረበ ሲሆን ይህ ጥናት የኦሮምኛ ስነፅሁፍን በፊር /pattern/ ከፋፍሎ ለማጥናት ዓላማው አድርጎ የተነሳ ሲሆን ቋንቋው በተለያዩ ፊደላት ሲጠቀም የነበረበትን

ዘመን "The first phase of Afan Oromo writing" በማለት ከዛ በኋላ ያለውን ማለትም በአንድ ፊደል መጠቀም ሲጀምር ጀምሮ ያለውን ደግሞ "The second phase" በማለት በሁለት ዋና ዋና ዘውጎች በመከፋፈል አስራ ስምንት (18) የኦሮምኛ ሥራዎቹን መርምሮ በአምስት ምድብ በማደራጀት አጥንቷል። አከፋፈሉም የፈጠራ ሥራዎችን ተተኳሪ ነጥቦች ማለትም ሥነፅሁፎቹ የሚያተኩሩባቸው ተመሳሳይ ነገሮች ከግምት በማስገባት የተደረገ ድልደላ ነው። በዚህም፡-

**አንደኛ ምድብ፡-** የደርግን ዘመን የሚመለከቱ ሥራዎች

**ሁለተኛ ምድብ፡-** ከዘመነ ኃይለ ሥላሴ በፊት ጀምሮ እስከ ዘመነ ኢህአዴግ የሚደርሱትን ሥራዎች። በተለይ ትኩረታቸው ከኦሮሞ አንፃር ሁኖ የኦሮሞነትን ስሜት በማስረፅ ላይ ያነጣጥራሉ።

**ሶስተኛ ምድብ፡-** ከ1984 ዓ.ም. ወዲህ ህዝቡን ማዕከል በማድረግ በኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) እና በኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት መካከል ያለውን ልዩነት ያነሳሉ የተባሉት ተመድበዋል።

**አራተኛ ምድብ፡-** በባህላዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረጉ የፈጠራ ሥራዎች ሰፍረዋል።

**አምስተኛ ምድብ፡-** የየራሳቸው ተተኳሪ ጉዳይ ያላቸው የተባሉት ሁለት ሥራዎች ለብቻ ተመድበዋል።

ሀዊ የተሰኘው የኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለድም በሁለተኛ ምድብ ውስጥ ተካቷል። በዚህም የተነሳው ቁምነገር አጠቃላይ የልቦለዱ መንፈስ የሚጠቁም ሆኖ የ1960ዎቹን የተማረ ትውልድ አስተሳሰብ የተንፀባረቀበት፣ የወቅቱ ምሁር የራስ አመለካከት "የእኔነት" ስሜት የተነሳበት ክፍል ነው። በይበልጥ የልቦለዱ ጭብጥ የተገለፀበትና የዘመኑ መንፈስ የተጠቆመበት ክፍል ነው። እዚህ ውስጥም ሀዊ እንደ አንድ ዋና ገፀባህሪ ከመነሳት ውጪ የተለየ ትኩረት የላትም።

ሁለተኛው ጥናት በድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራም "እንስታዊ የስነፅሁፍ ሂስ ከ1984-1997 ዓ.ም. በታተሙ የሴቶች የግጥም መፃህፍት ውስጥ" በሚል ርዕስ በ2000 ዓ.ም. በአዲሱ ዘገየ የቀረበው ጥናት እንስታዊ የሥነፅሁፍ ሂስን እንደ አንድ አንፃር በማየት ፈለጉ አድርጎ የተከተለው ይህ ጥናት የንቅናቄው መሪዎች ያወጡትን የሥነፅሁፍ ቲዎሪ መሰረት በማድረግ

በአማርኛ ቋንቋ ከታተሙት የግጥም መፃህፍት መካከል የተመረጡትን በቲዎሪው መነሻ ሃሳብ ቃኝቶ አቅርቧል።

ይህ የአዲሱ ሥራ ሁለት የትኩረት አቅጣጫዎችን ይዞ የተነሳ ሲሆን የወንዶች የፈጠራ ሥራዎች ስለሴቶች ያለውን አመለካከት ሚዛናዊነት መመርመርና የተዘነጉ/ትኩረት ያልተሰጣቸው/ የሚላቸውን የሴቶች የፈጠራ ውጤቶችን እንዲያንሰራሩ የሚያደርግ ዓላማ ያለው ነው። የአዲሱ ጥናት አባዊውን የሥነፅሁፍ ዓለም ለሴቶች የወሰነውን ማህበራዊ ደረጃ ከወንድና ሴት ገጣሚዎች አንፃር በጥልቀት የተመለከተ ጥናት ነው።

የይዘት ትንተና ላይ በማተኮር በተመረጡ የግጥም መፃህፍት ውስጥ ያሉ ፆታዊ ዝንባሌ የሚታይባቸውን ግጥሞች ተንትኖ አቅርቧል። በተለይም በሦስተኛው ምዕራፍ የተመረጡ የወንዶችና የሴቶች ግጥሞችን ትንታኔ አቅርቧል። ወንድ ገጣሚዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሴትን የተዛባ ምስል የሚገልፁ የኢትዮጵያውያን የግጥም ሥራዎችን መመልከቱን ይጠቁማል።

አዲሱ 1984 ዓ.ም.ን መነሻ 1997 ዓ.ም.ን መድረሻ ወሰን አድርጎ የተነሳባቸውን ምክንያቶች በመጠቆም ከወንድ ገጣሚዎች የደበበ ሰይፉ፣ ለራስ የተፃፈ ደብዳቤ (1992 ዓ.ም)፣ የበእውቀቱ ስዩም፣ ኗሪ አልባ ጎጆዎች (1995 ዓ.ም)፣ የአማኑኤል መሐሪ፣ ጥለት (1996 ዓ.ም) ተመርጧል።

የሴቶች የግጥም መፃህፍትም የመቅደስ ጀንበሩ፣ ንባሰል (1994 ዓ.ም)፣ በተለያዩ ሴት ደራሲያን የተገጠሙ፣ እኛ 170 ግጥሞች (1990 ዓ.ም)፣ የሙሉ ሰለሞን ብዙነህ፣ ጊዜ (1992 ዓ.ም)፣ የሰናይት አበራ፣ የጨረቃ ሳቆች (1995 ዓ.ም)፣ የትርሲት በቀለ፣ ፍላፆ(1995 ዓ.ም)፣ የታሪኳ ገብረየስ፣ እስኪነጋ ድረስ (1997 ዓ.ም) ናቸው። የተመረጡበትን ምክንያት ሲያስረዳ ሁሉም ግጥሞች በየዘመናቸው ጥሩ ተቀባይነትን ያገኙ መሆናቸውን በመጠቆም በብዛት የሴቶቹን ሥራ የወሰደበትንና የወንዶቹንም ያካተተበትን ምክንያት ሲያስቀምጥ እንስታዊ የስነፅሁፍ ሂስ ትኩረቱ በወንዶች የፈጠራ ሥራ ላይ በመሆኑ የወንዶችን ድርሰቶች ማካተት እንዳስፈለገ ገልጦ ርዕሱ እንደሚያመላክተው የሴቶች የግጥም መፃህፍትን በእንስታዊ የስነፅሁፍ ሂስ አተያይ ይተነትናል ስለሚል ለዚህም ሲባል የጥናቱ ትኩረት ወደ ሴቶቹ የፈጠራ ውጤቶች እንዳጋደለ ይጠቁማል።

## ሐ. በውጪ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡ

የመጀመሪያው በድህረ ምረቃ የትምህርት ፕሮግራም የቀረበው ጥናት በሙሉ መብት ዘነበ በ1996 ምስለ/ገፀ/ሴትን አስመልክቶ "A comparative Analysis of the Images of Men and Women in the works of some Ethiopian Women Writers" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን፣ ከዚህን በፊት በብዛት በአንድ ፆታ ተወስኖ ይቀርብ የነበረውን የሴቶች ምስል በሁለቱም ፆታዎች ላይ በማተኮር ንፅፅራዊ ጥናትን ያካሄደ፣ ሚዛናዊነትን ለመጠበቅ የተጣረበት ጥናት ነው ለማለት ይቻላል።

በሦስት ምዕራፎች ብቻ ተጠቃሎ የቀረበ ይህ ጥናት በአውሮፓውያን፣ በአሜሪካውያንና በአፍሪካውያን ስነፅሁፍ ውስጥ ምስለ /ገፀ /ሴት/ images of women/ እንዴት እንደተቀረፀ አጥኝዋ አመላክታለች።

በተመረጡ መፃህፍት ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ወንድና ሴት ገፀባህሪያት ወንዶቹ እንደ ግፈኛ/ጨቋኝ/፣ ሴቶቹ እንደ ግፍ ተቀባይ /ተጨቋኝ/ አካል ሆነው እንደተሳሉ ከድርሰቶቹ ማስረጃ በማቅረብ ታመላክታለች። አባዊው ስርአት ሴቶችንና ወንዶችን እንደጎዳቸው ሲታመላክት በይበልጥ ግን የሴቶቹ ጉዳት እንደሚያይል ትናገራለች። ጠንካራ ተደርጎ የተሳሉትን ሁለቱም ፆታዎች ከተነተነ በኋላ ለንፅፅር የሚያቀርብ ይህ ጥናት ወንዱን ግፍ ፈፃሚ ሴቷን ደግሞ ግፍ ተቀባይ በማለት ትሰይማቸዋለች።

ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ እንደሚታየው በፈጠራ ሥራዎች ውስጥም የገኙነት ቦታ እንዳልተሰጣቸው (እንዳላገኙ) የሚቆጥር ነው። ወግና ልማድ ሴቶችን ብቻ እንደጎዳቸው አጥኝዋ ትናገራለች። ጠንካራ ብሎ ማህበረሰቡ የሚቀበለው አካልም ወንድን ብቻ እንደሆነ ከፈጠራ ስራዎቹ እንደ አስረጅ በማድረግ ታቀርባለች። ሴት ደራሲያት የሚቀርፁት ገፀባህሪያት ደግሞ ተአማኒነት የሚጎድላቸው ከደራሲያቱ የግል ፍላጎት ብቻ የመነጩ የሚመስል አይነት ነው በማለት ትተቻለች።

መኮንን ዘገዬ " Images of Women and plot structure in the first four Novels of Fikiremarkos Desta" በሚል ርዕስ በ2000 ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም የቀረበው ጥናት የሴቶችን ምስል ስለሚያነሳና ሴቶችን ከማህበረባህላዊ አንፃር ስለሚያይ ብቻ በተዛማጅነት ተመልክቻለሁ። ይህ ጥናት ከአዲሱ ዘገዬ ጥናት ጋር በመጠኑም ቢሆን የሚመሳሰል ሲሆን ስለአባዊ ስርአትና ስለ ፆታ ጥያቄ አንስቶ፣ የእንስታዊነትን ምንነት እንዲሁም ስለእንስታዊ

የስነፅሁፍ ሂስ አንዳንድ ነገሮችን የሚያነሳ ጥናት ነው። ምስለ ሴትን በተመለከተ በአሜሪካና በአፍሪካ ያሉ ጥናቶችን ከጠቀሰ በኋላ በኢትዮጵያ ያሉትንም ጥናቶች ለብቻ ይቃኛቸዋል።

የባህል ሰለባ (victims of culture) ስለሆኑ ሴቶች በማውጣት ከባህሉ ነፃ ለመውጣት የሚፍጨረጨሩትን ሴት ገፀባህሪያት ያመላክታል። ነገር ግን ሴቶቹ ባህሉን እንዴት ይቀበሉታል? ወይም እንዴት ያዩታል? የሚለውን ነገር አይመለስም። ከባህል ተፅዕኖ የተነሳ ጉዳት የሚደርስባቸውን ሴቶች አስመልክቶ ከተፅዕኖ ነፃ ለመውጣት ሙከራ ያደረጉትንና የተሳካላቸውን እንዲሁም ያልተሳካላቸውን ሴቶች በማቅረብ የአተያይ ሚዛናዊነቱን አሳይቷል።

መኮንን ፊቃዱ "Images of Women's in the Fictions of selected African Women writers: A comparative Black Feminist study" በሚል ርዕስ በ2005 የቀረበ ጥናት ስለ እንስታዊነት ምንነት፣ የእንስታዊ ስነፅሁፍ ሂስ ምንነት፣ በአፍሪካ ውስጥ ስላለ የእንስታዊያን እንቅስቃሴ በብዛት የተረከበት ሁኔታ ይታያል።

ይህ ጥናት ስለ አሜሪከውያን፣ አፍሪካውያንና ኢትዮጵያውያን ሴት ፀሐፊዎች አጫጭር መግለጫ ካቀረበ በኋላ በተመረጡ ሥራዎች ላይ ትንታኔና ትርጓሜ አካሂዷል። በዚህም መሰረት የፆታና የመደብ ጭቆና የደረሰባት ሴት ምስል፣ ምስለ እናት፣ ለባህሏና ወጓ የምትቆረቆር ሴት ምስል፣ የቤተሰቦቿን ባህልና ወግ ጠብቃና አክብራ የምትኖር ሴት ምስል፣ በማለት ሰቶች በገሃዱ ዓለም ያላቸውን ማህበረባህላዊ ደረጃ በየወገኑ በመመደብ ሲያቀርብ ይታያል። መኮንን ከኢትዮጵያውያን ሴት ፀሐፊዎች ወጣ በማለት የሌሎች ሃገሮችን ደራሲዎች ሥራ ማካተቱ፡ በተለያዩ ቦታ ያሉ የሴቶች ድምፅ ምን እንደሚመስል ለመገምገም ጥሩ መንገድ ነው።

ሌላው በዚሁ ትምህርት ክፍል ብሩ ተሊላ የተባለ አጥኚ "Images of Female Characters in Hawwii" በሚል የሰራ ሲሆን እሂን የጥናት ወረቀት ለማግኘት የተቻለኝን ሁሉ ባደርግም ከሦስቱም ቤተመፃህፍት የለም ስለተባልኩኝ ሳለየሁ ቀሪቻለሁ።

መ. ሌሎች

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅ ሊሆኑ ይችላሉ ያልኳቸው ጥናቶች በዘሪሁን አስፋው ከቀረቡ ጥናቶች መካከል "የበዓሉ ግርማ ሴቶች አምስት ሃይለኞች" በሚል ርዕስ በ1985 ዓ.ም አምስት ሴት ገፀባህሪያትን በምልዓት ተዳስሶ እናገኛለን። ከአጥኚው ገለፃ እንደምንረዳው ሃይለኞቹ

ሴቶች ለዓላማቸው ስኬት በፅናት የሚታገሉ፣ ጠንካሮች ሆነው እንደተሳሉ ተመልክቷል። የፈለጉትን የማግኘትና ለግባቸው በቁርጥ ውሳኔ የመጓዝ፣ ከአላማቸው ፍንክች ያለማለት ብርታት እንዳለቸው ተገልጿል። የሴቶቹ አካካዊና ህሊናዊ መልክ መመሳሰልም ተገልጿል። የሃይለኛነታቸው ምስጢርም በትንታኔ ቀርቧል። ምናልባትም የሴቶቹ ሃይለኛነት ምንጭ ከተቀረፁበት የህይወት ቅንብብ፣ ከገቡባቸው ሁኔቶችና ከስብዕናቸው የሚነሳ፣ ወዘተ መሆኑ ተገልጿል።

"መልክዓ ሴት በአማርኛ አጭር ልቦለድ በሶስት ደራስያን ናሙናነት" በሚል ርዕስ በ1988 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለዘጠነኛው ዓመታዊ ሲሚናር በዘሩሁን አስፋው የቀረበ ጥናት በተመረጡ ደራሲያን አጭር ልቦለዶች ውስጥ የሴት ገፀባህሪያት ጠንካሮች ሆነው የተሳሉበትን ሁኔታ ያመላከተበት ጥናት እናገኛለን።

በተለይ በኢትዮጵያ ከ1949 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1986 ዓ.ም በታተሙ ሥራዎች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር ባላቸው ማህበራዊ ቁርኝነት (Women as defined interms of men's need) አንፃር እንደ ቀረቡ የተጠቆመበት ጥናት ነው።

በመቀጠልም ዘሪሁን በ1997 ታህሳስ ወር በኪዮቶ በቀረበው አስራ ሦስተኛው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ጥናት ጉባኤ ላይ "Women in the works of Ethiopian short story writers" በሚል ርዕስ በተመረጡ አስር ደራሲዎች የተፃፉ መቶ ሰላሳ ሶስት አጭር ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ መቶ ሴት ገፀባህሪያት የተሳሉበት ሁኔታ በትክክል የተዳሰሱበት ጥናት ይገኛል።

ሴቶች በእናት፣ በሚስት፣ ባላገባች ሴት፣ በሴተኛ አዳሪ፣ በብቸኛ ሴት እና የቤት አገልጋይ ሴት በሚሉ ስድስት ዘውጎች ተወስኖ ቀርቧል። እነዚህ ኢትዮጵያውያን ደራሲዎች ሴቶችን በዋናነት በእናት፣ ሚስትና የፍቅር ጓደኛ አድርገው እንደሳሉ ተመልክቷል። ይህ አሳሳል ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ለሴት ልጅ ከሚሰጠው ማህበራዊ ደረጃና የወንድን ፍላጎት ከመሙላት አንፃር እንደሆነ አመላክተዋል።

በእስካሁን ድረስ በዝርዝር የቀረቡ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በሙሉ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ከእያንዳንዱ ጥናት ጋር ለማየት ያልተሞከረበት ምክንያት እነዚህ ጥናቶች በሙሉ በአንድ ነጠላ ጉዳይ ያውም ሴቶችን ከማህበረ ባህላዊ አንፃር

የተመለከቱ በመሆናቸው ብቻ ነው። ሌሎች ደግሞ የደራሲውን ሥራ ስላነሱ ብቻ እንደዚህም ተሰርቷል ለማለት ያህል እንጂ ከሁሉም ጥናታዊ ፅሁፎች ጋር መሠረታዊ የሆነ ልዩነት አለን።

## 2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

### 2.2.1. የመረዳት ፅንሰ ሃሳብ

መረዳት (perception) የሚለው ቃል በተለያዩ መዝገበ ቃላት እና ኢንሳይክሎፒዲያ ውስጥ በተለያየ መልክ ተበይኖ እናገኛለን። ለምሳሌ ያህል *The American Heritage Dictionary of the English Language* (2004) የሚለው መዝገበ ቃል ውስጥ "Perception is the process, act or faculty of perceiving something," በማለት ሲያስቀምጥ፤ በመቀጠልም "perception is the effect product of perceiving. It is the mental organization and interpretation of sensory information በማለት ተጨማሪ ማብራሪያ ይሰጣል። መረዳት የሚለውን ቃል አንድ ሰው አንድን ነገር እንዴት እንደተቀበለው፣ እንደተረዳው የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን ይገልፃል። እዚህ ላይ "መቀበል" ሲባል በአዕምሮ ውስጥ ለነገሮች የምንሰጠውን ቦታ፣ ትርጉም የሚመከለት ጉዳይ ነው።

እንደ Wikipedia the free encyclopedia ከሆነ ደግሞ መረዳት "Perception is the process of attaining awareness or understanding of sensory information" ትክክለኛ መረዳት የሚመጣው በመጀመሪያ በውስጣችን ላለው ነገር ትክክለኛ ቦታ፣ መልስ ስንሰጠው ነው ወይም መስጠት ስንችል ነው በማለት ያብራራል። በመቀጠልም "perception" የሚለው ቃል የተገኘው "perceptio, percipio," ከሚለው ከላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም "Receiving, collecting and action of taking possession, apprehension with the mind or senses" ይላል። ወደ አዕምሮ ለወሰድነው ነገር ወይም በአዕምሮአችን ውስጥ ላስቀመጥነው ነገር በአዕምሮአችን ትርጉም፣ ብይን ስንሰጠው ነው መረዳት የምንለው ነገር መታየት የሚችለው የሚል ሃሳብ ያስቀምጣል።

Lindsay and Nurman (1977), በመጥቀስ እንዳለው ሞላ እንዳስቀመጠው "Perception in humans describes the process where by sensory stimulation is translated in to organized experience, That experience or percept, is the joint product of the stimulation and of the process it self" በማለት ያስቀምጣሉ።

Khera, Shiv (2002) እንደሚያስቀምጠው እኛ እንድናስብና እንድንሰራ የሚያደርገን ውስጣችን ያለው ነገር ነው ይላል። የሰው ልጅን ልዩ ከሚያደረጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ የመረዳት አቅሙ ነው። ይህ መረዳት ደግሞ የሚፈልቀው ከውስጥ ነው። ውስጣችን ያለው ነገር የእኛን መረዳት ወይም አስተሳሰብ የመቀየር ሃይል አለው። የሰው ልጅ እርስ በርሱ የሚለያየውም ከዚህ ከውስጣዊ መረዳቱ የተነሳ ነው። የእኛን መረዳት ወይም አመለካከት ወይም አስተሳሰብ የመቀየር ስልጣን ያለው እውስጣችን ያለው ነገር ብቻ ነው ይላል።

(Khera, Shiv 2002፡2) ላይ እንደተገለፀው በሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የተካሄደው ጥናት እንደሚጠቁመው አንድ ሰው በህይወቱ ውስጥ ለውጥ ሲያሳይ ወይም የተሻለ የሥራ እድል ሲያገኝ 85 ከመቶ ሊሳካለት የቻለው ከሰውየው ግላዊ መረዳት (self perception) የመጣ ሲሆን ቀሪው 15 ከመቶ ሊሳካለት የቻለው ከሰውየው ጉብዝና ነው። ከዚህ በመነሳት መረዳት (perception) የሚለው ቃል በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ በጣም አስፈላጊ እንደሆነና የሰው ልጅ የህይወት አቅጣጫ ላይ እንዲሁም በማንኛውም ሰው ስብእና ላይ እና በማንኛውም የሙያ መስክ ላይ ተፅዕኖ ሊያመጣ የሚችል ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን።

> *Our perception determines how we look at a set back. To a positive thinker, perception can be a stepping stone to success. To a negative thinker, it can be a stumbling block (pp.5).*

እንደ 'khera' ሃሳብ ይህችን ዓለም የምናይበት መነፅር በመረዳታችን ልክ ሊወሰን ይችላል። አዎንታዊ መረዳት፣ አመለካከት፣ ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች ይህ መረዳታቸው ለዕድገታቸው የመሰረት ድንጋይ ሲሆናቸው በታቃራኒው አሉታዊ መረዳት፣ አመለካከት፣ ግንዛቤ ላላቸው ደግሞ የማደናቀፊያ ድንጋይ ይሆንባቸዋል። ስለዚህ አንድ ሰው ያለው የመረዳት ክህሎት ለተሻለ ኑሮ ወይንም ለውድቀት ሊዳርገው ይችላል ማለት ነው።

ስለ መረዳት ስናወራ በብዙዎቻችን አዕምሮ ውስጥ ስንወለድ ከመረዳት ጋር እንወለዳለን ወይስ ስናድግ እናገኘዋለን? የሚለው ጥያቄ መጫሩ አይቀርም። ብዙዎች የመረዳት ክህሎቻችን መስመር የሚይዙት ገና ከመጀመሪያው እድሚያችን ነው ይላሉ። ይህ የሚያሳየን ደግሞ ስንወለድ ለመረዳት ከሚያስችለን አቅም ጋር እንደምንወለድ ነው። ከዚህ በመነሳት በአንድ ሰው የመረዳት ክህሎት ላይ ተፅዕኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮች ሦስት እንደሆኑ ያስቀምጣል። እነርሱም፡-

1ኛ. አካባቢ (environment)

2ኛ ልምድ (experience) እና

3ኛ. ትምህርት (education) ናቸው (Khera, 2001:8).

አካባቢያዊ ተፅዕኖ በአብዛኛው የመኖሪያ አካባቢ፣ ትምህርት ቤት፣ የሥራ ቦታ፣ ሚዲያ፣ ባህል(cultural background)፣ ሃይማኖት፣ ልማድ እና እምነት፣ ማህበራዊ ጉዳዮች እና ፖለቲካዊ ዳራዎችን ሊያጠቃልል ይችላል። ትምህርት ደግሞ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ኑሮን እንዴት መግራት እንደሚቻል ብቻ ሳይሆን እንዴት መኖር እንዳለብንም የሚያስተምረን መሳሪያ መሆኑን ያስቀምጣል። ልምድ ደግሞ በሰው ልጅ የእለቱ እለት ኑሮ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው። ከልምዳችን ተነስተን ለወደፊት ህይወታችን ወይም ኑሮአችን እናቅዳለን፤ ለተለያዩ የኑሮ ውጣ ውረዶችም ጭምር ልምድ ጥሩ ትምህርት ቤት እንደሆነ ያስረዳል።

ከነዚህም በተጨማሪ በአንድ ሰው ግላዊ መረዳት (self perception) ላይ ተፅዕኖ ሊያደርሱ ይችላሉ ከሚባሉት ውስጥ እድሜ፣ ተክለሰውነት (በተለይም ለሴቶች)፣ ፆታ፣ ባህል፣ ገቢ (income) ወዘተ. እዚህ ውስጥ ሊጠቃለሉ እንደሚችሉ በተለያዩ ምሁራን ይነገራል።

አዎንታዊና አሉታዊ መረዳት ያላቸውን ሰዎች ከግብራቸው እና ከሚያከናውኑት ሥራ መረዳት እንደሚቻል ይጠቁመናል።

> *People with positive perception have certain personality traits that are easy to recognize. They are caring, confident, patient and humble. They have high expectations of themselves and others. They anticipate positive outcomes (ibid:10-11).*

አዎንታዊ መረዳት ያላቸው ሰዎች ሁሌም ፍሬ እንደሚያፈራ ተክል ነው ይላሉ። "A person with positive perception (attitude) is like a fruit of all seasons. He is always welcome" ይላል። የትኛውም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም እንኳ ከአመለካከቱ፣ ከአስተሳሰቡና ከመረዳቱ የተነሳ ይወጠዋል፤ ለድልም ይበቃል ይላል።

ስለዚህ አዎንታዊ መረዳት፣ ግንዛቤ፣ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ከፍሬያቸው ልንረዳቸው እንችላለን ማለት ነው።

### 2.2.2 የውክልና ፅንሰ ሃሳብ

የውክልናን ፅንስ ሃሳብ አስመልክቶ፣ International Encyclopedia of the Social Science (IESS) እንደሚለው ቃሉን በቀጥታ ይህ ነው ብሎ ለማለት እንደሚያስቸግር ይጠቅስና ለቃሉ የተለያዩ ትርጓሜና ትንታኔ እንደሚያስፈልግ በማስቀመጥ ቃሉን ለመበየን አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ በወካዩና በተወካዩ መካከል ክፍተት በመኖሩ እንደሆነ ያስረዳል።

> *The term representation can not be given a definitive meaning because there will always be a gap between intention and realization, original and copy ( pp.172).*

በተጨማሪ በወካይና ነገሩን በሚወክለው ተወካይ መካከል ሁል ጊዜ ክፍተት እንደማይጠፋ በተመሳሳይ ሁኔታ የተለያዩ ምሁራን ይስማማሉ። ስለዚህ የውክልናን ፅንሰ ሃሳብ ለመረዳትና ያለውን ክፍተት ለመሙላት ትንታኔ እና ትርጓሜ አስፈላጊ እንደሆነ ይስማማሉ።

> *..., neither pictures nor sentences nor thoughts represent intrinsically, a picture of a man walking up hill could also be a picture of a man sliding back wards down hill. There is nothing inherent in the picture which makes the first reading more valid than the second. A representation only represents by virtue of being interpreted and ultimately represents any thing it is capable of suggesting (Cavallaro, 2001:39).*

ስለዚህ "አንድ ነገር አንድን ነገር ይወክላል" ብለን ለመናገር ትንታኔና ትርጓሜ አስፈላጊ መሆኑ የብዙ ምሁራን ድምፅ ነው። Dani, Cavallaro በመቀጠልም ነገሮችን ተመልክተን ወይም ተገንዝበን በትክክል "ይህኛው ነገር ይህኛውን ይወክላል" ብለን ለመናገር እንደሚከብድ ትገልፃለች። ምክንያቱን ስታስቀምጥ ይሄኛው ነገር የዚህኛው ወካይ ወይም ተወካይ ነው ለማለት እንደ ተመልካቹ ግላዊ መረዳት ሊለያይ ስለሚችል ነው ትላለች።

> *The world can not be represented accurately and objectively for the reason that it is not a given but rather an effect of how it is perceived from the various view points (Ibid: 40).*

ስለ ውክልና ስናነሳ የተወካይ እና የወካይ ግንኙነት እንዲሁ የተሰጠ፤ የታወቀ ሳይሆን እንደተመልካቹ ወይም እንደወካይ ዓላማና የመረዳት ክህሎት ሊለያይ እንደሚችል ትገልፃለች። ግላዊ አተያይ፣ ባህላዊ ከለላ፣ ማህበራዊ ደረጃ በወካይና ተወካይ መካከል ተመሳሳይ ትርጉም እንዳይኖር ከሚያደርጉት ውስጥ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም የውክልና ፅንሰ ሃሳብ ገና ከመጀመሪያው ከአመለካከት ጋር የተቆራኘ የተቆላለፈ ስለሆነ ነገሩን በቀላሉ ለማስረዳት አዳጋች ይሆናል ትላለች።

> *It is also important to bear in mind that the collusion of representation and ideology is not just a contemporary phenomenon, for representation has been inter wined with ideology throughout human history (Ibid: 41-42).*

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የውክልናና የአመለካከት ጉዳይ እንዲሁ ዝም ተብለው በዘልማድ የሆነ ክስተት አይደለም። በማንኛውም ጊዜ ሊነጣጠሉ የማይችሉ ነገሮች መሆናቸውን ትገልፃለች።

(Hall, 1997) 'The works of representation' በሚለው መፅሐፉ ውስጥ international encyclopedia of the social science' በመጥቀስ ውክልና ውስጥ መዓት ነገሮች ሊነሱ እንደሚችሉ ይጠቁማል። ከጥንት ጀምሮ ውክልና ስነፅሁፍን፣ ኪነጥበብንና ትርጓሜን (semiotics) በማጥናት በኩል ትልቅ አስተዋፅኦ ሲያደርግ እንደኖረ ይገልፃል። ስለዚህ ውክልና ከስነ ፅሁፍና መሰል ጉዳዮች ጋር የጠበቀ ቁርኝት ስላለው የአንድን ማህበረሰብ ብሎም ሃገር ማህበራዊ፣ ፓለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ሊገልፅ እንደሚችል ይነገራል።

> *Representation is a medium or process through which meaning, associations and values are socially constructed and reifiend by people in a shared culture (Ibid: 172).*

እንደ ሆል ገለፃ ለነገሮች ትርጓሜ የምንሰጠው እንደየ አረዳዳችን እንደየአመለካከታችንና እንዳደግንበት ባህልና እንደምንከተለው ርእዮት ሊለያይ ይችላል። ይሁን እንጂ ውክልና ተመሳሳይ ባህልና ቋንቋ ባላቸው ማህበረሰቦች ዘንድም ማንነትንና ምንነትን ለመግለፅ እና ለመወከል በነገሮች ተመሲለው ሊቀርብ እንደሚችል ይናገራል።

The politics of representation, then revolve around the issues of power and control over one's own self and its representations and reproductions by others (Ibid:172).

የውክልና ጽንሰ ሀሳብ አድማሱን ወደ ፓለቲካ፣ ርዕዮት እና አመለካከት ሰፍቶ ትርጓሜው ብዙን ጊዜ በውስጡ የሚንፀባረቁ ጉዳዮች ፓለቲካዊ ጣጣ ያለባቸው ነገሮች እንደሆኑ ይገልፃል።

መላክነህ መንግስቱ (Tuffin, 1995:199) በመጥቀስ በዚህ ሃሳብ ዙሪያ እንዲህ ይላሉ።

> *Representation; is related to the portrayal of individuals, people or historical events. In the context of politics, representation linked to the issues of bias for or against stereotyping and influence of discourse... in fact, no representation is ever neutral but a means through which it is constructed (Melakneh, 2010:70).*

ውክልና፣ ግለሰቦች፣ ማህበረሰቦች ወይም ሰዎች እንዲሁም ታሪካዊ የሆኑ ነገሮች በፓለቲካ ጉዳይ ውስጥ የሚኖራቸውን ገፅታ የሚመለከት ሲሆን ሰዎች ከባህል፣ ከዘር፣ ወዘተ ጥላቻ የተነሳ የሚሰጣቸውን ደረጃ የሚመለከት ነው። ያም ሆነ ይህ ውክልና ከአድልዎ ሊፀዳ አይችልም፤ ነገር ግን እንደየ አገባቡና አገላለፁ ሊለያይ ይችላል።

ለውክልና ቀጥተኛ ትርጉም ወይም ብያኔ ለመስጠት ቃሉ በቀጥታ ከሌሎች ነገሮች ጋር መጣመር አለበት የምትለው spivak; በ 'Ashcroft, et,al., (1989:125)'

...The concept of representation must be reconsidered in connection with representation in politics, representation in the sense of any capacity for a person to be the agent of, to stand for, the will of other people.

በመቀጠልም 'can the subaltern speak' በሚለው ርዕስ ስር እንደጠቆመችው ውክልና ከሌሎች ነገሮች ጋር ተጣምሮ ሲገለፅ በተለይ በኢኮኖሚያዊም ሆነ በፓለቲካዊ አኳኃን ዝቅተኛ ቦታ የሚሰጣቸው ህዝቦች፣ ሃገሮች በአጠቃላይ የተገለሉትን ለመጠቆም እንደሚገባ ታስረዳለች።

... representations, especially of marginalized groups from developing countries, are intimately linked to positioning; socioeconomic, gendered, cultural, geographic, historical and institutional (Ibid:127).

ከዚህ በመነሳት በዓለም ላይ ያሉ ነገሮች ውክልና ሊኖራቸው እንደሚችል እንገነዘባለን። ምክንያቱም የውክልና ፅንሰ ሃሳብ በዋናነት እንደወካዩ ግላዊ መረዳት ስለሚለያይ እንዲሁም ቃሉ እንደየአተረጓጎማችንና እንደየአረዳዳችን ሊለያይ ስለሚችል ለነገሮች የሰጠነው ውክልና በተረዳነውና በተረጎምነው ልክ ሊሆን ስለሚችል ነው። ከዚህ በመነሳት ውክልና ከግላዊ መረዳት ጋር የጠበቀ ቁርኝት እንዳለው እንመለከታለን። "አንድ ነገር አንድን ነገር" ይወክላል ብለን ለመናገር ግላዊ መረዳታችን ወሳኝነት አለው።

## 2.3. የእንስታዊያኑ ሃሳብ በሴቶች ላይ

ስለ እንስታዊነት (feminism) ምንነት በየዘመናቱና በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ብያኔዎች ሲነሱ ኖረዋል፤ እየተነሱም ይገኛሉ። ከነዚህም ውስጥ፡

> *Feminism is a method of analysis as well as a discovery of new materials. It asks new questions as well as coming up with new answer. Its central concern is with the social distinction between men and women, with the fact of this distinction, with its meanings, and with its causes and consequences (Ruth, 1998;5).*

የእንስታዊያኑ ሃሳብ ተነስተው የማያውቁ ወይም ትኩረት ያልተሰጣቸው የፆታ ነክ ጥያቄዎችን በማንሳት ለምላሹም መፍትሄ የሚፈልጉ ሲሆን መሰረታዊ ጉዳያቸው ደግሞ ማህበረሰቡ ለሴቶችና ለወንዶች የሚሰጠውን የማህበረ ባህላዊ ደረጃን ልዩነት ማወቅና መመርመር ሲሆን ለልዩነቱ መፈጠር ምክንያት የሆኑ ትንተና ውጤቱን መረዳት ነው።

ለእንስታዊነት (Feminism) በተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎች ቢሰጡትም ሁሉም ብያኔዎች ግን የሴቶች መብት መከበርን ማዕከል ያደረጉ ናቸው። በመሆኑም እንስታዊነት ሴቶች ከወንዶች እኩል ፓለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ መብት ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚያምን የአመለካከት አይነት ነው።

*Feminism is the movement for the social, political and economic equality of men and women. It maintains that women and men are, and have been, treated differently by society, and that women have frequently and systematically been unable to participate fully in all the available social arenas and social institutions (Peter, 2010:30).*

በየዘመናቱ የሚነሱት የእንስታዊያኑ ትልቁ ዓላማ ሴቶች በዓባዊው ዓለምና አስተዳደር ውስጥ የደረሰባቸውንና የሚደርስባቸውን ማህበረ ባህላዊ አድሎ በራሳቸው እንዲረዱ የሚያደርግና ለለውጥ የሚያነሳሳ፣ ለመብቶቻቸው ድምፆቻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያሰሙ የሚቀሰቅስ የቲዎሪ መሰረት ያለው ነው።

ሴቶችን አላማው አድርጎ የተነሳው ይህ የቲዎሪ እንቅስቃሴ ለሴቶች በግለሰቦችና በማህበረሰቡ ዘንድ ንቃተ ህሊናን መፍጠር/ conscious raising/፣ ስለማንነታቸውና ምንነታቸው፣ ስለ አኗኗራቸው ቆም ብለው እንዲያስተውሉ፣ አባዊው ዓለም የወሰነላቸውን ማህበረ ባህላዊ ደረጃ በመሞገት የራሳቸውን ደረጃ በራሳቸው መወሰን እንዲችሉ የሚያነሳሳ፣ ከሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ያላቸው ግንኙነቶች መወሰን ያለባቸው እራሳቸው መሆን እንዳለበት የሚጠቁም የተቃውሞ ድምፅ ያለው ነው።

ይህ ጥናት የሴቶችን ግላዊ መረዳት እና ውክልና በተመረጡ የኦሮምኛ ልቦለዶች ውስጥ የሚለውን ዋና ዓላማው አድርጎ የተነሳ ቢሆንም በአባዊው ሥርዓት ውስጥ ለሴቶች የሚሰጠውን ማህበረ ባህላዊ ደረጃ ለመመርመር መንገድ ከፍቶለታል። በአባዊው ማህበረሰብ (patriarchal society) ውስጥ ሊደፈሩ፣ ሊነሱ የማይችሉ ጉዳዮችን ቋሚነታቸውን የሚሞግተው ይህ የእንስታዊያን ቲዎሪ "ቋሚ" ተብለው የሚታሰቡትን ሥርዓቶች ትክክለኛነታቸውንና ወገንተኝነታቸውን ይመረምራል፤ ይፈትሻል።

*A movement seeking the re-organization of the world up on a basis of gender equality in all human relations; a movement which would reject every differentiation between individuals up on the grounds gender, that would abolish all gender privileges and burdens, and would strive to set up the recognition of the common humanity of women and men as the foundation of law and custom (Ibid:30).*

እንስታዊያኑ የአባዊውን ሃሳቦች በበርካታ ምክንያቶች ይቃወሙታል። አባዊው ዓለም ለሴቶች ተገቢውን ክብርና ትኩረት እንዳልሰጠ በማስታወስ ሴቶች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ማስተካከል እንዳለባቸው፣ እጅና እግራቸውን አጣምረው እንዲቀመጡ ሳይሆን ጊዜ ሳይሰጡ ድምፃቸውን ማሰማት እንዳለባቸው፣ ለራሳቸው ከራሳቸው ውጪ ሌላ ወገን እንደማይሻል፤ የራሴን በራሴ በማለት መነሳት እንዳለባቸው የሚጠቁም የቲዎሪ አይነት ነው።

"In the patriarchal society, women are historically, socially and politically powerless, culturally mute and insignificant" (Nenola, 1993:49).

እንስታዊያኑ ይሄን በአባዊው ሥርአት ውስጥ በሴቶች ላይ ሲደርስ የኖረውን ጫና የሚቃወም፣ ለሴቶች ድምጽ መሰማት የሚቆረቆርና ፓለቲካዊ ገፅታም የፈጠረ የቲዎሪ አይነት ነው። ለዚህም ነው ይህ ቲዎሪ በዓባዊው ዓለም የተጫነባቸውን ሥርዓቶች መቃወምና መሟገት እንዳለባቸው በተቻለው መጠን የመቀስቀስ ስራን የሚሰራው።

2.3.1. እንስታዊነት እና ባህል

የሴቶችን ሁለንተናዊ መብቶች ከማስከበር አኳያ ለባህል ወይም ለልማድ ትኩረት ሰጥቶ የሚንቀሳቀሰው የእንስታዊነት ንድፈ ሃሳብ ባህላዊ እንስታዊነት (cultural feminism) በመባል ይታወቃል። ይህ ንድፈ ሃሳብ የሴቶችን መብት ማስከበር የሚቻለው የማህበረሰቡ ባህል ወይም ልማድ ሲቀየር ብቻ እንደሆነ ያስረዳል። የማህበረሰቡን ባህል ወይም ልማድ መቀየር ያስፈለገበት ምክንያት ደግሞ ህብረተሰቡ ለሴቶች ያለው አመለካከት የተዛባ በመሆኑ ነው (ርዕዮት፣ 2004፡174)።

ይህንን እውነታ አስመልክተው (ዘሪሁን፣1988፡ 84) ላይ እንዲህ ባለ ሁኔታ ያስቀምጣሉ፡-

> በማንኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ ሴቶች በበታችነት መታየታቸው ተደጋግሞ የሚነገር ዕውነት ነው። ወንዶች ጠንካራ፣ አዋቂ፣ አሳቢ፣ ጀግና ሲባሉ ሴቶች ደግሞ አላዋቂ የማያስቡና ፈሪ ይባላሉ። ሴቶች ጠንካራና ብርቱ ሆነው የተገኙ እንደሆነ ደግሞ "የወንዶች ሥራ" በመስራታቸው ወንዳወንድ ሴትነታቸውን የረሱ ተብለው ይወቀሳሉ። በተፈቀደላቸው ክብ ውስጥ ሆነው ክቡ የሰጣቸውን ስራ ብቻ እንዲሰሩ ይጠበቅባቸዋል።

በኦሮሞ ባህል ውስጥም የተጠቀሰውን አባባል እውነትነት የሚያስረግጡልን በርካታ የአኗኗር ዘይቤዎች/ባህሎች/ እና ከዚህም የሚቀዱ ምሳሌያዊ ንግግሮች አሉ።

"Dubartiin beektuu hin qabdu beekaa dessi malee" (የሴት አዋቂ የላትም፤ አዋቂ ትወልዳለች እንጂ)፣ "Dubartiifi ijoolleen gara golaa tolti" (ሴት እና ህፃናት በጓዳ ያምራሉ)፣ "Dugda dubartiifi dugda harree irraa nyaatu" (በሴት እና ከአህያ ጀርባ ይበላል)፣ "Harreen moonaa hin qabdu, moonaa loonii galti; dubartiin mana hin qabdu mana dhirsaa galti" (አህያ በረት የላትም፤ በከብቶች በረት ትገባለች፣ ሴት መኖሪያ የላትም በባሏ ቤት ትኖራለች)፣ ... እና የመሳሳሉት የሴቶችን ክብር የሚያዋርዱ ብዙ ስነቃሎች ተጠቃሽ ናቸው። ይህ ስር የሰደደ አስተሳሰብና አመለካከት እስካልተቀየረ ድረስ ለሴቶች የሚሰጠው ክብር ሊለወጥ አይችልም የሚሉት ባህላዊ እንስታዊያን በዚህ ሃሳብ ዙሪያ ጠንከር ያለ ስራ መሰራት እንዳለበት የሚያምኑ የቲዎሪ መሰረት ያላቸው ናቸው።

## 2.3.2. እንስታዊነት እና ሃይማኖት

የባህላዊ እንስታዊነት ፍልስፍና አራማጆች እንደሚያምኑት የሴቶችን መብት ለማስከበር መደረግ ያለበት ሌላው ጉዳይ ሴቶችን የሚያንኳስሱ ሃይማኖታዊ አስተሳሰቦች ላይ ያተኮረ አብዮት ማካሄድ ነው ይላሉ። ይህም አካሄድ የሃይማኖት መፃህፍት ስለሴቶች ያላቸውን አስተምሮት ማጥናትና አሉታዊ ሆነው የተገኙትን ማስወገድንም ያጠቃልላል ይላሉ።

ርዕዮት ዓለሙ (2004) Mahjubah መጽሔት በ2002 ዓ.ም የየካቲት ወር ዕትሙ "The educative role of women in Islam" የሚለውን በመጥቀስ እንዳስቀመጠችው፡-

በመፅሐፍ ቅዱስ እና በቁርአን ውስጥ የሚታወቁ ሴቶችን ስንመለከታቸው

"Abrham's Wife, mother of John, paraoh's wife, Job's wife, mother of Moses, etc (ገፅ:184) ይላል።

ይህ አቀማመጥ ግን ለእንስታዊያኑ የሚዋጥ አልሆነላቸውም። ሴቶችን ጥገኛ የሚያደርግ አይነት ነው በማለት ክፉኛ ይቃወሙታል። ምክንያቱም ሴቶች በሙሉ ሲጠቀሱ በራሳቸው ስም "እገሊት" ተብለው ሳይሆን "የእገሌ ሚስት፣ የእገሌ እናት፣ ..." እየተባለ በወንድ ልጃቸው አለያም በባላቸው ስም መጠራታቸው ለሴቶቹ ሳይሆን ለወንዶቹ ዕውቅና የሚሰጥ አቀራረብ መሆኑን በመጥቀስ ይከራከራሉ።

## 2.4. ሴት ገፀባህሪያት በኪነጥበብ ስራዎች ውስጥ የሚሰጣቸው ውክልና

ለሴቶች መብት መከበር ከእነስታዊያን ሃሳብ ሌላ የኪነጥበብ ሚና ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። ኪነጥበብ ነገሮችን የመገንባትም ሆነ የማፍረስ ጉልበት አለው፣ እንደሁም የአንድን ማህበረሰብ አስተሳሰብ፣ የአኗኗር ዘይቤ የመቆጣጠር ሃይል እንዳለው በብዙ ምሁራን አንደበት ተመስክሮለታል። በእነዚህ ሥራዎች ውስጥ ያሉ የሴት ገፀባህሪያት አሳሳሎች ደግሞ ብዙን ጊዜ አሉታዊና ተደጋጋሚ ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚህ ደግሞ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው አንዱ የኪነጥበብ ባለሙያዎች አብዛኞቹ ወንዶች መሆናቸው ነው። በርካታ ወንድ  የኪነጥበብ ባለሙያዎች ሴት ገፀባህሪያት የደካማነት ገፅታን አላብሰው እንደሚቀርፁ ይታወቃል። ወይም ደግሞ ዝቅተኛ ቦታ የሚሰጠውን ነገር ወክለው እንድ ከውኑ ያደርጋሉ። ባለሙያዎቹ እንዲህ ያለ አሳሳል እንዲጠቀሙ ወይም ለእንደዚህ አይነት ውክልና ሴቶችን እንዲጠቀሙ ከሚያስገድዳቸው ነገሮች መካከል በገሃዱ ዓለም ያለው የሴቶች አኗኗር እንደሆነ ይነገራል። ኪነጥበብ የገሃዱ ኣለም ነፀብራቅ እንደመሆኑ መጠን የሃገራችን ብሎም የአፍሪካ ሴቶች ደግሞ አሁንም የወንዶች ጥገኛ ሆነው የሚኖሩበት ሁኔታ በብዛት ስለምንፀባረቅ የኪነጥበብ ባለሙያዎች እህንኑ የገሃዱን ዓለም እውነታ ለማፀባረቅ ሲሉም ጭምር እንደሚቀርፃቸው እሙን ነው። ያም ሆነ ይህ ሴቶች በኪነጥበብ ውስጥ የኮሳሳነት ገፅታ ተላብሰው፣ ዝቅተኛ ቦታ የሚሰጣቸውን ነገሮች ወክለው መቅረባቸው የማንክደው ሀቅ ነው። (Albrecht, 1956) በመጥቀስ Frank, Linda እንደሚለው፤

If literature directly reflects society, its cultural norms and values, then the fiction produced by society should reinforce those attitudes and ideals (Frank, 1985:24).

ከዚህ በመነሳት እንደዚህ አይነት ኪነጥበብ ስራዎችን የሚያየው፣ የሚያዳምጠው ወይም የሚያነበው ሰው በሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀርም። ሴቶችም ቢሆኑ በኪነጥበብ ውስጥ ያስተዋሉትን ገፀባህሪያት አመል፣ አመለካከት፣ ፀባይ በአጠቃላይ የእነርሱን ማንነት ለመልበስ መዘጋጀታቸው አይቀርም። ምክንያቱም የሚያዩት፣ የሚያነቡት እና የሚሰሙት ነገሮች  የሴቶችን የቤታችንነት የሚሰብኩ ከሆነ ይህ ነገር ለሴቶች የተደነገገ ነገር ነው ብሎ ራሳቸውን ለዚህ ነገር ሊያዘጋጅ ይችላሉ። ወንዶችም ቢሆኑ ለእነርሱ ሴት ማለት በኪነጥበብ ውስጥ የተሳሉት አይነት በመሆናቸው ለሴቶች  ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ይሆናል። ርዕዮት አንደምትለው ከሆነ በሴት ደራሲያን ዘንድ አልፎ አልፎ የሚስተዋሉ የሴት

ገፀባህሪያት "በጎ አሳሳልም" ቢሆን ኢ-ተአማኒ በመሆኑ የሚያስከትለው ችግር አለ። በአጠቃላይ አሉታዊ፣ ተደጋጋሚና ኢ-ተአማኒ የሆኑ የሴት ገፀባህሪያት በኪነጥበብ ሥራዎች ውስጥ በብዙ መልኩ በሴቶችና በህብረተሰቡም ዘንድ ጉዳት ማስከተሉ አይቀርም። የእንስታዊያን ፍልስፍና ባለሙያዎችንም ያነጋገረው ጉዳይም ሆነዋል። ምክንያቱም ሴቶች በገሃዱ ዓለም የሌላቸውን ሰብእና በኪነጥበብ ውስጥ ማምጣቱ ስላቅን ሊያስከትል ይችላል ባይ ናቸው። እንዲሁም ሴቶች በገሃዱ ዓለም የሚኖሩትን ኑሮ በኪነጥበብ ውስጥ ማንፀባረቁም ደግሞ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ስለዚህ የእንስታዊነት ፍልስፍና ተከታይ የሆኑ ሃያስያን (Feminist Critics) የተጠቀሱትን ችግሮች ለማስወገድ የዘየዱ ዘደዎች አሉ።

ከነዚህም ውስጥ ሴት ገፀባህሪያት በኪነጥበብ ስራዎች ውስጥ እንዴት እንደተሳሉ በመመልከት (observing and analyzing) አሉታዊ ሆነው የተገኙትን በተለያዩ መንገዶች መቃወምና አዎንታዊ የሆኑትን ደግሞ ማበረታታት የሚሉ ጉዳዮች ይገኙበታል።

Miller (1990:23) በመጥቀስ Peter, Zola እንደሚለው፤

"In African literature as a whole woman hardly have a mouth yet; having a voice is the rhetorical tool of unity, homogenization and their empowerment" (2010:150).

ይሄን ጉዳይ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው እንስታዊያኑ ለሴቶች መብት መከበር በየትኛውም መስክ እየተንቀሳቀሱ የሚገኙት።

Mary, Anne Ferguson; Images of Women in Literature, በሚለው መፅሐፏ ስለሴት ገፀባህሪያት አሳሳል ማብራሪያ ስትሰጥ፣ ሴቶች በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ምንም አይነት የጎላ ቦታ የማይሰጣቸው፣ በፖለቲካና በንግድ እንቅስቃሴ የጎላ ድርሻ የሌላቸው፣ ቁሳዊ የሆኑ ነገሮች የሚማርኳቸው ደካሞች፣ ትንንሾችና ተደጋጋሚ የሆነ ሥራ መስራት የማይሰለቹ ተደርገው በድርሰት ውስጥ እንደሚቀርቡ በመፅሐፏ የመጀመሪያ ክፍል ገልፃለች። ሴቶች በስነ ፅሑፍ ውስጥ ምን አይነት ቦታ እንደተሠጣቸው ለመመልከት ሴቶች በነባራዊው አለም ምን እንደሚመስሉ ማጤን አለብን። ምክንያቱም ስነፅሁፍ የነባራዊው ዓለም ነፀብራቅና እውነታ ለማሳየት የምንጠቀምበት መሳሪያችን በመሆኑ ነው የምትለው ፌርጉሴን በድርሰት ውስጥ የሚሳሉትን ሚስት ገፀባህሪያትን የተመለከትን እንደሆነ ለልጆቻቸው ብቻ ሳይሆን

ለባሎቻቸውም ጭምር እንክብካቤ የሚያደርጉ፣ ምግብ የሚያዘጋጁና በባህሪያቸውም ነዝናዛዎች ተደርገው ይሳላሉ ብላለች።

በአብዛኛው ማህበረሰብ ውስጥ የሴት ልጅ አስፈላጊነቷ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈፀምና ልጅ ለመውለድ ተደርጎ ይታሰባል። በመሆኑም ለወንዶች ስሜት መወጫ ዕቃ ተደርጋ ትታያለች። በአጠቃላይ ሴቶች በስነፅሁፍ ውስጥ እንደ ሚስት፣ እናት፣ ያላገቡ፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀሚያ ተደርገው ተስለዋል ትላለች (Ferguson, 1977፡ 12-13)::

ከዚህ በመነሳት ስነፅሁፍ የሴቶችን ማንነት እና ምንነት እንዲሁም የመረዳት አቅማቸውን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ቦታ ስለሚሰጠው ተጠንቅቆ ቢሰራ የሚያመጣው ለውጥ ይህ የማይባል እንደሆነ ይገመታል።

# ምዕራፍ ሦስት፡ የመረጃ ትንተና

## መግቢያ

### የልቦለዶቹ ትውውቅ

ሀ. Hawwii-(ሀዊ)

የኃይለ ሥላሴን ዘመነ መንግስት ለማሳየት የተነሳው ይህ ረጅም ልቦለድ ከነቀምቴ ከተማ በ1950ዎቹ ጀምሮ እስከ አውሮፓ ከዚያም መልስ የታሪኩ ጡዘት አዲስ አበባ ላይ በ1960ዎቹ ጣሪያ ረግጦ ይረግባል።

በታሪኩ ውስጥ የ1960ዎቹን የተማሪ ትውልድ አስተሳሰብን የሚያመለክተው የድርሰቱ መልዕክት በወኪል ገፀባህሪያቱ አማካኝነት የወቅቱን ምሁር የራስ እይታ (አመለካከት) "የእኔነት" ስሜት ይዳስሳል። "እኔ ቀብራራው ጎንደሬ" (ገፅ፣ 165) ከሚለው ኢንጅነር አማረ ጀምሮ አዲስ አበባ ውስጥ ከፍተኛ ትምህርት ተምሮ የባንክ ሰራተኛ የሆነው ወጣት ስሙን ከ "ለሙ በንቲ" ወደ "አለሙ ባንቴ" በመቀየሩ ሲሞት እንኳ አባቱ ውርስ አልባ እስከሆነው የተማሪው የወቅቱ የኦሮሞ ልጅ ድረስ የሚያትት ሆኖ የወቅቱን የብሔር ስሜትና መንስኤውን ያመላከተ ድርሰት ነው።

ይሁን እንጂ የሀዊ ልቦለድ ወደ ተደራሲው የደረሰው ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን ደራሲው ከሬዲዮ ስርጭት ሥራው ጋር አያይዘው ለሦስት ተከታታይ ወራት በእሁድ ማለዳ ኦሮምኛ ፕሮግራም ላይ "Wajjin duuna" (አብረን እናልፋለን) በሚል ርዕስ በድራማ መልክ አቅርቧል። በ1985 ዓ.ም ደግሞ በልቦለድ መልክ አሳትሟል።

ለ. Yeroon Siif Haadhiistu- (የሮን ይቅር ትበለህ)

የዚህ ልቦለድ ታሪክ ከጅማ ከተማ ይጀምርና አዲስ አበባ ውስጥ መቋጫውን ያገኛል። የሮን እና ሰለሞንን በዋና ገፀባህሪነት ይዞ የተነሳው ይህ ድርሰት በእየሱስ ክርስቶስ ካመናችሁ ሁሉም ነገር ይሆንላችዋል የሚል መልዕክት ይዞ የተነሳ ቢሆንም በውስጡ ትልቅ ቁምነገር የያዙ ንኡሳን ጭብጦች አሉት።

ሰለሞን በአጋሮ ከተማ ውስጥ ታዋቂ የእግር ኳስ ተጫዋች ነበር። ካለው መጥፎ ፀባይ የተነሳ ከአባቱ ጋር መስማማት ስላልቻለ ወደ ጅማ ከተማ በመሄድ ከአንድት በእድሜ የገፋች ሀብታም አሮጊት ጋር አብሮ እየኖረ የምታምር፣ ጥሩ ፀባይ ያላት፣ በትምህርቷም ጎበዝ ከሆነችው የሮን

ጋር ይተዋወቃል። ከእርሷ ጋር በመተዋወቁም ከፍተኛዋ ባለቤቱ ጋር ይጣላል። ከዚያም የሮንን አግብቶ ሁለት ልጆች ይወልዳሉ።

የየሮን ቤተሠቦች በጣም ሃብታም ስለነበሩ ነገር ግን ወንድ ልጅ ሲለሌላች ንብረታቸውን በሙሉ ሰለሞን እንዲያስተዳድር ያደርጋሉ። ያ መጥፎ ፀባይ ሰለሞንን ስላልለቀቀው ከየሮን ጋር እያለ ቆንጂት ከምትባል ልጅ ጋር ይተዋወቃል። የቤተሠቧን ንብረትም ቀስ በቀስ በቆንጂት እጅ ያስገባል። እነ የሮንም ባዶ እጃቸውን ይቀራሉ። በመጨረሻም ሁለቱን ልጆች እሷ ላይ ትቶ ቆንጂትን ያገባል። ከዚህም የተነሳ የሮን በማትፈልገው ሥራ ላይ በመሰማራት ልጆቿን ለማሳደግ ትገደዳለች

ባርኬሳ የሚባል ሰው ከየሮን ልጆች ጋር ይተዋወቅና ወደ እግዚአብሔር ቤት ሄደው በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል። እነርሱም ሄደው በማመን ህይወታቸው ሲቀየር እንመለከታለን። የሮን በፊት ያቋረጠችውን ትምህርቷን በመቀጠል ዶ/ር ለመሆን በቅታለች። አንደኛው ልጇም ትምህርቱን ጨርሶ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ይሆናል። አንዱ ደግሞ አሜሪካን ሀገር ሂዶ የህክምና ትምህርት በመማር ዶክተር ይሆናል።

የሰለሞን እና የቆንጂት ኑሮ ግን ወደ ሃዘን ይለወጣል። በመጨረሻም ሰለሞን በሞት ቆንጂት ደግሞ በአካል ጉዳት ምክንያት የአልጋ ቁራኛ ትሆናለች። የእነ የሮን ንብረትም ይመለስላቸዋል። ደስተኛ ህይወትም እየኖሩ ታሪኩ ይቋጫል።

ሐ. Yoomi Laataa? (መቼ ይሆን?)

ጊዜው በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ውስጥ ነው። ሲንቶሊናና ያደኖ ጃራ በሀረር ክፍለ ሀገር ሐራዌ በምትባል ስፍራ ተጋብተው የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ። ተጋብተው በአመታቸው አንድ ወንድ ልጅ "ሰንዳባ" የሚባል አፍርተዋል። የክፍለ ሀገሩ ገዥ የነበሩት ቀኝ አዝማች ግዛቸው ከሲንቶሊና ጋር ግንኙነት ይጀምራሉ። በኋላ ያደኖ እንዳጋጣሚ አንድ ላይ ያገኛቸውና ቀኝ አዝማችን በመግደል ከሀገር ሲወጣ ሲንቶሊና ደግሞ ቀኝ አዝማች እቤታቸው ውስጥ በመሞቱ ሀረር ከተማ ውስጥ መኖር እንደማትችል በመገንዘብ ልጇን አዝላ ለመጥፋት ከቤት ትወጣለች። የልቦለዱ ታሪክ ከዚህ ይጀምራል።

ሲንቶሊና በጠፋች እለት ራስ ጌታውንና ሹፌራቸው የነበረ ዋሪዮ በመንገድ ዳር አግኝተዋት ወስደው አዲስ አበባ ይገባሉ። ራስ ጌታውን የኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ባለስልጣን ሲሆኑ ከባለቤታቸው ንግስት ሊዲያ ልጅ ማግኘት ስላልቻሉ የሲንቶሊናን ልጅ እንደ ልጃቸው ለማሳደግ ሲንቶሊናን ደግሞ በቤት ሠራተኝነት እንድታገለግል አደረጉ። በዚህን ጊዜ የንግስት

ሊዲያ እህት  የነበረችው ቤቲ በዩኒቨርሲቲ ወስጥ ከተዋወቀችው ፍቅረኛዋ ገዳ በማርገዟ ፍቅርን ትወልዳለች። እራሷ ደግሞ በወሊድ ላይ ህይወቷ ያልፋል።

ንግስት ሊዲያ ፍቅርን ተቀብለው ከሰንዳባ ጋር አሳደጉ። ፍቅርም እድሜዋ እየጨመረ በመጣ ቁጥር ሰንዳባ ፍቅር እየባሰባት ይመጣል። በኋላ ሳያስቡበት ፍቅር ከሰንዳባ አርግዛ ሁለት መንቲያ ልጆች ትወልዳለች። በዚህን ጊዜ ንግስት ሊዲያ ከራስ ጌታውን ጋር ለህክምና ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ ስለነበር ወደ  ሀገር ሲመለሱ እነዚህ ልጆች የሲንቶሊና እና የዋሪዮ እንደሆኑ ነገሩዋቸው።

በዚህ  እየኖሩ እያለ የኃይለ ሥላሴ መንግስት ወድቆ ደርግ ስልጣን ያዜ።  የደርግ ባለስልጣናት በፈጠሩት ጫና ራስ ጌታውን  ራሳቸውን ሲገድሉ ንግስት ሊዲያ ደግሞ ታስረው በእስር ቤት ውስጥ በህመም ምክንያት ይሞታሉ። ፍቅርም የራስ ጌታውንን ንብረት  በሙሉ ለሠራተኞቻቸው አከፋፈለች። ፍቅር በቀይ ሽብር ዘመቻ ስለ ተቸገረች ባለቤቷና ልጆቿ በፊት በወለጋ ክፍለ ሃገር ነቀምቴ  ከተማ ስለነበሩ እነርሱ ጋር በመሄድ እዛ ትምህርቷን ቀጠለች። በአዲስ አበባ ውስጥ የነበረው ሁኔታ ስላሰፈራቸው ዋሪዮ እና ሲንቶሊናም ወደ ሀረር ተመለሱ። ሰንዳባ ደግሞ ቤተሠቦቹን ጥሎ ለትግል ሀገር ለቆ ይወጣል።

ፍቅር ከልጆቿ ጋር እያለች ለደርግ  ያላት አመለካከት ስለታወቀባት ፈርታ ከነልጆቿ ወደ አዲስ አበባ  ተመለሰች። ከዛም ልጆቿን ይዛ ወደ  ሀረር በመሄድ ከዋሪዮ እና ሲንቶሊና ጋር ተገናኝታለች። ትምህርቷንም በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ቀጥላለች። ከጊዜ በኃላ ደግሞ  የፒኤች ዲ እድል በማግኘት ወደ አውስትራሊያ ቴጉዛለች።

ሲንቶሊና በደርግ ባለስልጣናት በመጠርጠሯ ምክንያት ታሰራ ከእስር እንደወጣች ተመልሳ አዲስ አበባ ገብታለች። በ1983 ዓ.ም የኦሮሞ ህዝባዊ ዴሞክራሳዊ  ድርጅት (ኦህዴድ) ደርግን ለመጣል ተሳትፎ ሲያደርጉ ለነበሩት አካላት በሙሉ በውጭም  ላሉ ጭምር ወደ ሀገር እንዲገቡ አዋጅ  ስላወጣ ሰንዳባ ወደ ሀገር ተመለሰ።

ሰንዳባ ሳብን ወደ አስመራ  ለመሸኘት የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ሲሄድ ዋሪዮ እና ሲንቶሊና ደግሞ ፍቅር ከአውስትራሊያ ስለምትመለስ ለመቀበል ቦሌ ሄዳ ሁላቸውም እዚያ በመገናኘት ታሪኩ ይቋጫል።

## 3. በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ግላዊ መረዳት (Self Perception of Major Female Characters in Isayas Hordafa's Novel)

### 3.1. የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያቱ አጠቃላይ ስብእና

በዚህ ምዕራፍ ስር የአንድን ዋና ገፀባህሪ አጠቃላይ ስብእና ከመመልከታችን በፊት ዋና ዋና ገፀባህሪ ስንል በራሱ አንድን ገፀባህሪ ዋና ሊያሰኝ የሚያስችል መስፈርት ምንድን ነው? ካልን ሐርቬይ "Characters and the Novel" በሚለው መፅሐፋቸው፡-

> *...those Characters whose motivation and history are mostfully established, who conflict and change as the story progresses, who engage our responses morefully and steadily;.. they are the vehicles by which all the most interesting questions are raised; they are what the novel exists for, it exists to reveal them (Harvey, 1965:56).*

በማለት አንድን ገፀባህሪ ዋና ሊያሰኝ የሚያስችለውን መስፈርት ይጠቁማል። ከዚህ በመነሳት በሶስቱም የኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ የተመረጡትን ዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት አጠቃላይ ስብእናቸው ምን እንደሚመስል እንመለከታለን። በዋናነት ገፀባህሪያቱ ለህይወትና በአጠቃላይ ለአለም ባላቸው አመለካከት፣ የትምህርት ደረጃቸውንና ለፍቅር ያላቸው ግምት እንዲሁም አብሮአቸው ለተሳሉት ሌሎች ገፀባህሪያት ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል እንመለከታለን።

የገፀባህሪያቱ አጠቃላይ ስብእና ሲባል ውጫዊና ውስጣዊ ማንነታቸውን የሚመለከት ሲሆን የአንድ ግለሰብ የግል መታወቂያ የሆኑት አካላዊና አዕምሮአዊ ባህሪይ፣ አመለካከት፣ ዝንባሌ፣ አቋም፣ ድርጊት፣ ወዘተ. በሌሎች ሰዎች አይን በግልፅ ሊታይ የሚችሉና የማይችሉትን በተለይ ግላዊ አቋም፣ ጥልቅ ስሜት፣ የቀለም ምርጫ፣ አካላዊ ገፅታ፣ የመሳሰሉ ጉዳዮች የአንድን ሰው አጠቃላይ ስብእናውን የሚያመላክቱ ነገሮች ናቸው። ስለዚህ አጠቃላይ ስብእና ስንል ውስጣዊና ውጫዊ ማንነታቸውን ጠቅልሎ የያዘ ማለታችን ነው።

የአንድን ገፀባህሪ ማንነት፣ አመለካከት እንዲሁም ለነገሮች ያለውን ግላዊ መረዳቱን የማወቂያ ሌላው ዘዴ ደግሞ ገፀባህሪያቱ ከሚያደርጉት ድርጊት እና ከሚናገሩት ነገር ተነስተን ማንነታቸውን፣ ሃሳባቸውንና አመለካከታቸውን መረዳት እንችላለን። ይህን ሃሳብ አስመልክቶ ስንታንፎርድ ጅድገዝ "Responding to literature" በሚለው መፅሐፋቸው፡-

*Observing, hearing what characters say leads to insights in to who they are; what they believe, what they fear, what they hope for and how they think about them selves and others (1992:34).*

በማለት ሲያስቀምጥ በመቀጠልም ገፀባህሪያት የገሃዱን አለም ሰዎች መስለው ባማረና በተዋበ ቋንቋ በሚቀረፁበት ጊዜ የራሳቸው የሆነ እምነት፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብ አላቸው ይላል። ይህንም በልቦለዱ ውስጥ በሚፈፅሙት ድርጊት፣ በሚናገሩት ንግግር እንዲሁም ከሌሎች ገፀባህሪያት ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት እና ሌሎች ገፀባህሪያት ስለነርሱ በሚያወሩት እናውቃቸዋለን ይላል።

በአጠቃላይ ገፀባህሪያት በዚህ ዓለም የሚኖሩትን ሰዎች ወክለው ውጫዊና ውስጣዊ ስብእናን በደራሲው ምናብ ተላብሰው የሚቀርቡ ሰዎች መሆናቸውን ያብራራል።

ከዚህ በመነሳት በደራሲው የመጀመሪያ ረጅም ልቦለድ ውስጥ Hawwii (1985 ዓ.ም.) የሀዊን፣ በሁለተኛ Yeroon Siif Haadhiistu (2000 ዓ.ም.) የየሮን ስብእና እንዲሁም በመጨረሻ Yoomi Laataa? (2003 ዓ.ም.) የሲንቶሊናን አጠቃላይ ስብእና በቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው ቀርቧል።

3.1.1. Hawwii -ሀዊ

በኢሳያስ ሆርዶፋ "Hawwii" በተሰኘው ረጅም ልቦለድ ውስጥ በዋና ገፀባህሪነት የተሳለችው እራሷ ሀዊ ናት። ሀዊ ከአባቷ አቶ ቡልቻ እና ከእናቷ ወ/ሮ ድንስሪ በምሥራቅ ወለጋ ነቀምቴ ከተማ በ1945 ዓ.ም. ተወለደች። በአስከፊ ድህነት ውስጥ የሚኖሩት ቤተሠቦቿ ልጅ ከማጣታቸው የተነሳ የተለያዩ ሃሳቦችን ሲሰነዝሩ ከቆዩ በኋላ በስተርጅናቸው አንዲት ውብ ሴት ልጅ በማግኘታቸው ሀዊ-ምኞት/ ተስፋ ብለው ሰየሟት። ገና እንደተወለደች ውበቷን አይታ፣ "ልጄ ካደገች ለሃብታም ድሬ ከዚህ አስከፊ ኑሮዬ እላቀቃለሁ" በማለት የሚናገሩት እናቷ ሀዊም ሲታድግ ቀይና የተስተካከለ አቋም ያላት መልከ መልካም ልጅ ሆና ተገኘች።

*Hawwiin hojjaan ishee akka dheerachuu ta'ee dhaabbata gaarii qabdi. Latiinis diimaa dheeraa miidhagaadha. Walumaa galatti lamaanuu qajeelinni funyaan isaanii, iji, haphinni hidhii, kuullinyaara isaanii haadhoo garaa tokko bahan isaan fakkeessa (Fuula:30).*

ሀዊ ቁመቷ ወደ ረጅምነት ያደላ ሆኖ የተስተካከለ ቁመና ያላት ናት። ለቲም ረዘም ያለ ቀይ የሚያምር ልጅ ነው። በአጠቃላይ የአፍንጫቸው ሰልካካነት፣

አይናቸው፣ የከንፈራቸው ስስነት፣ የቅንድባቸው ኩል ከአንድ ሆድ የወጡ ያስመስላቸዋል (ገፅ፡ 30)።

ለቲ ጅሬኛም እንደ ሀዊ ከደሃ ቤተሠብ የተወለደ አብሮ አደጓ ሲሆን መልካቸውን ልብ ብሎ ላስተዋለ ሰው ከአንድ እናትና አባት የተወለዱ ልጆች ይመስላሉ። ነገር ግን ከጉርብትና በስተቀር የደም ዝምድና እንኳ የላቸውም።

በአምስት አመቷ ከአብሮ አደጓ ለቲ ጋር ትምህርት የጀመረችው ሀዊ ከአብሮ አደጎቿና በእድሜ ከሚበልጧት ልጆች ቀድማ የበሰለች፣ ነገሮችን አመዛዝና የማየት ተሰጥኦ ያላት አስተዋይ ልጅ ሁና ተገኘች። ሀዊ በራሷ ላይ ከፍ ያለ እምነት ሲኖራት ላመነችበት ነገር ወደ ኋላ የማትል የውስጥ ስሜቷን የማትደብቅ በይሉኝታ መኖር የማይቀናት ግልፅ ልጅ ናት። ይህንን ባህሪዋን ደግሞ ገና በልጅነቷ ያፈቀረችውን አብሮ አደጓ ለቲ ጅሬኛን የራሷ ለማድረግ በምታደርገው ጥረትና ድርጊት እንዲሁም እስከመጨረሻ የእርሱ የመሆን ፍላጎቷን በግልፅ ስትገልፅለት እንመለከታለን።

> "...nagaa waaqayyoof yoo namni harka naqabe malee waan dhiirri qubaan naxuqu natti hinfakkaatu".. Latiinis deebisee "Yoo heerumte Abbaan manaakee hoo?" jedhe ammas itti kokkolfaa "Atis dabarsitee Ormatti nakennuu yaddaa? Jette( Fuula፡ 32-33).
>
> ለእግዚአብሔር ሰላምታ ሰው እጄን ካልነካ በስተቀር ወንድ በጣቱ የሚነካኝ አይመስለኝም... ለቲም መልሶ "ሲታገቢ ባልሽንስ? ብሎ መልሶ ሲስቅባት "አንተም አሳልፈህ ለሌላ ሰው ልትሰጠኝ ታስባለህ? አለችው (ገፅ 32-33)።

ሀዊ ይህን ሃሳብ የምትሰነዝረው 10ኛ ክፍል እያለች ስሆን ከዚህ ንትርክና ጭቅጭቅ የተነሳም በትምህርቷ እየቀነሰች መጥታለች።

ከዚህ ጊዜ ጀምራ ለቲን በተቻላት መጠን ለመቆጣጠር የምትጥር፣ የተሰማትን ነገር ደግሞ ጊዜ ሳትወስድ በግልፅ መናገር የሚቀናት ጠንካራ ልጅ ናት። የእናቷን ሃሳብ የሚያውቅ ለቲ የሀዊ ቤተሠቦች በድብቅ ልጃቸውን ለሃብታም ሰው ለመዳር መዘጋጀታቸውን ሰምቶ አቋሟ ምን እንደሚመስል በዘዴ ሲጠይቃት እንዲህ ትለዋለች።

> *"ilaa namni dhimma ofiisaa irratti ofii isaan hin murteessu taanaan garba! Gabrumma jala jiru; ykn horii qe'eeti jechuudha" jette (Fuula: 51).*

"ይኸውልህ ሰው በራሱ ጉዳይ ላይ እራሱ መወሰን ካልቻለ ባሪያ ነው! በባርነት ያለ ነው ወይም የቤት እንስሳ ነው ማለት ነው (ገፅ፡ 51)። በማለት በራሷ ላይ ያላትን ጠንካራ እምነት (አቋም) ትገልፅለታለች።

የሰው ልጅ በራሱ ነገር ላይ አስቦበት፣ አመዛዝኖ በራሱ ጊዜ መወሰን ካልቻለ ከባርነትም አልፎ ከእንስሳ ተርታ የሚቆጠር እንጂ የሰው ልጅ ልንለው አንችልም በማለት ቁርጥ ያለ ውሳኔ በመወሰን የግሏን አቋም ታንፀባርቃለች። የራሷን ፍላጎት ለማሳካት እና የፍቅረኛዋንም ሃሳብ ለመጠበቅ ስትል ለሃብትና ለዝና የማትጨነቀው ሀዊ የእናቷን ሃሳብ በቀጥታ ስትቃወም እንመለከታለን። እናቷ ገና ከመጀመሪያው ለራሳቸው በማሰብ አለ ለሚባለው የከተማው ሃብታም ለመዳር ሲዘጋጁ ሀዊ ገና ከለቲ እንደሰማች ያላትን  ስሜት ተራኪው እንዲህ ይገልፃል።

*Sagaleen haadha ishee akka sagalee bineensaa ishee sodaachise sagalee diinaa ta'ee itti dhaga'ame. Ishee jibbisiise haadha ishee itti fakkaachuu didde. "Gaggaba horiif yoona kana na gurgurachuuf qabdii hin fudhatiin haftii? budaan kun! Jireenya koo isagara fuula duraa najalaa balleesite" jettee gumgumte (Fuula: 54).*

የእናቷ ድምፅ እንደ አውሬ ድምፅ አስፈራት፤ የጠላት ድምፅ ሆኖ ተሰማት። አስጠላት፤ እናቷም አልመስል አለቻት። "ይህን ለገንዘብ ካላት ስግብግብነት የተነሳ እኔን ለመሸጥ ቀብድ ሳትቀበል ትቀራለች? ይህች ቡዳ! የወደፊት እድሌን አበላሸችብኝ።" ብላ አጉረመረመች (ገፅ፡ 54)።

የማህበረሰቡ ወግና ልማድ የማያግዳት፣ ይሉኝታ የማያጠቃት፣ ሐሳቧን እንደፈለገች የምትናገረው ሀዊ የቤተሠቦቿን አስተሳሰብ ንቃ ትምህርቷን አቋርጣ ከለቲ ጋር የወሰኑትን ነገር በመተግበር በድቅድቅ ጨለማ ለብቻዋ ከቤት ወጥታ የማታውቅ ልጅ ወደ አዲስ አበባ ኮበለለች። አወጣጧ የለቲ አጎት ልጅ የሆነው ደለሳ መርጋ ጋር ለመኖር ሲሆን እንደመጣችም እርሱን ማግኘት ባለመቻሏ ብዙ እንግልትና ስቃይ ያየች የተወለደችበትን ቀን እስከመርገም የደረሰች በጣም አስከፊ ህይወት ያሳለፈች ሲሆን ለፍቅረኛዋ በመታመን ንፅህናዋን እስከመጨረሻው የጠበቀች ጠንካራ ልጅ ናት። አንድም ቀን ማንነቷን ለጥቅም ያልደለለች፣ በችግሯ ጊዜ ፍቅረኛዋን የሚያስረሱ የተለያዩ ነገሮች ቢቀርቡላትም አንድም ቀን ያልተበገረች አስተዋይ ልጅ ናት።

ከቤተሠቦቿ ጠፍታ ወደ አዲስ አበባ ከመጣችበት ጊዜ አንስቶ በመንገድ ከተዋወቀችው አቶ አያና ጋር በመግባት ለአንድ አመት እቤቱ ስታሳልፍ የአቶ አያና ልጅ ጫላ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ ደህና ደመወዝ ያለው በራሱ መኪና የሚንቀሳቀስ መሀንዲስ ሲሆን ለጋብቻ ሲጠይቃት አቋሟን እንዲህ ስትል ትገልፅለታለች።

> "lakkii Latiin ana malee animmoo isa malee tokkoon keenya waldhabnee hin jiraannu." Jette (Fuula: 125).
>
> አይሆንም፤ ለቲ ከኔ በቀር እኔ ደግሞ ከርሱ በስተቀር አንዳችን አንዳችንን አጥተን መኖር አንችልም (ገፅ፡ 125)።

በማለት ለፍቅረኛዋ ምን ያህል ታማኝ እንደሆነች ቁርጥ ባለ አነጋገር ትገልፃለች። የጫላ እህት ሶኒ ለማሳመን ስትሞክር "waan hin yaadamnedha!" jettee murtiishee isa dhumaa ibsite" (Fuula:125). ከለቲ ሌላ ሰው የማይታሰብ መሆኑን ጠንከር ያለ አቋሟን ገለፀችለት።

እኔ ለእርሱ ያለኝ ፍቅር እርሱም ለኔ ያለው ፍቅር የሚያልቅ ወይም በብር የሚለወጥ አይደለም በማለት ድምጿን አሰምታለች።

የለቲ አጎት ልጅ ይሰራበታል የተባለውን የካዛንቺስ ባንክ ተመላልሳ ስትፈልገው በታክሲ ላይ አንድ ቀን ያጋጠማትን የቋንቋ ችግር እንዲህ ስትል ትናገራለች፡-

> *"Amma kan akka kanaatti kan kofaltan Amaariffa akka Amaaraatti dubbachuu dhabuu kootimitii? Isiniif afaan Abbaa keessaniiti. Utuu isin afaan Oromoo caccabsitanii dubbattan ta'ee ani isinitti hin kolfu. Garuu amma Amaariffa wallaaluun koo qaama namummaakoo keessaa hir'uu akkan qabutti nalakkaa'uun keessan of tuulummaa waaqa hin sodaannedha. Afaan Amaariffaa kan biyya keessaani dubbachuu dhabuun koo anaaf qaanii miti. Afaan alagaati hin komatamu. kan na'aarsu garuu doofummaa keessan miti, Finfinnee biyya abbaakoo keessa teessanii anaan nama biyya ormaa gootanii afaan natti haxaa'achuu keessanidha. Utuu beektanii miilla keenyarratti kuftanii nugalateeffachuu qabdu ture. Lafti isin gooftaa itti taatan kun hundi lafa keenyadha. Biyya keenyadha. Isaintu biyya keenya dhufe malee nuti biyya keessan hin dhufne. Maal godhu nu oromootatu tokkummaa dhabuu keenyatu akkas nu godhe Oromootu gamtaa cimaa dhabe malee isin hayyama*

*keenya malee lafa biyya keenyaarra ejjechuu hin dandeessan ture (Fuula:130).*

አሁን እንደዚህ የሚትስቁት አማርኛን እንደ አማራ ባለመናገሬ አይደለም? ለእናንቴ የአባታችሁ ቋንቋ ነው። እናንተ ኦሮምኛን እንደዚህ ሰባብራችሁ የምትናገሩ ቢሆን እኔ አልስቅባችሁም። ምክንያቱም የአባታችሁ ቋንቋ እንዳልሆነ ስለማውቅ ነው። ነገር ግን አሁን አማርኛን አለማወቄ ከሰውነቴ የሆነ ነገር እንደጎደለኝ (ጉድለት እንዳለኝ) መቁጠራችሁ እግዚአብሄርን የማይፈራ ትዕብት ነው። የእናንተን ሀገር ቋንቋ አማርኛን አለመቻሌ እኔን አያሳፍረኝም። የባዕድ ቋንቋ ስለሆነ አልወቀስበትም። የምያናድደኝ ግን ጅልነታችሁ አይደለም። የአባቴ ሀገር ፊንፊኔ ውስጥ ተቀምጣችሁ እኔን የሰው ሀገር ሰው አድርጋችሁኝ አፋችሁን ስትጠርጉብኝ ነው። ብታውቁ ኑሮ እግራችን ላይ ወድቃችሁ ታመሰግኑን ነበር። እናንተ ተከብራችሁ የምትኖሩበት መሬት ሁሉ የእኛ ናት። የእኛ ሃገርም ናት... ምን ያደርጋል አንድነት ማጣታችን ነው ለዚህ ሁሉ የዳረገን።.. የኦሮሞ ህዝብ የጠበቀ አንድነት በማጣቱ ነው እንጂ እናንተ ካለኛ ፍቃድ በእኛ መሬት ላይ መርገጥ አትችሉም ነበር (ገጽ፡130)።

በማለት ለማንነቷ ያላትን አቋም ግልፅ አውጥታ በታክሲ ውስጥ ስትናገር የሚያደምጧት ሁሉ ከዚህች ልጅ እንደዚህ አይነት ንግግር ስላልጠበቁ ሁሉም ሰው ዝም ብሎ አዳመጣት። አንድም ቃል የመለሰላት የለም። በጥቅምና በተለያዩ ነገሮች ተደልሎ ማንነቱን ሳይሸጥ የኦሮሞ ህዝብ አንድ ቢሆን ኖሮ ማንም ሰው እኛን ሊደፍረን አይችልም ነበር በማለት ለማንነቷ በግልፅ ትናገራለች። በእው ቀን ካዛንችስ ሄዳ የለቲን እኅት ልጅ አጥታ ወደ አቶ አያና ቤት ለመመለስ ታክሲ ይዛ አራት ኪሎ መውረድ የነበረባትን ተሳስታ ፒያሳ ወረደች። ከዚህ በኋላ ወዴት እንደምትሄድ አቅጣጫ ስለጠፋባት በመንገድ ዳር ብዙ ሰዓት ከቆመች በኋላ አንድ ወጣት መኪናውን አጠገቧ አቁሞ "ክላክስ" አደረገላት። ወዴት እንደምትሄድ ጠይቋት መኪናው ውስጥ ገባች።

*Fuula duraafis gaaridha wal barra Haayiluudha maqaan koo kan kee woo? Jedhe. "Hawwii" jetteen. Owu! Hawwii maal jechuudhaa afaan maaliiti? Jedhee gaafate. "Hawwiin maqaa Oromooti. Hiiki isaa afaan Amaaraatti "Minyot" jechuudha jette. Innis "owu! Yes! Yes! Gaallinyaa" jedhe. Tasuma, afaan Gaallaa*

*hin fakkaatu, it is beautiful name!" itti fufee" maqaa faranjii fakkkaata." Jedhe Hawwiin garaa isheetti "yaa Rabbi safuu! Maqaanis walcaalaa? Kan isaaniifi kan faranjii bareedaa kan Oromoo fokkisaa! Ajaa'ibadha. Kan Oromoo fokkisaadha jedhee kan itti murteesse waaqa moo isaanuma kana Laataa? Waaqayyo garuu walqixxee nu'uume yoomilaataa kan ilaalchi kun sammuu isaanii keessaa baduu? (Fuula:132-133). Jette*

"ለወደፊቱም ጥሩ ነው እንተዋወቅ፤ ኃይሉ እባላለሁ፤ አንቺስ?" አላት። "ሀዊ" አለች። "እ! ሀዊ ምን ማለት ነው? በምን ቋንቋ?" ብሎ ጠየቃት። "ሀዊም የኦሮሞ ስም ነው። ትርጉሙ በአማርኛ "ምኞት" ማለት ነው አለችው። "እሱም "እ! አዎ! አዎ! 'ጋልኛ'" አለ። "በጭራሽ የጋልኛ ቋንቋን አይመስልም፤ የሚያምር ስም ነው" አለ። ቀጥሎም "የፈረንጅ ስም ይመስላል" አለ። ሀዊም በልቧ "አቤት እግዚአብሄር ሆይ! ስምም ይበላለጣል? የእነርሱና የፈረንጅ ስሞች የሚያምር የኦሮሞ የሚያስጠላ! የሚገርም ነው። የኦሮሞ የሚያስጠላ ነው ብሎ የወሰነው እግዚአብሔር ነው ወይስ እነዚህ ራሳቸው? እግዚአብሄር ግን እኩል አድርጎ ነው የፈጠረን። መቼ ይሆን ይህ አስተሳብ ከአዕምሮአቸው ውስጥ የሚጠፋው?" አለች (ገፅ፡132-133)።

የተናገራት ኃይሉ እሷ የሚታነሳው ግን ስለማህበረሰቡ ነው። ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ እንደዚህ አይነት አስተሳሰብ መኖሩን አመላካች ነው። ምክንያቱም "መቼ ይሆን እንደዚህ አይነት አስተሳሰብ ከአእምሮአቸው የሚጠፋው?" ስትል አእምሮአቸው የኦሮሞን ማንነት በመናቅ እንደሰው ያለመቁጠር ሁኔታ በታሪኩ መቼት ውስጥ ኃይሉ በወከለው የአማራው ማህበረሰብ ዘንድ ስለሚንፀባረቅ ነው። እግዚያብሔር ግን እኩል አድርጎን ነው የፈጠረን። ማንን? እኛን ሁላችንን ማለትም አማራ፣ ኦሮሞ፣ ከንባታ፣ ሃድያ አላለንም ማለቷ ነው።

ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳያ የተፈጠረ፤ ማንም ማንንም የማይበልጥ መሆኑን ጠንቅቃ ታውቃለች። በሰዎች እኩልነት የምታምነው ሀዊ ከራሷ ምኞት አስቀድማ ለሌሎች የምታስብ እራሷን የማታስቀድም 'ሰው ከሚያዝንብኝ በእኔ ቢጎድል ይሻላል' የምትል ናት። ይኸንን በታሪኩ የተለያዩ ቦታዎች እናገኛለን። የአቶ አያና ባለቤት "ከሌላ ሴት የወለዳትን ልጅ አመጣብኝ" ብላ አምርራ ለራሷ ስትናገር ሀዊ "ይኸን የተሳሳተውን ሃሳቧን ከመቃወም እድሜ

ልካቸውን ያለምንም ችግር አብሮ የሚኖሩትን ቤተሠብ ከምበትን እኔ ብወጣ ይሻለኛል" በማለት ከቤታቸው ወጥታለች። በታሪኩ ሌላ ቦታ ይኸንን ሃሳቧን ደለሳ መረጋን አግኝታ አብረው እየኖሩ ሳለ ከሲውዲን ሃገር በኢንጂነሪንግ ተመሪቆ ከደሌሳ ጋር የሚኖረው የአማራ ብሔር ተወላጅ የሆነው አማረ ቤት ውስጥ ሊያባልጋት ሲጠይቃት እምቢ ብላው ከተሳደበች በኋላ አማረም ይኼ ጉዳይ ከደሌሳ ጆሮ ከደረሰ ይገለኛል ብሎ ሰግቶ ከቤት ሲወጣ እሷ ግን ድሮ አብሮ የሚኖሩ ጓደኛሞች በእኔ ምክንያት መጣላት የለባቸውም በማለት ምንም ሳትናገር ቀርታለች። ይህ ደግሞ ከራሷ ምቾት ይልቅ ለሰው ልጆች ምን ያህል እንደምትጠነቀቅ የሚያመላክት ነው።

በማንነቷ በጣም የምትኮራው ሀዊ ስለ ኦሮሞነቷ እንዲህ ስትል ትገልፃለች፡-

> *"Namni maaliif of tuffataa? Maaliif sabummaa (Oromummaa) isaatti qaana'aa? Balleessaa naamusaa nama qaanessu yoo hojjete qaana'a malee Oromummaan isaa eenyummaa isaati" (Fuula:149).*
>
> ሰው ለምን እራሱን ይንቃል? ለምን በኦሮሞነቱ ያፍራል? የሚያስነውር ስነ ምግባር ከፈፀመ ያሳፍራል እንጂ ኦሮሞነቱ ማንነቱ ነው (ገፅ 149)።

ይኸን ሃሳብ ያነሳችው በራሷ ብሔር፣ ቋንቋ በአጠቃላይ በማንነቷ ላይ ከፍ ያለ አቋም ስላላት ነው። የሰው ልጅ ማፈር ያለበት በሰራው አስነዋሪ ስራ ካልሆነ በቀር በማንነት አይታፈርም የምትለው ያለ ምክንያት አይደለም። በብሔረሰባቸው፣ በቋንቋቸውና በማንነታቸው አፍሮ ማንነታቸውን ቀይሮ የሌላቸውን ማንነት ለመላበስ የሚጣጣሩ የኦሮሞ ብሔር ወጣቶች ሲያጋጥሟት ነው ሀዊ የራሷን አቋም በዚህ ሁኔታ የምትገልፀው።

ደለሳ መርጋ እና የአማራን ብሔረሰብ ወክለው የቀረበው ኢንጂነር አማረ እንዲሁም አንዳንድ ቀን እየመጣች አማረን የምታነጋግረው እየሩሳሌም በደለሳ ቤት አንድ ቀን በመሃላቸው በተፈጠረው አለመግባባት ሀዊ ስታዳምጥ ከቆየች በኋላ የራሷን አስተሳሰብ እንዲህ በማለት ትሰነዝራለች፡-

*"Nigaha mee farsoo dhugaa. Dubbiin baay'ateef baay'ee namaaf gala miti. Yoo qulqullummaa dhugaan jiraate dhala namaaf jechi tokkollee ni gaha" jettee burcuqqoo farsoo duwwaa taa'utti farsoo guuttee teesse (Fuula:179).*

እስቲ ይብቃችሁ ጠላ ጠጡ። ነገር ሲበዛ አይደለም ለሰው ልጅ የሚገባው፤ እውነተኛ የውስጥ ንፅህና ካለ ለሰው ልጅ አንድ ቃልም በቂ ነው። ብላ ባዶ ብርጭቆ ላይ ጠላ ቀድታ ተቀመጠች (ገፅ፡179)።

ይህን ሃሳብ እንድትናገር ያስገደዳት እየሩሳሌም ባነሳችው ሃሳብ ላይ ደለሳ ተናዶ ብዙ የፖለቲካ ጉዳዮችን ስላነሳ እነርሱን ለማረጋጋት እንዲሁም በፖለቲካ ጉዳይ ላይ የራሷን አቋም መግለጿም ጭምር ነው። ሀዊ በፖለቲካውም ጭምር የሰው ልጅ ተከባብሮ፣ ተደማምጦ ቢኖር መልካም ነው የሚል አቋም አላት'። የሰው ልጅ ሰው ከሆነ እንደሰው ማሰብ አለበት የምትለው ሀዊ እቤት ውስጥ ከተሰበሰቡ ሰዎች የተሻለ ሃሳብ ያነሳች ልጅ ናት። ደለሳ መርጋ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቆ የባንክ ሰራተኛ ነው። ነገር ግን በፖለቲካ ጉዳይ ግልፍተኛ ነው። ቶሎ ይናደዳል ለአማረ በተቀዳለት ጠላ ውስጥ የገባው ዝንብ ትልቅ መሆኑን አይታ እየሩሳሌም ማለትም የአማረ ፍቅረኛ "ይሄኛውስ  የጋላ ዝንብ ነው" ስትል ነበር ደለሳ ከመጠን ያለፈ ንዴት የተናደደው። "ዝም በይ! ለእኛ ትልቅ ዝንብ ማነው የሰጠን? ኦሮሞ ዝንብ ያረባል አሉሽ ወይስ ኦሮሞ ከዝንብ ጋር ዝምድና አለው አሉሽ?  የእናንተ ዝንብ ምን ይመስላል? እናንተ እስከመቼ ነው እንደዚህ አይነት የደከመ አስተሳሰብ ይዛችሁ አብረን የምንኖረው" (ገጽ፣ 175)። ብሎ ሲናገር ሀዊ ግን እንደ ባለ አእምሮ ሰው ስትናገር እንሰማታለን። የሰው ልጅ ከገባው አስሬ መናገር አያስፈልግም አንድ ቃልም በቂ ነው። ካልገባ ደግሞ ስለማይገባው መናደዱ ተገቢ አይደለም ባይ ናት። እንደዚህ ስትል የእኛ ስም 'ጋላ' አይደለም እኛ ስም አለን ብላ ስለተናገረች እነርሱ ደግሞ ይሄ ነገር ስላልተዋጠላቸው ሀዊ መተውን መረጠች። ምክንያቱም ሆነ ብለው ቃሉን እንደሚጠቀሙና ለንቀት ስለተነሱ እንጂ ጠፍቷቸው እንዳልሆነ ቀድማ የተረዳች ትመስላለች። ለዚያም ነው "መናደዱ ለውጥ አያመጣም" የምትለው። ይህ አስተሳሰቧ ደግሞ ከምንም በላይ አስተዋይ ሊያሰኛት ይችላል።

ሀዊ በጋብቻ ምክንያት ከቤት ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ አማረ በሸረበው ሴራ ምክንያት መርዝ ጠጥታ ሆስፒታል እስከገባችበት ጊዜ ድረስ ምንም አይነት የመንፈስም ሆነ የአዕምሮ እረፍት ያላየች፤ ነገ ያልፍልኛ በማለት ብቻ ለማንነቷና ለምንነቷ ተጠንቅቃ የኖረች አስተዋይ ልጅ ናት። ሐሳቧን በትክክል ፊት ለፊት የምትገልፀው ሀዊ ከመሰሎቿ ቀድማ የበሰለች

የሚያዋጣትን ነገር ከቁብ አስገብታ መመርመር የምትችል፣ የትናንት ማንነቷንና ነገ ምን ሊሆን እንደሚችል ቀድማ በመወሰን በአዕምሮዋ የምትመራ ጠንካራ ልጃገረድ ናት።

### 3.1.2. Yeroon -የሮን

በኢሳያስ ሆርዶፋ Yeroon Siif Haadhiistu "የሮን ይቅር ትበልህ" በተሰኘው ሁለተኛ ረጅም ልቦለድ ውስጥ በዋና ገፀባህሪነት የተሳለችው የሮን የጠይም ቆንጆ ናት። በጅማ ከተማ አሉ ከሚባሉት የሐብታም ቤተሠብ የተወለደችው የሮን የ11 ኛ ክፍል ተማሪ ናት። እናትና አባቷ ከእርሷ በስተቀር ሌላ ልጅ የላቸውም። በቅንጦት ያደገችው የሮን "በሚያዝያ 27" ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚማሩት ተማሪዎች በጣም የምትለይ ልጅ ናት። ልዩ ከሚያደርጓት ነገሮች ውስጥ የምታደርጋቸው ጫማ፣ ልብሶቿ፣ የእጅ ሰዓቷ፣ የአንገት ወርቋ፣ ወዘተ. ከውበቷ ጋር ተደማምሮ ልዩ ያደርጋታል።

> *Yeroon magaala diimtudha. Ijishee inni habaaboo fakkaatu yommuu laalan nama marara. Ofitti nama hawwata. Funyaanshee utuu baay'ee ol hin ka'iin Mahaandisaan safaramee kan dhaabame fakkaata, hidhiinshee lamaan haphii ilkaanshee aannan fakkaatanii akka toora boqqollootti sirnaan kan biqilanidha. Walumaa galatti yeroo kofaltu habaabo amma reefu dhoye fakkaatee baay'ee nama mararti (Fuula: 8).*
>
> የሮን ጠይም ናት። አበባ የምመስለው አይኖቿ ሲያዩት ያምራል። የሰውን ቀልብ ይስባል። አፍንጫዋ በጣምም ሳይወጣ በመሃንዲስ ተሰፍሮ የቆመ ይመስላል። ከንፈሮቿ ስስ ሆነው ጥርሶቿ ደግሞ ወተት መስለው እንደ በቆሎ እሸት በመስመር ተደርድረው የበቀሉ ናቸው። በአጠቃላይ ስትስቅ ገና የፈነዳ አበባ መስላ በጣም ታማልላለች (ገፅ፡8)።

ውጫዊ ማንነቷን ስንመለከት ውብ እና መልከ መልካም የሆነች ልጅ መሆኗን እንመለከታለን። የሮን የነጋዴ ልጅ ናት። አባቷ በአስም በሽታ ምክንያት ጅማ ከተማን ለቀው አዲስ አበባ ስለሚኖሩ በጅማ ከተማ ውስጥ የሚገኙትን የአባቷን ሃብት የምትቆጣጠረው የሮን ለአባቷና ለስሟ በጣም የምትጠነቀቅ በጥሩ ስነምግባር ያደገች ልጅ ናት።

> *Abbaa fi haadha sheerraa fagaattee kan jiraattu yoo taatellee maqaa sheefi kan warrashee eegdee barumsashee hordofaa qabeenya abbasheemmoo sirnaan towattee hojiisaa gaggeessaa jirti" (Fuula:9).*

ከእናት አባቷ ርቃ የምትኖር ብትሆንም ስሟንና የቤተሰቦቿን ስም አስጠብቃ ትምህርቷንም እየተከታተለች የአቧቷን ሃብት በስነስርዓቱ እየተቆጣጠረች፣ ስራውን በትክክል እያከናወነች ነው (ገፅ፡9)።

በዚህ ሁኔታዋም በብዙዎች ዘንድ አድናቆትን አትርፋለች። በጥሩ ስነምግባር ስላደገች ለራሷና ለቤተሰቦቿ ስም ስትል በጣም ተጠንቅቃ የምትኖር ጨዋ ልጅ ነች። በ100 ሜትር ሩጫ ተወዳዳሪ የሌላት የሮን በትምህርቷም በጣም ጎበዝ ከሚባሉት ተማሪዎች ትመደባለች። "Yeroon barumsaanis akkuma ispoortii jabduudha. Sababii kanaa barsiisotaafi barattoota hiriyyootashee biratti kabajaa fi jaalala guddaa qabdi" (Fuula: 8).

"የሮን በትምህርቷም እንደ እስፖርቱ ጎበዝ ናት። በዚህ ምክንያት በመምህራኖቿና በተማሪዎች ዘንድ ትልቅ ከበረታና ፍቅር አላት"(ገፅ፡8)። "Barumsaanis taanaan kutaa 1ffaa-11ffaatti sadarkaa 1-3 argachuudhaan kutaadha gara kutaatti ceeti" (Fuula:79).

በትምህርቷም ቢሆን ከ1ኛ እስከ 11ኛ ክፍል ከ1-3 በመውጣት ከክፍል ወደ ክፍል ትዛወራለች (ገፅ፡79)።

ከሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት ያላት የሮን በተፈጥሮ በተቸረችው ጉብዝናዋም የማትኩራራ፣ ግቡቡ ልጅ ነች።

*"Dandeettiifi kennaa uumamaa qabduunis boontee ol hiixachuu hin beektu. Gara bal'eettiifi obsa qabeettii wan taateef waliigalteefi jaalalaan hiriyyootashee wajjin jiraatti" (Fuula:8).*

በችሎታዋና ተፈጥሮ ባደለቻት ነገሮች ተኩራርታ አታውቅም። ሆደ ሰፊና ታጋሽ ስለሆነች ከጓደኞቿ ጋር በሰላምና በፍቅር ትኖራለች (ገፅ፡8)።

ከዚህ ፀባይና አመለካከቷ የተነሳ እንዲሁም የአባቷን ሃብት በማየት ብዙ ሰዎች ለትዳር አባቷን ጠይቀዋል። የአባቷ መልስ ግን 12ኛ ክፍል ትጨርስ የሚል ሲሆን እሷ ደግሞ እራሴ የመረጥኩትን ሰው ማግባት እችላለሁ የምትል በራሷ የምትተማመን ልጅ ናት። በራሴ ውሳኔ ውስጥ ማንንም አያገባም የምትለው የሮን በአይን አይታ፣ በንግግሩና በመልኩ ተማርካ ለማግባት የወሰነችውን ሰለሞንን እንዲህ ብለዋለች።

*"Abdallaa kan bulchu anuma. Dhimma koo keesa seenuu hin danda'u." abbaan koo ni guddiseen malee hin dhalchine" (Fuula:19).*

አብደላን የማስተዳድረው እኔው ነኝ። በእኔ ጉዳይ ውስጥ መግባት አይችልም። አባቴ አሳደገው እንጂ አልወለደውም (ገፅ:19)። በማለት በቤታቸው ውስጥ በጉድፈቻ መልክ የየሮን አባት ያሳደጉትን አብደላን አትፈሪም ወይ? ብሎ ሰለሞን ሲጠይቃት የሰጠችው መልስ ነበር።

ማንንም ሳታማክር በራሷ ውሳኔና ምርጫ ለማንም ያልተበገረች ንፅህናዋን ጠብቃ የቆየችና በትምህርቷም የት ትደርስ ይሆን? የተባለችው የሮን "በእናትና አባቱ የተጠላ፣ ካለው ተወለድ ወይ ካለው ተጠጋ" (ገፅ:28)። የሚል መፈክር አላማው አድርጎ የተነሳውን ሰለሞንን አገባች። ሰለሞንን ካገባችበት ጊዜ ጀምሮ በጅማ ከተማ ውስጥ የተረጋጋ ኑሮ መኖር ያልቻለችው የሮን አባት እና እናቷን በማስፈቀድ አዲስ አበባ ገብታለች። ለሰለሞን ሁለት ወንድ ልጆችን ከወለደች በኋላ የተሳሳተ ትዳር ውስጥ መግባቷን ያወቀችው የሮን እንዲህ ስትል ለራሷ ትናገራለች።

*Yaa yeroon! Yaa yeroon! nama hin taanetti heerumtee qabeenya abbaafi haatikee ijoollummaa saanitti horatan bittinneessitee? Yaa yeroon! nama itti heerumtu sana seenaasaa qorattee utuu hin beekin itti heerumtee jireenya qaanessaa kanarratti kuftee? (Fuula:78).*

ወይ የሮን! ወይ የሮን! የማይሆን ሰው አግብተሽ አባትና እናትሽ በልጅነታቸው ያፈሩትን ሃብት አባከንሽ? ወይ የሮን! የምታገቢውን ሰው ማንነቱን ሳታውቂ፣ ሳታጠኚው አግብተሽ የሚያሳፍር ኑሮ ላይ ወደቅሽ? (ገፅ:78)።

የሚል ከአዕምሮዋ ውስጥ መደወል የጀመረው ሰለሞን የአባትና እናቷን ሃብት ጨርሶ ሌላ ሴት ካገባ በኋላ ነው። በራሴ ውሳኔ መሄድ ጎድቶኛል በሚል በወሰነችው ውሳኔ ከመጠን በላይ ብትፀፀትም ልጆቿን በራሷ ለማሳደግ የመጣውን መከራ ለመጋፈጥ እራሷን ስታዘጋጅ እንመለከታለን። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ልጆቿን ለማሳደግ ወዳልፈለገችው የሴተኛ አዳሪነት ህይወት የገባችው የሮን በዚህ ስራ ከተሰማሩት ሴቶች በመልክና በቁመና ስለምትበልጣቸው የብዙ ወንዶች አይን እሷ ላይ ስለሚያርፍ ከጎረቤቶቿ ሴተኛ አዳሪዎች ለገጠማት ችግር የምትሰጠው መልስ ቀና ነበር።

*"Muu haadhakoo! Hojjettuun biiroo akkakee hin jiru! ni sobdii hojjettuu biiroo maaliiti kun asitti ta'uufii didnaan karaa irratti sagaagaluuf jooraa ooltee galti!" ittiin jedhu (Fuula: 104).*

"ኤጭ! (ንቀት) እንዳች አይነት የቢሮ ሰራተኛ አልተገኘም ! የምን የቢሮ ሰራተኛ ናት እች ውሸቷን ነው፤ እዚህ ስላልሆነላት በመንገድ ላይ ዝሙት ለመስራት ብላ ስትዞር ውላ መጣች እንጂ!" አሉዋት። የሮን ግን ክፉ መልስ ሳትሰጣቸው እንዲህ ትላለች፡- "*waaqayyo isin haa'ebbisu! Eebba Waaqayyoo argadhaa" ittin jetti (Fuula:104)*
እግዚአብሄር ይባርካችሁ! የእግዚአብሄር በረከት ያግኛችሁ ትላቸዋለች (ገጽ፡104)።

"ክፉን በክፉ ሳይሆን በበጎ ነገር ነው ማሸነፍ የሚቻለው" የሚል መፈክር ያላት የሮን ከተንደላቀቀ ኑሮ ወደ ሴተኛ አዳሪነት ከዛም ወደ ቢሮ ሠራተኝነት የመጣችሁ በህይወቷ ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፋለች። በልጆቿና በአንዳንድ የሚቀርቧት ሰዎች ምክንያት ሃይማኖቷን ከእስልምና ወደ ክርስትና (protestant) ከቀየረች ጊዜ ጀምራ ለትዳር ለሚጠይቋት ሰዎች በጣም ጥንቃቄ የምታደርግ፣ የሰው ልጅ ካለፈው ህይወቱ መማር አለበት ብላ ለራሷ የምትናገረው የሮን ጠንካራ ሴት ናት። በትምህርት ምንስቴር መዝገብ ቤት ውስጥ በ182 ብር ተቀጥራ በምትሰራበት ጊዜ በስራ አስኪያጁ ለትዳር ተጠይቃ፡-

*"Nama sirriitti hin beeknetti of kennuun badisa guddaarratti nama gata. Kan Solomoon fakkeenya gaarii naa ta'uu danda'a" jechaa qofaa shee dubbachaa deemti" (Fuula:105).*

"ራስን በደንብ ለማያውቁት ሰው አሳልፎ መስጠት ለትልቅ ኪሳራ ልዳርግ ይችላል። የሰለሞን ጥሩ ምሳሌ ሊሆነኝ ይገባል" በማለት ለብቻዋ እያወራች ትሄዳለች (ገፅ፡105)።

ሰውን ሰው ነው ብለን ማወቅ የምንችለው መጀመሪያ ማንነቱን ካልተረዱ ሰው ልብስ ለብሶ ስለሄደና ከአንደበቱ ጥሩ ጥሩ ቃላቶች ስለወጡ ብቻ አይደለም የምትለው የሮን ሰውን ለማወቅ ጊዜ ወስዶ አስቦበት ካልሆነ የሰው ልጅ አስቸጋሪ እንደሆነ ከራሷ ህይወት ልምድ የወሰደች ጠንካራ ሴት ናት።

ለልጆቿ ብላ ስንት ስቃይ ያየችው የሮን ልጆቿም አድገው በመሃል ያቋረጠችውን ትምህርቷን እንድትከታተል እና ሰው እንድትሆን መንገድ ከፍቶላታል። በልጆቿ ምክንያት ወደ

ትምህርቷ የተመለሰችው የሮን የወርቅ ተሸላሚ በመሆን የህክምና ትምህርትን ለመማር በቅታለች ።

*"Yeroon barnoota toorbatti "A" toorba argattee mooticha Atse Haayile Sillaaseerraa sa'aati harkaa warqee badhaafamte... Yuuniversiitii Q/H/S Medical Faculty galte" (Fuula: 106).*

የሮን በሰባት የትምህርት አይነት ሰባት "A" በማምጣት ከንጉስ አፄ ኃይለ ስላሴ የወርቅ ሰዓት ተሸለመች። በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ትምህርት ክፍል ተመደበች (ገፅ፡106)።

ለባለቤቷ ጥሩና ቀና አመለካከት የነበራት የሮን የቤተሠቦቿን ሃብት አሚጦ ከጨረሰ በኋላ ወደ ሌላ ሴት ለገንዘብ ብሎ ሲኮበልል የራሷን ውሳኔ ወሰዳ ልጆቿንና ራሷን ለማዕረግ ያበቃች ጠንካራ ሴት ናት። ዶ/ር የሮን "ክፉን በበጎ ማሸነፍ አለብን" የሚል አስተሳሰብ ያላት ስትሆን ዶክተር ሁና ኑሮዋ ከተለወጠ በኋላ የቤተሰቦቿን ሃብት የት እንዳለ በሰማች ጊዜ አልተናደደችም።

*"Qabeenyi abbaafi haatishee horatan Qonjit harka akka jiru dhageesssee hin aarre. Haala shee itti hin jijjiirre" (Fuula: 133).*

"እናትና አባቷ ያፈሩት ንብረት ቆንጂት እጅ መኖሩን ሰምታ አልተናደደችም። ፀባይዋንም አልቀየረችባትም" (ገፅ፡ 133)።

ቆንጅት ሰለሞን የሮንን ትቶ ያገባት ደህና ሃብት ያላት ሴት ስትሆን እሷም እንደ ሰለሞን በገንዘብ እንጂ በፍቀር አታምንም ነበር። ቆንጂት፣ ሰለሞን ባደረሰባት አደጋ ሆስፒታል ገብታ በየሮን እጅ ስትታከም ለየሮን አጫወተቻት። እንዲሁም የሴተኛ አዳሪነት ህይወት በምትኖርበት ጊዜ በቅናት ህይወቷን ለማጥፋት ደፋ ቀና የሚሉትን ብርቄ እና ክብነሽንም አግኝታ ውለታቸውን በክፉ ሳይሆን በበጎ ስትመልስላቸው እንመለከታለን።

*"Dr. yeroon kibabii (kaafteeriyaa) hospitaalichaa keessatti miindesisiifte" (Fuula: 147).*

"ዶ/ር የሮንም በሆስፒታሉ ክበብ (ካፌ) ውስጥ እንዲሰሩ አስቀጠረቻቸው" (ገፅ፡147)።

በዚህ ሁኔታ ድሮ መቆሚያና መቀመጫ የሚያሳጡዋትን ጎረቤቶቿን ከዚህ አስከፊ ህይወት እንዲወጡ መንገድ ስትከፍትላቸው እነርሱም ከልባቸው ሲያመሰግኗት እንመለከታለን።

በህይወቷ ውስጥ ላጋጠማት የተለያዩ ችግሮችና ለቤተሠቦቿ ንብረት መባከን ራሷን ጥፋተኛ አድርጋ የምትቆጥረው የሮን ጋብቻዋን አስመልክታ ጥፋተኛ እኔ ነኝ ብላ ሁሌ የምትናገር ሲሆን አንድም ቀን የበደሏትን ሰዎች ለመበቀል ስታቅድም ሆነ ስታስብ ያልታየች፤ ለአላማዋ መሳካት ቆርጣ የተነሳች፤ አስተዋይና ጠንካራ ሴት ናት። ከሴተኛ አዳሪነት ህይወት ተነስታ ዶ/ር ከመሆን አልፋ ለብዙ ሰዎች መንገድ አስከመክፈት የበቃች ቀና አመለካከት ያላት ሴት ናት። ሁልጊዜ እንደምትናገረው "የሰውን ልጅ በበጎ እንጂ በክፉ ማሸነፍ አይቻልም" የምትለው የሮን ያለችውን በትክክል ስትተገብር ታይታለች።

### 3.1.3. Siintolinnaa-ሲንቶሊና

በኢሳያስ ሆርዶፋ Yoomi Laataa? (መቼ ይሆን?) ውስጥ በዋና ገፀባህሪነት የተሳለችው ሴት ሲንቶሊና ናት። በሀረር ገጠራማ ክፍል "ሐራዌ" በምትባል ስፍራ ከጭቁን በተሠቦች የተወለደችው ሲንቶሊና መልከ መልካም ልጅ ናት።

> *"Rifeensi siintolinnaa dheeratee dudda ishee irratti gadi jiga. Magaala baay'istee bareedduudha. Rabbi bifa fuula ishee barreechee akkasumas dhaabbata qaamaishee lookoo godhee mimmiidhaksee ishee uume" (Fuula: 12).*
>
> የሲንቶሊና ፀጉር በጀርባዋ ወርዶ ወገቧ ላይ ይዘናፈላል። ጠይም መልከ መልካም ናት። የፊት ገፅታዋን ያሳመራት አምላክ ቁመቷንም ለግላጋ አድርጎ የፈጠራት ልጅ ናት (ገፅ:12)።

ለንጽህናዋና ለምትለብሰው ልብሶች እንዲሁም ለምትቀባባቸው ቅባቶችና ሽቶ ምርጫ የምታበዛ ሲንቶሊና መኳኳልና ፅዱ ሆኖ መታየት ይቀናታል።

> *"Haala ishe tahee siintolinnaan uffata gaarii uffachuu, dhiqachuu fi dibattee filattee of mimmiidhaksuu ni jaallatti" (Fuula:19).*
>
> "ተፈጥሮዋ ሆኖ፣ ሲንቶሊና ደህና ልብስ መልበስና ታጥባና ተቀባብታ መኳኳል ትወዳለች" (ገፅ:19)።

በ16 አመቷ በቤተሠቦቿ ፍላጎት ከ8ኛ ክፍል ትምህርቷን አቋርጣ ያደኖ ጃራን ያገባችው ሲንቶሊና በአመቱ አንድ ወንድ ልጅ ወለደችለት። ይህ ዘመን የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመነ

መንግስት ስለሆነ ከመላው የኦሮሞ ብሔረሰቦች መሬታቸውና ያላቸው ሃብት በሙሉ ተወስዶ ለሀገር ገዥ ባለሥልጣናት ስለተከፋፈለ ሲንቶሊናና ባለቤቷ ያደኖ የራሳቸው የሆነ ምንም ነገር ስለሌላቸው በቀኝ አዝማች ግዛቸው አበራ ቤት ተቀጥሮ መስራት ግድ ሆነባቸው። በአባታቸውና ቅድመ አያቶቻቸው መሬት ላይ መብት አጥተው ለሰው ተቀጥሮ መስራት እጣ ፈንታቸው ሆነ።

> *"Qanyaazimaachi intala bareedduu kana qalaadii isaarratti argachuu isaa akka carraa guddaatti lakkaa'a. Siintolinnaanis fedhii ishee malee dirqiidhaan wajjin ciisti" (Fuula :12).*
>
> ቀኝ አዝማች እንደዚህ ያለች መልከ መልካም ልጅ 'በቀላዳቸው' ላይ በማግኘታቸው እንደ ትልቅ እድል ይቆጥራሉ። ሲንቶሊናም ሳትወድ በግድ ከእርሱ ጋር ትተኛለች። ከቀኝ አዝማች ጋር የምታደርገውን ግንኙነት ፈልጋ ሳትሆን ተገዳ የምታረገው ስለሆነ እረፍት እየነሳት፣ የአእምሮ ህመም እየተሰማት ትፈፀመዋለች (ገጽ፡ 12)።
>
> "Itti hadhaawa garuu maal haagootu? Filannoo gara biraa hin qabdu" (Fuula: 12).
>
> ይመራታል ነገር ግን ምን ታደርጋለች? ሌላ አማራጭ የላትም (ገፅ፡12)።

ባሏ ይሄን ጉዳይ ሳይሰማ ቆይቶ አንድ ቀን በድንገት አንድ ላይ አግኝቶአቸው ቀኝ አዝማችን ገድሎ ሸፈተ። በዚህን ጊዜ ሲንቶሊና በሀረር ከተማ ውስጥ መኖር እንደማትችል በመገንዘብ ልጇን አዝላ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ መንገድ ዳር ቆማ የሚያልፈውን መኪና ትለምናለች። ሲንቶሊና እንደ አጋጣሚ ሆኖ ያገኘችው መኪና የአፄ ኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ባለስልጣን የሆኑትን የራስ ጌታውን ሚንዳስይልን መኪና ነበር። ራስ ጌታውንም የሲንቶሊናን ውበት እና ንፅህናን በማድነቅ እንዲሁም ልጅ አዝላ በማየታቸው በመኪናቸው ይዘዋት ለመሄድ ወስነው አቆሙላት። ራስም ከሲንቶሊና ጋር መጫወት ፈለጉና ስሟንና የልጇንም ስም ከጠየቁ በኋላ የስሟን ትርጓሜ ሲጠይቋት፡-

> "Abbaan kee maqaakana akkamittiin siif maggaase?" (Fuula፡ 23).
>
> "አባትሽ ይሄን ስም እንዴት አወጡልሽ? ወይም ሰየሙልሽ?"

*Hacuuccaan itti hammaatee barri toluuf didnaan barri dhufu siintolinna? Hacuuccaafi roorroon nafxanyootaan nurratti rawwatamaa jiru kun dabree barri nuuf tolu nuuf dhufaa laata? siintolinnaa laata? Siintoluu danda'a taha. Lafti nurraa fudhatame nuuf deebi'a ta'a. jechuu isaa akka tahe yeroo dubbatu nin dhagahan ture (Fuula: 23).*

ጭቆና በዝቶበት የዘመኑ አገዛዝ ስላስመረረው የሚመጣው ዘመን ባንቺ ይቀናኝ ይሆን? በነፍጠኞች እጅ የምንረገጥበት እና የምንበዘበዝበት ጊዜ አልፎ ጥሩ ጊዜ ይመጣ ይሆን? ባንቺ ይቀናኝ ይሆን? ባንቺ ሊቀናኝ ይችል ይሆናል። የተወሰደብንም መሬት ይመለስልን ይሆናል። ማለቱ እንደሆነ ሲናገር እስማለሁ። በማለት ሲንቶሊና ግልፅነቷን አስመሰከረች (ገፅ፡23)።

ተፈጥሮዋ ሆኖ ዝምተኛ አይደለችም። ተጫዋችና ሳቂታ ልጅ ናት። በቶሎ ሰውን የመልመድ ነገር የሀረር ልጆች ተሰጥኦ ነው። ተጣልታ ሰውን ማኩረፍ አታውቅም። ነገሯ በሙሉ ግልፅ ነው (ገጽ፣ 38)። ይሄን ሃሳቧን ደግሞ የምንረዳው ራስ ጌታውን ወደ ቤታቸው ይዞ በመግባት ልጇን እንደ ልጃቸው ለማሳደግ ከባለቤቱ ጋር ተመካክረው ሲስማሙ ራስ ከዚህም ውጭ ሌላ አላማ ስላላቸው ባለቤታቸውን ደብቀው ሲንቶሊናን መገናኘት ይፈልጋሉ። የራስ ጌታውን ሹፌር ዋሪዮ ደግሞ ሲንቶሊናን በግልፅ ለጋብቻ ይፈልጋታል። ተስማምተዋልም። ነገሮችን ደብቆ መጨነቅ የማይሆንላት ሲንቶሊና ራስ ባገኙት አጋጣሚ ከእርሷ ጋር ባደሩበት ቀን ዋሪዮ ተናዶ ሲጠይቃት፡-

*Waariyoo kiyya! Akkam abbaa kiyya godhu?... "haayi! Ani duuba akkamin godhaa? Yoon sitti hime aartee gubatta. Yoon jaarsa dide kan anarra gahuu danda'u atillee hin wallaaltu... jettee akka boo'uu taate (Fuula:45).*

እንዴት አባቴ ልሁን! የእኔ ዋሪዮ!... " ሃይ! እንዴት ላድርግ? ብነግርህ በንዴት ትቃጠላለህ። ሽማግሌውን እምቢ ብለው ደግሞ የሚደርስብኝ ነገር ካንተም የተሰወረ አይደለም" አለች እንደማልቀስ ሁና። ዋሪዮ የራስ ጌታውን ሹፌር እና የመንግስት ሰራተኛ ነው። "እኔ በመኪና ወስጄው ወደ ገደል መግባት አያቅተኝም ሌላ ነገር ቢያቅተኝ" ብሎ ሲናገር ዋሪዮን ለማረጋጋት የምታደርገው ጥረት አስተዋይነቷን ይገልፃል።

*"Haayi! Gurbaa ni maraattee aniifi ati wal fudhannee badnee waliin jiraachuu osoo dandeenyuu kana yaaddaa?...maaliif of balleessuu yaaddaa? Jette" (Fuula: 85).*

ወይ! አንተ! አብደሃል? እኔ ና አንተ ተያይዘን ጠፍተን አብረን መኖር እየቻልን ለምን ይሄን ታስባለህ?... ለምን ራስህን ለማጥፋት ታስባለህ? አለችው (ገፅ፡85)።

ሲንቶሊና በትምህርት ደረጃዋ በኩል ስትታይ ከዋሪዮ አትደርስም። እርሱ ትምህርቱን ጨርሶ የመንግስት ተቀጣሪ ሆኖ የሚሰራ ነው። በዚህም ላይ ሹፍርና ተምሯል። ነገር ግን ከንዴት የተነሳ "ራስ ጌታሁንን ወስጄው በራሱ መኪና እሱንም ራሴንም አጠፋለሁ" ሲል ይደመጣል። ሲንቶሊና ግን የተሻለ ነገር ስታቀርብ እንመለከታታለን።

ሲንቶሊና በራስ ጌታውን ቤት ሠራተኛ ሆና እያለች በግልፅ ዋሪዮን አግብታ ሁለት ልጆችን የወለደች ስትሆን አንድ ወንድ ልጅ "ኦብስና" እና ሴት ልጅ "ኦብስኔ" ይባላሉ። ትርጉሙም "እንታገሳለን" እና "ታገስን" የሚል ነው። ሲንቶሊና እነዚህን ልጆች እንደዚህ ብላ የሰየመቻቸው በሰው ቤት አገልጋይነት እያሳለፈች ያለውን ህይወት ለማስታወስ ያደረገች ይመስላል። በዚህ ሁኔታ እያለች ደርግ ከኃይለ ስላሴ ሥልጣን የወሰደው በሚያዝያ ወር 1966 ዓ.ም. ነበር። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ራስ ጌታውንና ባለቤታቸው በተለያዩ ጊዜ በደርግ ባለስልጣናት በደረሰባቸው ጫና እና እንግልት ህይወታቸው ያልፋል። ከዚህ ጊዜ አንስቶ ሲንቶሊናና ፍቅር የራስ ጌታውንን ንብረት የራሳቸው አድርገው መቆጣጠር ቢጀምሩም ከደርግ ባለስልጣናት በተለያዩ ጊዜ ዛቻና ማስፈራሪያ ይደርስባቸው ነበር። አንዳንድ ጊዜ በጠባብ ብሔርተኝነት፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ "EDU" ማለትም Ethiopian Democratic Union ማለት ሲሆን "የቀድሞ የዘውድ አገዛዝ ለመመለስ በ1976 ዓ.ም. የተቋቋመ ድርጅት ነው።" በእነዚህና በተለያዩ ነገሮች ተጠራጥራ ስትታሰር እና ስትሰቃይ ቆይታ ህይወት አልሆንላት ሲላት ተመልሳ ወደ ትውልድ ሃገሯ ሀረር ሄዳ የራሷን ሆቴል ከፍታ መኖር እስከጀመረችበት ጊዜ ድረስ ብዙ ውጣ ውረዶችን ያሳለፈች ነገር ግን አንድም ቀን ለገንዘብና ለጥቅም ብላ ማንነቷን አሳልፋ ያልሰጠች ጠንካራ ሴት ናት።

በሀረር ከተማ ውስጥም 'ሲንቶሊና ሆቴል' ብላ የራሷን የተረጋጋ ኑሮ መምራት ስትጀምር ሆቴሏ "የሽፍቶች መናኸሪያ" ተብሎ በመጠርጠሩ በደርግ ባለስልጣናት ተይዛ ወደ እስር ቤት ተወሰደች። በዚህ ማረሚያ ቤት ውስጥም የሞት ፍርድ የተፈረደባት ነገር ግን በአንዳንድ ስልጣን ላይ ባሉ የኦሮሞ ተወላጆች ምክንያት ከሞት ተረፈች። ከዚያም ሀረር ከተማ ውስጥ

ዳግም መኖር እንደማይቻል አምና ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የኖረች ጠንካራና አስተዋይ ሴት ናት።

ተመልሳ አዲስ አበባ እንደገባች የደርግ ባለስልጣናት ልጇን ለውትድርና ለመመልመል ተዘጋጅተው ሃብት አላት ስለተባለች "50ሺ ብር ጉቦ ካላመጣሽ ልጆችሽ ወደ ውትድርና ይላካሉ" ተባለች። ብሩን ለባለስልጣናቱ ካስረከበች በኋላ ሃላፊው ሴት ልጅሽንም እፈልጋለሁ ሲሏት፡-

> *Isin foon keenya nyaattani dhiiga keenya dhuguuf aangoo qabattan malee uummata bal'aa Itiyoophiyaaf yaaddanii miti. Garaa keessaniif qabsooftu malee uummataaf miti. Garuu maqaa uummata baldhaatiin daldaltu. Mee kan ati fiddun ilaala. Intalakoos hin argattu. Birrii koos naaf deebisi (Fuula:254).*
>
> *እናንተ ስጋችንን በልታችሁ ደማችን ለመጠጣት ስልጣን ላይ ወጣችሁ እንጂ ለሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አስባችሁ አይደለም። ትግላችሁ ለሆዳችሁ ነው እንጂ ለህዝብ አይደለም። ነገር ግን በሰፊው ህዝብ ስም ትነግዳላችሁ። እስቲ የምታመጣውን አያለሁ። ልጄንም አታገኛትም፣ ገንዘቤንም መልስልኝ በማለት ሞትንም እንደማትፈራ ገለፀችለት(ገፅ፡254)።*

እዚህ ላይ ሲንቆሊና ራሷን ሳታስበልጥ ያላትን ሀብት ሰብስባ ለባለ ስልጣናት ጉቦ ሰጥታ ልጆቿን ለማትረፍ ስትጥር እንመለከታታለን። ነገር ግን ባለስልጣናቱ 50 ሺህ ብር ከተቀበሉ በኋላ ሴት ልጇንም ለፆታዊ ግንኙነት እንደሚፈልጉ ሲነግሯት ነበረ፣ "እኔ ከዚህ በኋላ ሞትን አልፈራም" ብላ የምትናገረው። "ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች" የሚባለውን አባባል የተገበረች ለልጆቿ ስትል እስከ ሞት መሰዋዕት የከፈለች ጀግና ሴት ናት።

ሲንቆሊና በጣም ግልፅ፣ ለሰው አዛኝ፣ የራሷን ጥቅም የማታስቀድም፣ ምስጢር ጠባቂ፣ ቅን ሁና ነው የተሳለችው። ነገር ግን ከ16 ዓመት እድሜዋ ጀምሮ አንድም ቀን የተረጋጋ ኑሮ መምራት ያልቻለች በፊት በሰው ቤት ስትንገላታ፣ ከፈቃዷ ውጪ ከማትወደው ሰው ጋር የምትተኛ በኋላ ደግሞ በተለያዩ የመንግስት ባለስልጣናት ዘንድ ተጠርጥራ ስትታሰርና ስትገረፍ ለማንነቷ መከራከር የማትችል፣ ለመናገር መብት የሌላት፣ ብትናገርም እስከሞት ልትቀጣ የምትችል ነገር ግን ለሚደርስባት ችግር አንድም ቀን ያላጎረመረመች ነገ ሌላ ቀን ነው በማለት ህይወቷን የመራች አስተዋይ ሴት ናት።

## 3.2. በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ተመሳስሎ እና ልዩነት

### 3.2.1. የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያቱ ተመሳስሎ

በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ ተቀርፀው የቀረቡት ዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት በውጫዊ መልካቸው ቆንጆና የሚስቡ ሲሆኑ በውስጣዊ ገፅታቸውም ውብ ሆነው ተስለዋል። በነዚህ ልቦለዶች ውስጥ የተሳሉት ሴት ገፀባህሪያትን የጠይም ቆንጆ አድርጎ በመቅረፅ ደራሲው እርስ በርሳቸው አመሳስለዋቸዋል። የገፀባህሪያቱን ውስጣዊ ማንነታቸውን የተመለከትን እንደሆነ ጠንካሮች፣ አስተዋዮችና አላማዬ ብለው የተነሱትን ነገር ከግቡ ለማድረስ ቆርጠ የተነሱ ናቸው። የራሳቸውን ፍላጎት ለማሳካትና ለሌሎች ፍላጎት መሳካትም ሲሉ የራሳቸውን ምቾትና ደስታ ወደ ጎን በመተው እስከ ሕይወት መስዋዕትነት የደረሱ ናቸው። በፍቅር ህይወታቸውም ታማኝ አፍቃሪዎች፣ ለወንድ ጓደኞቻቸው ጥሩና ቀና አመለካከት ያላቸው በመሆናቸው በብዙ መልኩ ይመሳሰላሉ። በአጠቃላይ ሰብእናቸውን በማየት ይህን ያህል ይመሳሰላሉ. ካልን የሴቶቹን የህይወት ውጣ ውረድ፣ የቤተሰቦቻቸውን ሁኔታና ከአጠቃላይ የህይወታቸው ቅንብብ ተነስተን ስንመለከትም ብዙ የሚያመሳስላቸው ነገሮች አሉ።

የአላማ ጽናታቸው፣ ጠንካራነታቸውና የመልካቸው መመሳሰል እንዲሁም ለሰው ልጆች እኩልነት ያላቸው አመለካከት እንዳለ ሆኖ እነዚህን ሴቶች የሚያመሳስላቸው ሶስት ትልልቅ ጉዳዮች አሉ። እነርሱም፡-

#### 3.2.1.1. ብቸኛ ሆኖ መወለድ

የእነዚህ ሴቶች ቤተሰቦች ከእነዚህ ሴቶች ውጪ ሌላ ልጅ አለመውለዳቸውን የሚጠቁሙ ነገሮች በልቦለዶቹ ውስጥ ተጠቅሰዋል።

> *Akka kanaan aadde Dinsiriifi obbo Bulchaan dhala dhaban argachuuf utuu hawwanii Latiin dhalatee waggaa 2ffaa irratti durba argatan. Kan hawwan dhabanii jireenyi isanii inni gaddaan golgamee ture gammachuudhaan bakka bu'e. kanumaan maqaa ishee Hawwii! Jedhanii moggaasan (Hawwii, Fuula:17).*

በንደዚህ ዓይነት ወ/ሮ ድንስሪ እና አቶ ቡልቻ ልጅ ለመውለድ ሲመኙ ለቲ ተወልዶ በሁለተኛ አመቱ ሴት ልጅ አገኙ። የተመኙትን ስላገኙ በሃዘን ተሸፍኖ የኖረው ኑሮአቸው በደስታ ተሞላ። ከዚህም የተነሳ ምኞት/ተስፋ ብለው ስየሟት (ሀዊ፣ገፅ፡17)።

እነዚህ ቤተሠቦች ሀዊን ካገኙ በኋላ ምንም አይነት ልጅ አልወለዱም። የየሮንም ቤተሠቦች ስንመለከት ተመሳሳይ ሁኔታ ይታይባቸዋል።

"Yeroon barattuu kutaa 11ffaa dha. Haatiifi abbaanshee ishee malee dhala garabiraa hin qaban" (Yeroon Siif Haadhiiftu Fuula:7).

የሮን የ11ኛ ክፍል ተማሪ ናት። እናትና አባቷ ከእርሷ በቀር ሌላ ልጅ የላቸውም ።

አባ ገሮ ማለትም የየሮን አባት ብዙ ሃብትና ንብረት ቢኖራቸውም ከየሮን ውጪ ሌላ ልጅ አልወለዱም። ከዚህም የተነሳ በአንዳንድ ስራ እንዳይቸገሩ የጉዲፈቻ ልጅ እንዳላቸው ተገልጿል።

የሲንቶሊና ቤተሠቦች ስም በልቦለዱ ውስጥ አንድም ቦታ አልተነሳም። ሲንቶሊና ከሀረር ክፍለ ሃገር "ሐራዌ" ከምትባል ገጠራማ ክፍል አንዲት መልከ መልካም የ16 ዓመት ልጅ ተገኝታ ያደኖ ጀራን እንድታገባ ተደረገች ከማለት ውጪ ምንም አልተነገረንም ሌላ ወንድምም ሆነ እህት እንደሌላት ለመገመት የሚያስችለን ደግሞ ይህ ሁሉ ታሪክ ሲነገረን አንድም ቦታ እህቷም ሆነ ወንድሟ እንዲሁም ዘመዶቿም ሲነሱ አለማየታችን ብቻዋን የተወለደች ትሆናለች ለማለት ያስችለናል። እንዲሁም አባቷ "ስቃይና እንግልት ሲበዛባቸው አንዲት ልጅ ብቻ ወልደው ምናልባት ባንቺ እንኳ ይቀናኝ ይሆን? ጥሩ ገድ ይኖርሽ ይሆን? ከአንቺ እድል የተነሳ የተወሰደብን መሬት ይመለስልን ይሆን?" ብሎ አንዲት ልጅ ብቻ ወልደው ያቆሙ ይመስላሉ።

ምክንያቱም የሲንቶሊና አባት በራሳቸው መሬት ላይ የመሬት ባለቤትነት ተነፍገው ለሰው ተቀጥረው መስራት እጣፈንታቸው ስለሆነባቸው ከዚች ልጅ ሌላ ለመውለድም ያቀዱ አይመስልም። እራሳቸውም የሚተዳደሩበት የግል ንብረት ስለሌላቸው።

### 3.2.1.2. በስተርጅና መወለድ

የእነዚህ ሴቶች ቤተሰቦች ከነዚህ ሴቶች ውጪ ልጅ አለመውለዳቸው ብቻ ሳይሆን የተወለዱትም ልጆች ተስፋ ከቆረጡ በኋላ፣ እድሜያቸው ከገፋ ያገኙ መሆናቸውን እንመለከታለን።

> Jireenyi maatii kana lamaan ii haala kanaan kana walfakkaatu yoo tahu karaa gara biraan ammoo dhala malee hafuu isaanitti baay'ee gaddu turan (Hawwii, Fuula:11).
>
> የእነዚህ ሁለት ቤተሰቦች የንሮ ሁኔታ በዚህ መልኩ የሚመሳሰል ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ያለልጅ በመቅረታቸው በጣም ያዝኑ ነበር (ገፅ:11)።

እዚህ ላይ ሁለቱ ቤተሰቦች ሲል የለቲና የሀዊ ቤተሰቦችን ማመላከት ሲሆን ሁለቱን በቤተሰቦች የሚያመሳስላቸው ትልቁ ነገር እድሜያቸው ካረጀ በኋላ ልጅ የመውለዳቸው ነገር ነው።

የየሮን ቤተሰቦች የሮንን ያገኙት እድሜያቸው ከገፋ በኋላ ነው ብለን መናገር የሚንችለው ደግሞ የሮን የ11ኛ ክፍል ተማሪ እያለች እድሜዋ 17 ነበር። በዚህ ሰዓት ቤተሠቦቿ ደግሞ ብዙ ሃብትና ንብረት አፍርተው ጅማ ከተማን በመልቀቅ አዲስ አበባ ገብተዋል። እንዲሁም የአባቷ የእድሜ መግፋት ተደማምረው የአስም በሽታ ስለ ባሰባቸው ቦታ ቀይሮ ለመኖር አዲስ አበባ ገቡ። በዚህ ጊዜ አባገሮ እድሜያቸው እንደገፋ የሚጠቁመን ነገር የአስም በሽታቸው መባባስ ሲሆን፤ ከዚህም በተጨማሪ የየሮን አባት ሰለሞንና የሮን ከጅማ ወደ አዲስ አበባ ከመጡ ብዙ ሳይቆዩ ነው የሞቱት። የሮንና ሰለሞን ደግሞ ተጋብተው ሁለት አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነበር ወደ አዲስ አበባ የሄዱት። ከዚህ ተነስተን የየሮን ቤተሰቦች የሮንን ሲያገኙ እድሜያቸው ገፍቷል ማለት እንችላላን።

ሲንቶሊና በእድሜ ከገፉ ቤተሰቦች መገኘቷን የሚጠቁም ነገር ቢኖር ግፍ እና ጭቆና በዝቶበት ተማሮ ከሚናገረው አባቷ አንደበት መገመት ይቻላል። ሳይወልዱ ቆይተው ነገር ግን በስተርጅናቸው ምን አልባት ልጅ ብወልድ ጥሩ ገድ ሊኖራት ይችላል በሚል ሰበብ አንዲት ልጅ ብቻ የወለዱ ይመስላሉ። ምክንያቱም ሲንቶሊና የስሟን ትርጉም ስትጠየቅ እንዲህ ብላለች፤ "በአንቺ እንኳ ይቀናኝ ይሆን? ጥሩ ገድ ይኖርሽ ይሆን? ከአንቺ የተነሳ የተወሰደብን መሬት ይመለስልን ይሆን?" (ገፅ:23)። ብሎ አባቴ ሲናገር እሰማው ነበር ትላለች። ከዚህ በመነሳት አባቷ አንድ ልጅ እንኳ ብወልድ ይሻል ይሆን ብለው ከሸመገሉ በኋላ የወለዱ ይመስላሉ።

### 3.2.1.3. ትዳር

የእነዚህን ሴቶች የትዳር ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ ሌላ የሚያመሳስላቸው ነገር እናገኛለን። ለሁሉም የመጀመሪያ ከሆነችው ሀዊ ብንነሳ፡-

ሀዊ ቤተሰቦቿ የመረጡላትን ባል አልፈልግም በማለት እዚህ ግባ ሊባል የማይችለውን ለቲ ጅሬኛን ካላገባሁ በማለት በቤተሰቦቿ ፍቃድ የተዘጋጀውን ድግስ ረግጣ ወደ አዲስ አበባ ኮብልላለች። የሮን አባገሮም በትምህርቷ በጣም ጎበዝ ስለሆነች አባቷ "12ኛ እስከምትጨርስ ለማንም አልድርም" ብለው ሲያወሩ እሷ ግን በራሷ ምርጫ ሰለሞንን አግብታለች። 'ከነዚህ ሴቶች የቤተሠቦቿን ምርጫ እሺ ብላ የተቀበለችው ሲንቶሊና ብቻ ናት።

ከትዳር ጉዳይ ሳንወጣ ሌላ የሚያመሳስላቸው ነገር ደግሞ የሦስቱም ሴቶች የችግራቸው መንስኤ የሚጀምረው ከትዳር ነው ወይም በኑሮአቸው ላይ ትልቅ አንቅፋት የሚያመጣው በትዳር በኩል የሚመጣ ነገር ነው። ሀዊ የተዘጋጀላትን "ትዳር" አልቀበልም በማለት ከቤት ወጣች። የሮን በሰለሞን በኩል በተፈጠረው ነገር መማር ይቅርና ጅማ ከተማ ውስጥ መኖር እንደማትችል ስለተገነዘበች ወደ አዲስ አበባ ተሰደደች። ሲንቶሊናን ስንመለከታትም ደግሞ በእርሷና በቀኝ አዝማች ግዛቸው መካከል በተፈጠረው ነገር ባሏ ቀኝ አዝማችን በመግደሉ ሀረር ከተማ ውስጥ መኖር እንደማትችል ስለተረዳች ወደ አዲስ አበባ አመራች። ስለዚህ እነዚህን ሴቶች ስንመለከታቸው የችግራቸው ዋነኛ ጉዳይ የሚነሳው <u>ከትዳር</u> ጋር ተያይዞው ነው። ከችግራቸው ለማምለጥ የሚመርጡት ሀገር ደግሞ አዲስ አበባን ነው። ከዚህ በተጨማሪ በነዚህ ሴቶች ላይ ችግር እንዲፈጠር ዋነኛ ተዋናይ የሚሆኑት የገዛ ዘመዶቻቸው ናቸው። የሀዊ ቤተሰቦች እኛ ያልነውን ሰው ካላገባሽ ስላሏት ትምህርቷን በመሃል አቋርጣ ተነሳች። የሮንም በገዛ ባሏ ሰበብ ህይወቷን ለማጥፋት እንደሚፈልጓት ስለተረዳች የትውልድ ቀየዋን ለመልቀቅ ተገደደች። እንዲሁም አዲስ አበባ ውስጥ ለሴተኛ አዳሪነት ህይወት የተዳረገችው በገዛ ባሏ ምክንያት ነው።

በአጠቃላይ እነዚህ ሴቶች እንድሳካላቸው የሚፈልጉ የራሳቸው የሆነ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ ፍላጎት እና ርእዮት አላቸው። ይሂን የራሳቸውን ፍላጎት ለማሳካት የሚፍጨረጨሩ ናቸው። በዚህ ውስጥ ደግሞ አንድም ጊዜ በብርና በተለያዩ ጥቅማጥቅሞች አልተደለሉም። ነገር ግን የራሳቸው የሆነ እንዲሟላላቸው የሚፈልጉት ነገር አላቸው። ሀዊ ለቲ በውጭ ሀገር ከእሷ ውጪ ሌላ ነገር አስቦ ከሆነ እኔ ሞቴን እመርጣለሁ ብላ ወሰናለች። ሲንቶሊና ከሰው ቤት ወጥታ የራሷን ሥራ ከጀመረችበት ጊዜ አንስታ በፖለቲካ ምክንያት የተረጋጋ ኑሮ መምራት

አልቻለችም እንጂ ሃብት አግኝታለች። ከዚህ የተነሳ ወገኖቻቸውን ነፃ ለማውጣት ጫካ ለጫካና በሰው ሃገር ውስጥ መከራ የሚያዩትን ወገኖቿን "በገንዘብ በኩል እኔ አለሁ" ብላ በድብቅ እየረዳቻቸው ነው። የሮን አባገሮ ከሃብታም ቤተሰብ በመወለዱ እንደልቧ እየበላችና አማርጣ እየለበሰች በቅምጥል ያደገች ልጅ በገዛ ባሏ በኩል ደህነት አይኑን አፍጥጦ ሲመጣባት ልጆቹንም ዞሮ ሳያይ እሷ ላይ ጥሎ ወደ ሌላ ሴት ለብር ብሎ የኮበለለውን ባሏን ትታ ገና ልጆቼ ያሳልፉልኛል በማለት ከተለያዩ ሰዎች የትዳር ጥያቄ እንኳ ቢቀርባላትም ካለፈው ኑሮዬ ትምህርት ወስጃለሁ በማለት ለልጆቿ ስትል መራራ ኑሮ ያሳለፈች፣ ሳትወድ ተገዳ የነፍስ ቁስል እያመማት የማትወደውን የሴተኛ አዳሪነት ኑሮ ኑራለች።

ሀዊ ገና የ10ኛ ክፍል ተማሪ እያለች በነቀምቴ ከተማ አለ የሚባል ሃብታም እንኳንስ የቤተሰቦቿን ኑሮ የዘመዶቿንም ህይወት መቀየር የሚችል ሃብታም ነጋዴ እምቢ አላገባውም በማለት "እከኩን ሊያወርሳት ነው" ብለው የተሳለቁበትን የደሃ ልጅ ለቲ ጅሬኛ ይሻለኛል በማለቷ ከቤት ወጥታለች። ለእርሱ ስትልም ከአቅሟ በላይ የሆኑ ፈተናዎችን ስትጋፈጥ ከቆየች በኋላ በመጨረሻ ሰዓት ሸክሙ ሲከብዳት እስከዛሬ ያቆየሁትን ማንነቴን ለሌላ ሰው አሳልፌ ከምሰጥ ሞቴን እመርጣለሁ የምትለው ሀዊ ለሰው ልጅ ትልቅ ከበረታ ያላት እንዲሁም "የሰው ልጅ ውስጡ ንፁህ ከሆነ አንድ ቃል ይበቃዋል" የሚል የራሷ መፈክር ያላት መርዝ ጠጥታ ሆስፒታል እስከገባችበት ጊዜ ድረስ የራሷን ፍላጎት የማታስቀድም ለሰው የምትጨነቅ ምስኪን የደሃ ልጅ ናት።

እነዚህ ሴቶች የሚያፈቅር ልብ እያላቸው ነገር ግን የእኔ የሚሉት ነገር ወይም ያለሙት ነገር እስኪሳካላቸው ምንም ነገር አናደርግም ብለው ሆዳቸውንና ቀልባቸውን ሰብስበው ለነገ የቆሙ ጀግኖች መሆናቸው እና የአላማ ፅናታቸው ያመሳስላቸዋል። ከዚህም ውጪ ሴቶቹ እንደተለኮሱ ሻማ በመሆን ራሳቸውን ለሌላ ሰው ወይም ወገን ሲሉ የሚሰው፣ ለመበልፀግና ለዝና የማይሯሯጡ፣ እውነት የሚወዱ፣ የሰውን ስሜት የሚረዱ፣ ታማኝ፣ ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሌሎች እና ለነጌ ብለው የሚጨነቁ ከፍተኛ መስዋዕትን የሚከፍሉ በደመነፍስ ሳይሆን በእቅድ የሚመሩ ራሳቸውንና ማንነታቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው ተመሳስሎአቸው የጎላ ነው።

ከመጀመሪያውንም እነዚህ ሴቶች የተገኙት በእድሜ ከገፉ ቤተሰቦች በመሆናቸው ከቤተሰቦቻቸው የወረሱ ጥሩ ጎኖች ሊኖሩ ይችላሉ። በኦሮሞ ባህል ውስጥ (Mucaan kun akka dhala jaarsaati hojiin isaa) "ይህ ልጅ የነገር አሰራሩ እንደ ሽማግሌ ልጅ ነው"

ሲባል ልጁ አስተዋይ፣ ስራውም ጥብቅ ነው ለማለት ተፈልጎ ነው። በሽማግሌ ስር ያደገ ልጅ አስተዋይ፣ ለነገሮች የማይቸኩል፣ የሚያገናዝብ፣ በራሱ ላይ ከፍ ያለ እምነት ያለው እንደሚሆን በባህል ደረጃ ይወራል። ስለዚህ እነዚህም ሴቶች ከእንደነዚህ ሰዎች በመገኘታቸው በራሳቸው ግላዊ አመለካከት ላይ የራሱ የሆነ ተፅእኖ ሊኖረው ይችላል።

### 3.2.2. የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያቱ ልዩነት

የእነዚህ ሴቶች ተመሳስሎ ጎልቶ ቢታይም በእውኑ ዓለም የሚኖሩ ሰዎች ምንም ያህል ቢመሳሰሉም ልዩነት ስለማያጡ በልቦለድ አለም ውስጥ የሚኖሩም ገፀባህሪያት እንደሚመሳሰሉ ሁሉ በመሃከላቸው ልዩነት አይጠፋም። እነዚህን የኢሳያስ ሆርዶፋን ሴቶች ስንመለከታቸው በአብዛኛው ልዩነታቸው ጎልቶ የሚወጣው በሚከተሉት ሃይማኖት፣ በቤተሰቦቻቸው የኑሮ ሁኔታና ከትውልድ ቦታቸው አኳያ ስንመለከታቸው ብቻ ነው።

#### 3.2.2.1. ሃይማኖት

ሀዊ በምስራቅ ወለጋ በነቀምቴ ከተማ ከደሃ ቤተሰብ የተወለደች የክርስትና እምነት ተከታይ ልጅ ነች። ይህን የሚያረጋግጥልን ደግሞ የለቲ ቤተሰቦች ማታ በለቲ እና ሀዊ ጉዳይ ላይ ተኝቶ ሲመካከሩ እንሰማለን።

> *"ani woo isa hin jenne abbaa Laatii! Haaji Yusuuftu kiristaana tahamoo Bulchaafaatu kirrii isaanii kutanii Islaama ta'uu?" jettee gaafatte (Hawwii, Fuula:46).*
>
> "እኔ የምልህ የለቲ አባት! ሐጂ የሱፍ ነው ክርስቲያን የሚሆነው ወይስ እነ ቡልቻ ናቸው ክራቸውን በጥሰው እስላም የሚሆኑት?"

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የሀዊ ቤተሠቦች ሀዊን ጨምሮ የክርስትና እምነት ተከታይ እንደሆኑ ነው። ከዚህም ሌላ ሀዊ የክርስትና እምነት ተከታይ እንደሆነች የሚጠቁሙ ነገሮች አሉ።

> *"...haala jireenya achi keessaa hiriyooti ishee, ishee madaqsanii jiru. Gaafa Dilbataa mana sagadaa fudhatanii deemu"-(Hawwii, Fuula: 147).*
>
> እዛ ውስጥ ያለውን ህይወት ለምዳለች፣ ጓደኞቿ አስለምዷታል። እሁድ እሁድ ደግሞ ቤተክርስቲያን ይዟት ይሄዳሉ።

ከዚህ እና ከመሳሰሉት ጉዳዮች ተነስተን ሀዊ የክርስትና እምነት ተከታይ እንደሆነች እርግጠኛ መሆን ይቻላል። የሮን አባጋሮ በጅማ ከተማ አሉ ከሚባሉ የሃብታም ቤተሠብ የተወለደች የእስልምና እምነት ተከታይ ነች።

"Hundi isaanii hordoftoota amantii Islaamaa waan ta'aniif jimaa malee dhugaatii alkoolii hin dhugani" (yeroon, Fuula: 20).

"ሁላቸውም የእስልምና እምነት ተከታይ ስለሆኑ ጫት እንጂ "አልኮል" አይጠጡም።

ከዚህ እንደምንረዳው ሁላቸውም ሲል የሮንን ጨምሮ ከእርሷ ጋር የሚኖሩ ሁለት ሴት ዘመዶቿን፣ ሰለሞን እና የየሮን አባት በጉዲፈቻ ያሳደጉትን አብደላን ጨምሮ ማለት ነው። የሮን በኃላ ሃይማኖቷን ወደ ፕሮቴስታንት ብትቀይርም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ እንደነበረች በልቦለዱ ታሪክ በብዙ ቦታ ተገልጿል። በሌላ ቦታም ሰለሞን ወደ ሌላ ሴት ሲኮበልል የሮን ለጠየቀችው ጥያቄ ከሚሰጠው መልስ ምን አይነት ሃይማኖት እንደሚከተሉ መረዳት እንችላለን።

"*maal solomoon rabbiin hin sodaattuu utuu ani jiruu dubartii gara biraa fuudhuun maalif sibarbaachisee?" "kasaaraa irratti kufnekaa! Akka seera keenyatti ammoo lamaafi sadiillee fuudhuun naa haayya mama." (Yeroo Siif Haadhiistu, Fuula:70, xiyyeeffannoon kankooti).*

"ምነው ሰለሞን እግዚአብሄርን አትፈራም እኔ እያለሁ ሌላ ሴት ማግባት ለምን አስፈለገህ?' "ኪሳራ ላይ ወደቅና! እንደ ህገ ደንባችን ደግሞ ሁለት እና ሦስት ባገባም ይፈቀድልኛል(ገፅ:70) (አፅንኦት፡ የእኔ)።

"እንደ ህገ ደንባችን" ሁለትና ሦስት እንኳ ማግባት እችላለሁ የሚለው ሰለሞን የሸሪአ ህግ መሆኑን እንገነዘባለን። የሸሪአ ህግ ተከታዮች ከሆነ ደግሞ የእስልምና እምነትን እንደሚከተሉ አያጠያይቅም።

ከዚህ ውጭ የቤተሠቦቿን ስም ብቻ በማየት የእስልምና እምነት ተከታይ እንደሆኑ መገመትም ይቻላል።

በሀረር ክፍለ ሃገር ሐራዌ በምትባል ገጠራማ ሥፍራ ከጭቁን ቤተሠብ የተወለደችው የሲንቶሊናን ሃይማኖት ስንመለከት ደግሞ ከነዚህ ሁለቱ የተለየ የምትከተለው እምነት አላት። እሱም "ዋቀፋና" (Waaqeffannaa) ይባላል። Waqqeffannaa (belief in Waaqa or sky God) የሚል ሲሆን ይሄን ደግሞ ከምታደርገውና በተለያዩ ቦታ ከምትፈፅማቸው እንቅስቃሴዋ መረዳት ይቻላል። ከዚህም ውስጥ አንዱ ሲንቶሊና ሁለተኛ ባሏን ዋሪዮን በአዲስ አበባ በራስ ጌታውን ቤት እያለች አግብታ.. ከሌላ ሴት (ፍቅር) የተወለዱትን የልጇን ልጆች የራሷ በማስመሰል በቦረና ህዝብ ባህል መስረት የስም አወጣጥ ስነስርአት (sirna Gubbisaa) ላይ የክርስትና እምነት ተከታይ እንዳልሆነችና በኦሮሞ ማህበረሰብ ባህል መሰረት የምትተዳደር መሆኗን እንመለከታለን።

*"maqaa ijoollee eenyuufi eenyu jettanii?" waariyoonis;*

*"Alkumaafi Alkitil jedhee moggaaseera." Jedhe Liidiyaanis;*

*"Ayii! Taaxiboo ciqaa! Ati ammallee hin qaroomne! Ijoollee babbareedoo kana fakkaatan maqaa fokkisaa akkasiitti moggaastaa? Lakki maqaan isaanii kana hin tahu kaffaaleefi Dubbaalee, ykn Caarewu fi Shaarewu, ykn Naadewuufi Naaxewu, ykn Laxxi'aargeefi Tsaxxiaargee, ykn Andaargeefi Addaafiree ykn Fallaqafi Zallaqaa ykn Asmaareefi Amaaree ykn Ashebbirii fi Amberbir... "jechuudhaan maqoota kan kana fakkaatan taareessan.. Garuu aka aadaa Oromoo Booranaatti kan maqaa mooggaasu dhiira malee dubartiin hin moggaastu (Yoomi Laataa?, Fuula:64).*

"የልጆቹን ስም ማን ማን አላችሁ?" ዋሪዮም፤ "አልኩማና አልክትል" ብዬ ሰይመዋለሁ" አለ። ወ/ሮ ሊዲያም (የራስ ጌታውን ባለቤት) "አይ! ታጥቦ ጭቃ! አንተ እስካሁን አልሰለጠንክም! እንደዚህ የሚያማምሩ ልጆችን እንደዚህ የሚያስጠላ ስም ትሰይማቸዋለህ? አይ! ስማቸው እንደዚህ አይሆንም። ከፍ ያለና ዱባለ ወይም ጫረውና ሻረው ወይም ናደውና ናጠው ወይም ለጥአርጌና ፀጥአርጌ ወይም አንዳርገና አዳፍሬ ወይም ፈለቀና ዘለቀ ወይም አስማረና አማረ ወይም አሸብርና አምበርብር በማለት እነዚህን የመሳሰሉ ስሞች ዘረዘሩ... ነገሩ ግን በቦረና ኦሮሞ ባህል መሰረት ወንድ እንጂ ሴት ስም መሰየም አትችልም (ገፅ፡64)።

ይህ "ትሪዕት" የተፈጠረው ደግሞ በቦረና ኦሮሞ ባህል መሰረት የስም አወጣጥ ላይ በመሆኑ እና ሌሎችን የሲንቶሊናን አጠቃላይ ህይወት በማየት የ "Waaqeffannaa" እምነት ተከታይ እንደሆነች መረዳት ይቻላል።

ሲንቶሊና የ "Waaqeffannaa" እምነት ተከታይ እንደሆነች የሚጠቁመን ሌላው ትልቁ ነገር ደግሞ ራስጌታውን ሲንቶሊናን ከሀረር ካመጡ በኋላ ከልጇ ጋር ክርስትና አስነስቷታል። ይህ ደግሞ በፊት ክርስቲያን እንዳልሆነች ወይም የክርስትና እምነት ተከታይ እንዳልሆነች አመላካች ነው።

3.2.2.2. የቤተሰቦቻቸው የኑሮ ሁኔታ

የእነዚህን ሴቶች ቤተሰቦች የኑሮ ሁኔታ ስንመለከት ሶስቱም የተለያዩ የኑሮ ሁኔታ ካላቸው ቤተሰቦች የተገኙ ናቸው የሀዊን ቤተሰቦች ስንመለከታቸው የለየላቸው ደሀ እንደሆኑ እንመለከታል

> ...Namni boolla mana fincaan ii qochisiisuu barbaade ykn dallaa jajjabeeffachuu barbaade obbo Buchaa Filate. Harkisaa gaariidha jedhu. Kanaaf gaafa hojiin jiru barruusaafi qottoo isaa gurmuu irra kaawwatee hojjecha oolee kan argate qabatee gala. Jireenyi isaan ii kun sababii hin fooyyoofneef haati manaa isaa aadde Dinsiriin farsoo naaqxee, haraqee, baaftee wal grgaaranii akka kanaan jireenya isaanii wajjin qabsoo wal qabu (Hawwii, Fuula:10)

> ... የሽንት ቤት ጉድጓድ ለማስቆፈር ወይም አጥር ለማሳጠር የሚፈልግ ሰው አቶ ቡልቻን ይመርጣሉ። ጥሩ ሙያ አለው ይላሉ። ስለዚህ ስራ ያለበት ቀን መደሻና ምሳሩን ይዞ ሲሰራ ይውልና ያገኘውን ነገር ይዞ ወደ ቤቱ ይመለሳል። ... ይህ ኑሮአቸው መሻሻልን ስላላሳየ ባለቤቱ ወ/ሮ ድንስሪ ደግሞ ጠላ በመጥመቅ፣ አረቄ በማውጣት በመተጋገዝ ከኑሮአቸው ጋር ይታገላሉ (ገፅ፡10)።

ከዚህ ተነስተን የሀዊ ቤተሰቦች ቋሚ የሆነ የወር ገቢ እንደሌላቸውና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ እንደሚገፉ እንገነዘባለን።

የሮን አባገሮ በጅማ ከተማ ውስጥ አሉ ከሚባሉት ሀብታም ቤተሰቦች የተወለደች ልጅ ናት::

Abbaagaron magaalaa Jimmaa keessaa manneetii baaburaa afur qabu. Magaalaa Finfinnee keessaa dunkaana /suuqii/meeshota gegeeddara konkolaataa qabu (Yeroon, Fuula:9).

አባገሮ በጅማ ከተማ ውስጥ አራት የእህል ወፍጮ አላቸው። ፊንፊኔ ውስጥም የመኪና መለዋወጫ ሱቅ አላቸው (ገፅ:9)።

የየሮን ውድ ልብሶች፣ የአንገት ወርቋንና የምትቀባባቸው በውድ ዋጋ የሚገዙ ቅባቶቿንና መሰል ጉዳዮችን በማየት የሮን ከናጠጠ የሀብታም ቤተሰብ እንደተወለደች መረዳት ይቻላል።

ሲንቶሊናን ስንመለከት ደግሞ ቤተሰቦቿ የአባታቸውና የአያታቸው መሬቶች ተወስዶባቸው እያላቸው እንደሌላቸው ሆነው በገዛ መሬታቸው ላይ ለሰው ተቀጥረው የሚሰሩ ያላቸውን ከብቶች ለጊዜው ገኘር አስረክበው ተጨቁነው የሚኖሩ ቤተሰቦች ናቸው ። ስለዚህ ሲንቶሊና በሀረር ክፍለ ሃገር ከጭቁን ቤተሰብ የተገኘች ልጅ ናት

> ..."Abbaankee maqaa kana akkamittiin siif moggaasaa?" "Hacuuccaan itti hammaatee barri toluufe didnaan barri dhufu siintolinna hacuuccaafi roorroon nafxanyootaan nurratti raawwatamaa jiru kun dabree barri nuuf tolu nuuf dhufaa laataa? Siintolinna laataa? Siintoluu danda'a taha hafti n urraa fudhatame nuuf deebi'a ta'a (Yoomi Laataa?, Fuula:23).

> ..."አባትሽ ይህንን ስም እንዴት ሰየሙልሽ?
> ጭቆና በዝቶበት አላልፍልህ ሲለው መጪው ዘመን በአንቺ ይቀናኝ ይሆን? በነፍጠኞች እየደረሰብን ያለው ስቃይና እንግልት፣ ዛቻ አልፎ ጥሩ ዘመን ይመጣልን ይሆን? በአንቺ ይቀናን ይሆን በአንች ልቀናኝ ይችል ይሆናል። የተወሰደብን መሬት ይመለስልን ይሆናል።

ይህ የሚያመላክተው የሲንቶሊና አባት ተጨቁኖ እንደሚኖርና የራሴ የሚለው ነገር በሙሉ ተወስዶበት በራሱ ጉልበት ከራሱ መሬት አርሶ ለሌላ ሰው እንደሚገብር ያመላክታል። ከዚህና ከመሰል ሀሳቦች ተነስተን ሲንቶሊና ከጭቁን ቤተሰብ የተገኘች ምስኪን የደሃ ልጅ ነች ማለት ይቻላል።

3.2.2.3. ከትውልድ ቦታቸው አኳያ

የሰስቱንም ሴቶች የትውልድ ቦታ ስንመለከት ከተለያዩ የኦሮሚያ ክልል መምጣታቸው እንመለከታል። ለሁሉም የመጀመሪያ የሆነችው ሀዊ የተገኘችው ከወለጋ ክፍለ ሃገር ከነቀምቴ

ከተማ ነው። የሮን አባገሮ ደግሞ በጅማ ከተማ የተወለደች ልጅ ናት'። ሲንቶሊና ደግሞ በሀረር ክፍለ ሃገር ሐራዌ ከምትባል ገጠራማ ስፍራ የተገኘች መልከ መልካም ልጅ ናት።

ከነዚህ ጉዳዮች ውጪ እነዚህ ሴቶች በውጫዊና በውስጣዊ ሰብእናቸው በጣም የሚመሳሰሉ ብቻም ሳይሆን አንድ ናቸው ቢባሉም የሚለያቸው ጉዳይ ከላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች በስተቀር ምንም አይነት የጎላ ልዩነት የላቸውም።

## 3.3. የኢሳያስ ሆርዶፋ ሴቶች ከማህበረ ባህላዊ አንፃር

### 3.3.1. ማህበረሰቡ ለሴቶቹ ያለው አመለካከት

ማህበረሰቡ ለሴቶቹ የሚሰጠውን ቦታ ስንመለከት ፊርጉሰን እንደጠቀመችው ሀዊ ገና እንደተወለደች እናቷ የሚሉት አላቸው።

> "Haati Hawwii intalli isaanii guddattee geessee sooressatti heerumtee hiyyummaa keessaa ba'uu yaadu" (Hawwii, Fuula:30).
>
> የሀዊ እናት ልጃቸው አድጋና ደርሳ ለሐብታም ድረው ከድህነት ለመላቀቅ ይፈልጋሉ (ገፅ፡30)።

ከዚህ የምንረዳው ይህ ሃሳብ የሀዊን እናት ሃሳብ ብቻ እንደማይወክልና በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የበርካታ ሰዎች አስተሳሰብ ለሴቶች የሚሰጠውን ቦታ ያመላክታል። ልጃቸውን ለሃብታም በመሸጥ ራሳቸው ከገቡበት ችግር መላቀቅ የሚፈልጉ ለራሳቸው ብቻ የሚያስቡ ናቸው። የሀዊ እናት ልጇን እንደ ከብት በመሸጥ እራሷን ደግሞ ከድህነት ለማላቀቅ የምትመኝ ለራሷ ብቻ የምታስብ ናት። ሐጂ የሱፍ ሀዊን በስተርጅናቸው ማግባት የፈለጉበት ዋና ምክንያት ስንመለከት፤

> *"Amma Bulchaafi Dinsiriin isa kamiif intala isaanii kennuuf yaadanii?" "Haajii yusuufeefikaa jedhani. Haati Latii dubbiin kun bitaa itti galee "maal Haajii Yusuufniitii qaba mitii?" jette. Maaliree kan wajjin dullooman, Qabeenya kana hundumaa kan wajjin horatte jirti. Garuu isheerraa mucaa dhabe. Sababii dahuufi dadhabdeef durba fuudhuu barbaade", jedhani (Hawwii, Fuula: 46, Xiyyeefannoon kankooti).*
>
> አሁን ቡልቻና ድንስሪ ልጃቸውን ለማን ሊሰጡ አሰቡ? ለሐጂ የሱፍ ነዋ!" አሉ። የለቲ እናት ይሄ ነገር ግራ ገብቶአቸው" ምነው ሐጂ የሱፍ ሚስት አላቸው አይደለ?" አሉ።

አዎ አብረው ያረጁ፣ ይሄን ሁሉ ሀብት አብራው ያፈራች አለች። ነገር ግን ከእርሷ ልጅ አጣ። ልትወልድለት ስላልቻለች ልጃገረድ ማግባት ፈለገ" አሏት (አፅንኦቱ የእኔ)።

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ሐጂ የሱፍ ያጡት ልጅ ብቻ ነው። ስለዚህ የሚፈልጉት ሀዊን ሳይሆን ልጅ ማግኘት ላይ ነው ትልቁ አላማቸው። ምክንያቱም እድሜያቸውን ራሱ ስንመለከት ከ70 ዓመት በላይ እንደሆነ ነው። ስለዚህ ሀዊ ከገበያ እንደሚሸመት ዕቃ ተገዝታ ልጅ እንድትወልድ ነው። ቤተሠቦቿ ደግሞ ልጃቸውን በመሸጥ ከድህነት መውጣት አላማቸው አድርገዋል። ከቤተሠቦቿም ሆነ እሷን ለማግባት ከሚዘጋጁት ቤተሰቦች ለሀዊ ህይወት የሚያስብ አንድም የለም። እሷ እንደ እቃ ተቆጥራለች። ምክንያቱም ሁለቱም ቤተሠቦች እሷን የፈለጉበት ምክንያት ከርሷ በሚያገኙት ጥቅም አይን እንጂ ለሷ የተሰጣት ቦታ የለም። እንዳውም ከሰው ተራም አልተቆጠረችም። ሐጂ የሱፍ ሊሞቱ የደረሱ ሽማግሌ ተብለዋል። እኚህ ሽማግሌ የመሞቻቸው ቀን እየተቃረበ ስለሆነ ሃብታቸውን ሊያስወርሱ የሚፈልጉት ገና ለሚወለድ ልጅ ነው ማለት እንችላለን። ሀዊ ልጅ ከወለደች በኋላ ልትባረርም ትችላለች። ምክንያቱም የገዛ የሐጂ የሱፍ ባለቤት ናት እንዳንል የመጀመሪያ ባለቤታቸው ይሄን ሁሉ ሃብት አብራው ያፈራች እያለች ሀዊ ይሄን ሃብት ልትካፈል አትችልም። ስለዚህ ሀዊ ልጅ ብቻ እንድትወልድ የተፈለገች ናት እንጂ ለምንነቷና ለማንነቷ ቦታ አልተሰጠም።

"Ayii.. yaa Latuu koo utuu murtiin koo fi fedhiin koo fudhatama qaba ta'ee silaa dhaabbii kootti akka horii nan gurguran ture" (Hawwii, Fuula:54).

"አይ... የእኔ ለቲ የእኔ ሃሳብና ፍላጎት ተቀባይነት ቢኖረው ኑሮ በቁሜ እንደ ከብት አይሸጡኝም ነበር" (ገፅ፡ 54)።

ለሀዊ ሃሳብና ፍላጎት ምንም አይኔት ቦታ እንዳልተሰጠ የሚያመላክት ነው። እሷም እንደምትለው ለፍላጎቴና ለማንነቴ ቦታ ቢሰጠው ኑሮ እንደከብት በቁሜ አይሸጡኝም ነበር። ትላለች። ይሄ ደግሞ ማህበረሰቡ ለሴቶች የሚሰጠውን ቦታ የሚያመላክት ነው። ከዕቃ ያልዘለለ።

የሮንን ስንመለከታትም ገና ሰለሞን ሊያገባት በፈለገበት ሰዓት ለራሱ የሚላቸው ነገሮች አሉት፡-

> *"Amma utuun kana argadhee jaartii sanallee hin barbaadu. Qabeenyi kunillee kan koo ta'a... Intala bareedduu qabeenya*

*ishee wajjjin argachuun carraa guddaadha" jedha. Yaadasaan (Yeroon Siif Haadhiistu, Fuula: 11).*

"አሁን ይችን ባገኝ ያችን አሮጊት እንኳ አልፈልግም። ይሂ ሀብትም የእኔ ይሆናል ... ። የምታምር ልጅ ከነ ሀብቷ ማግኘት ትልቅ ዕድል ነው" ይላል በሃሳቡ (ገፅ፡ 11)።

የሰለሞን ትልቁ ዓላማ የሮንን ማግኘት ላይ አይደለም። በፍቅር ስም ተጠግቶ የአባገሮን ሀብት መውረስ ነው።

*"Solomoon akeekisaa inni guddaan akka fiixaan isaa bahe mirkaneeffate yerooniin fuudhee qabeenya sana hundaa dhaalee, gooftaa ta'ee akka jiraatu hubate" (Yeroon, Fuula:16).*

ሰለሞን ትልቁ ዓላማው እንደተሳካለት ተገነዘበ። የሮንን አግብቶ ይህን ሁሉ ሀብት በመውረስ ንጉስ ሆኖ እንደሚኖር ተረዳ።

ሰለሞን ገና የሮንን ሳያገባ በአዕምሮው ውስጥ የሚመላለሰው ስለሚያገኘው ሃብታቸው እንጂ ስለ እሷ ማንነት አልተጨነቀም። ማንም ትሁን ምን የእሱ ዓላማ ሃብት ላይ ነው። እሷን ካገባ ይሂ ሁሉ ሃብት ወደ እርሱ እንደሚዛወር የተረዳው ሳያገባት ነው። ይሂ የሚነግረን ደግሞ ማህበረሰቡ ውርስንና ንብረት የማስተዳደር ብቃትን አስመልክቶ ለሴቶች ያለውን ዝቅተኛ ግምት ነው። የየሮን አባት ገና ሰለሞን የሮንን አግብቶ ወር ሳይሞላው ነው ዱሮ የሮን የምታስተዳድረውን ንብረት ሰለሞን እንዲያስተዳድር መመሪያ የሰጡት።

*"....;Sababii kana ta'eef yerooniifi Solomooniin Waamanii eebbisanii haala qabeenya saaniitti bulchanis qajeelfama kennanii gara Finfinneetti deebi'an" (Yeroon, Fuula: 42).*

...;በዚህም ምክንያት የሮንንና ሰለሞንን በመጥራት መርቀው ንብረታቸውን የሚያስተዳድሩበትን መመሪያ ሰጥተውአቸው ወደ ፊንፊኔ ተመለሱ (ገፅ 42)።

አባገሮ የሮን ንብረቱን እንድታስተዳድር ፈልገው ቢሆን ኑሮ መመሪያ መስጠት አያስፈልጋቸውም ነበር። ምክንያቱም ዱሮውንም ስታስተዳድር የቆየች እሷ ስለሆነች ነው። የአባቷ ንብረት በፊት እሷ እያስተዳደረች እያለች ተበዝብዞ ቢሆን ኑሮ ለሰለሞን ቢሰጡም እውነት አላቸው ንብረታቸውን ማስተዳደር አልቻለችም ማለት ይቻል ነበር። ነገር ግን የሮን ለአባቷ ንብረት እና ለስሟ ተጠንቅቃ የምትሠራ በጅማ ከተማ ውስጥ በሚገኙ ሌሎች ሰዎች የተመሰከረላት ጨዋ ልጅ ሁና እያለች ነው አባ ገሮ ለሰለሞን ሃላፊነቱን የሰጡት። ይሂ ደግሞ ከመጀመሪያውም ማህበረሰቡ ለሴቶች የሚሰጠውን ዝቅተኛ ግምት ይጠቁመናል። አባቷ

የወለዱትን ልጃቸውን ትተው እምነታቸውን በልጃቸው ባል ላይ ያደረጉበት ዋናው ምክንያት ስናሰብ ሰለሞን ወንድ ስለሆነ ብቻ ነው። ከዚህ ተነስተን ለወንድና ለሴት የሚሰጠውን ክብርና ቦታ መገመት አያዳግትም።

ሲንቶሊና የ8ኛ ክፍል ተማሪ እያለች "የሴት ልጅ ትምህርት ከምን ያደርሳል?" በሚል በቤተሠቦቿ ፍቃድ መሠረት ትምህርቷን አቋርጣ ያደኖ ጃራ ወለቡማን እድታገባ ተደረገች።

*Obbo Jaarraan dulloomee mana oolu yeroo jalqabu" utuu hin du'iin ilmikoo fuudhee ilmasaa ijaan ilaaluunqaba" jedhee durba bareedduu ganda qalaadi irra jiraatan Harawwee keessa barbaachisee fuusise (Yoomi Laataa?, Fuula:11; sararri kan kooti).*

አቶ ጃራ አርጅተው እቤት መዋል ሲጀምሩ ከመሞቴ በፊት ልጄ አግብቶ ወንድ ልጁን በዐይኔ ማየት አለብኝ በማለት የምታምር ልጅ ከሚኖሩበት አካባቢ ከሐራዌ አስፈላጊው ዳረው (ገፅ፡ 11)፤(መስመር ከራሴ)።

ሲንቶሊና የተፈለገችበት ምክንያት ልጅ እንድትወልድ ነው። አቶ ጃራ ወለቡማ እድሚያቸው ስለገፋ የልጃቸውን ልጅ በዐይናቸው አይቶ መሞት ፈለጉ። ሲንቶሊና መውለድ የማትችል ሴት ብትሆን ኑሮ የሚያጋጥማትን ችግር መገመት ቀላል ነው። እዚህም ጋር ለሲንቶሊና ዋጋ ሲሰጣት አንመለከትም፤ ይልቁንም አቶ ጃራ ለማየት የጓጉት የልጃቸውን "ወንድ" ልጅ ነው። ከዚህ አባባላቸው የምንገነዘበው ሲንቶሊናም ወንድ ልጅ እንድትወልድ እንጂ ሴት ልጅ አይደለም። አሁንም ሴት ልጅ ብትወልድ የራሷም ተቀባይነት ከበፊቱም ይቀንሳል። የሲንቶሊናም ቤተሠቦች ለልጃቸው ዋጋ አልሰጡም እንዲያውም የሴት ትምህርት ከምን ያደርሳል በሚል ነው ትምህርቷን አቋርጣ እንድታገባ የተገደደችው። ከዚህ ተነስተን ማህበረሰቡ ለሴቶች የሚሰጠውን ቦታ መገመት እንችላለን። እንኳን ተወልጃ ላሉ ሴቶች ገና የሚወለደውም ልጅ ወንድ እንዲሆን ሙሉ ምኞታቸው ነው። ሴት ብትሆን ያው መቼስ ምን ይደረጋል በሚል የሚቀበሉ ካልሆነ ደስተኞች እንደማይሆኑ ከአነጋገራቸው በይፋ ይነበባል።

*Siintolinnaan akkuma yeroo kaanii haala Qanyaazimachi waan beektuuf akkafedhiisaatti cal jettee ajajamti malee fedhii isaa hin mormitu. Ammas fedhii sagaagalummaa isaa kana dirqiidhaandhammata. Itti hadhaawa garuu maal haagootuu? Filannaagara biraa hin qabdu (Yoomi Laataa?, Fuula:12).*

ሲንቶሊና እንደሌላ ጊዜዋ የቀኝ አዝማችን አኳኋን ስለምታውቅ ዝም ብላ ትታዘዛለች እንጂ ፍላጎቷን አትቃወምም። አሁንም የወሲብ ፍላጎቱን በግድ ይፈፅማል። ይመራታል ነገር ግን ምን ታደርግ ሌላ አማራጭ የላትም(ገፅ፡ 12)።

እዚህ ላይ ሲንቶሊና በገዛ አካሏ ላይ እንኳ መብት እንደተነፈገች ነው የምንመለከተው። ቀኝ አዝማች የራሳቸውን ፍላጎት ብቻ ነው የሚጠብቁት። እሷ ፍላጎት እንዳላትና እንደሌላትም አይገነዘቡም። ይህ ደግሞ ከግኡዝ ጋር ካልሆነ በስተቀር ህይወት ካላቸው ነገሮች ጋር አያስልፉትም። ይህ ሃሳብ ደግሞ የቀኝ አዝማች ግዛቸው ሃሳብ ሆኖ በቀረ የመላው ማህበረሰቡ ሃሳብም ነው። በተለይም ወንዶች ለሴቶች የሚሰጡትን ዝቅተኛ ግምት ያመላከተ ነው።

Marry, Anne Ferguson, በስነ ፅሁፍ ውስጥ ሴቶች በሰባት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ ብላ ከከፈለቻቸው በኋላ ራሮታዊት ሴት (Submissive Women) በሚለው ርዕስ ስር እንደምታስቀሚጠው፡-

> *.. a women has no right either to her own body or its fruit; her children and she her self are equally the property of her lord and master. Like children, women had no choice but to submit to their husbands will,... (Ferguson, 1977:17)* ብላለች።

ሰው ከሱቅ ዕቃ ገዝቶ የገዛውን ዕቃ ደግሞ እንደፈለገ ቢያደርግ የሚጠይቀው የለም። ሲፈልግ ይጠቀምበታል፣ ሲፈልግ ደግሞ ከድኖ ያስቀምጣል። ዕቃው በራሱ አንደበት ተናግሮ እንደዚህ አድርገኝ እንደማይል ሁሉ ሲንቶሊናም በራሷ አንደበት ተናግራ አንደዚህ አድርገኝ፣ይህ ደግሞ የማልፈልገው ነገር ነው ብላ ለመከራከር መብት ያልተሠጣት፣ ፀጥ ለጥ ብላ ከመገዛት ውጭ ሌላ አማራጭ የሌላት ሴት ናት። ይሄ ደግሞ ማህበረሰቡ ለነዚህ ሴቶች የሰጠውን ማህበረ ባህላዊ ደረጃ ይጠቁመናል። ሲፈልግ ማግኘት እንደሚችል፣ ካልፈለገ ደግሞ ያስቀመጠበት ቦታ የሚያገኝ ከዕቃ ያልዘለለ ቦታ እንደተሰጣቸው እንመለከታለን።

ሲንቶሊና በራስ ጌታውን ዘንድ በሚስጥር ለልጅ ብትፈለግም ፌርጉሰን እንደጠቆመችው በራሷ ልጅ ላይም መብት የሌላት ሴት ናት፡-

> *.. Siintolinnaa irraa mucaa godhachuu hin dandeenye. Sandaaba akka ilma isaanitti qanansiisanii guddisaa jiru. Siintolinnaafi sandaabaa kiristinnaa kan kaasan gaafa Goorgisii waan ta'eef maqaa sandaabaa Haayile Goorgis Geetawun jedhanii moggaasan (Yoomi Laataa?, Fuula: 46).*

ከሲንቶሊና ልጅ መውለድ አልቻሉም። ሰንዳባን እንደ ልጃቸው ተንከባክበው እያሳደጉት ነው። ሰንዳባንና ሲንቶሊናን ክርስትና ያስነሱት የጊዮርጊስ እለት ስለሆነ የሰንዳባን ስም ኃይለጊዮርጊስ ጌታውን ብለው ሰየሙት (ገፅ፡ 46)።

አባቷ ያደኖ ጃራ በኦሮሞ ባህል መሰረት የልጁን ስም ሳንዳባ ብሎ ሰይመውታል። እነዚህ ግን አባት የሌለውን ልጅ አግኝተው እንደፈለጉ ወደ ፈለጉት የቀየሩበት ምክንያት እናቷ ምንም ነገር ልታደርግ ስለማትችል ነው። የገዛ ልጇን የእኔ አይደለም እያለች እድታሳድግ፣ ማንነቱንና ማንነቷን እንዲቀይሩ ጥረት እያደረጉ ነው። ይህ ደግሞ ሴቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ምን ያህል እንደሚናቁ ያመላከተ ነው። የራሱን ስም፣ የአባቱንና የግል ሃይማኖቱን ትቶ በግድ ሳይወድ ወደ ተፈለገው ዓላማ ማስቀየር ማለት ሲንቶሊና እንደተባለውም ልጅ ለመውለድ ብቻ እንጂ ሌላ ተግባር እንደሌላት ያመላከተ ነው።

በአጠቃላይ ሲታዩ ሴቶቹ የራሳቸው መብት የተነፈጉ፣ የፈለጉትን ነገር የመናገር እና የመምረጥ ዕድል የሌላቸው፣ ቢናገሩም ሰሚ የሌላቸው፣ ለመብታቸው ለመከራከር ከወንዶች እኩል ለመሰለፍ ያልታደሉ፣ ይሁን እንጂ የተነሱለትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ወደ ኋላ የማይሉ ቆራጦች ሆነው ነው የተሳሉት። ይህ ደግሞ በእውኑ ዓለም ውስጥ የሚንፀባረቀውን የጀግና ሴቶች ህይወት ጋር ይመሳሰላል። በድሮ ጊዜ ሴቶች ማንን እንደሚያገቡ እንኳ የሚያውቁት የሚዳሩበት ጊዜ ከተቃረበ ነው። እሱንም ሰዎች ሲያወሩ ወይም ከጓደኞቿ ካልሰማች በስተቀር የመጠየቅም ሆነ እኔ እሱን አላገባውም የማለት ዕድል እንደለላቸው ይታወቃል። ከዚህ ተነስተን ማህበረሰቡ ለሴቶቹ የሚሰጠው ግምት ከፍ ካለ ከጌታና ሎሌ ያልዘለለ ነው ማለት እንችላለን።

## 3.3.2. ሴቶቹ ለማህበረ ባህላቸው ያላቸው አመለካከት

እነዚህ ልቦለዶች በተፃፉበት ወቅት ጋብቻ በሁለቱም ቤተሠቦች መፈቃቀድ ላይ ብቻ የተመሰረተ ነበር። ወላጆች በሀብትና በክብር ይመጥኑናል የሚሏቸውን ሰዎች ያለ ልጆቹ ፈቃድና እውቅና የሚመርጡበት ብሎም የሚድሩበት ጊዜ ነበር። አንዳንዶች ደግሞ የዛሬ ኑሮአቸውን ብቻ ከግምት በማስገባት የሰውየውን ሀብት ብቻ በማየት በገንዘብ ተደልለው ልጆቻቸውን እንደ ዕቃ የሚሸጡ የሆድ አምላኮች ይኖራሉ። እነዚህ ሴቶች ደግሞ በዘመኑ የነበሩ ወጣት እንደመሆናቸው መጠን ከተለያዩ ቤተሠቦች የተወለዱ ናቸው። አንዳንዶቹ ከደሃ ቤተሠብ የተወለዱ እንደ ሀዊ ቡልቻ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ከለየለት ሃብታም እንደ የሮን አባገሮ ሌሎች ደግሞ ከጭቁን ቤተሠብ የተወለዱ እንደ ሲንቶሊና አይነት ናቸው።

ሀዊ ቤተሠቦቿ የመረጡላትን "ትዳር" ትዳር ከተባለ እምቢ ብላ ሰርጓ ከደረሰ በኋላ ከቤት ጠፍታለች፤ የዘመኑን አስተሳሰብና እምነት ተቃውማለች፤ ጥላም ወጥታለች። ከቤተሠቦቿ ፍቃድና እውቅና ውጪ "ለእሷ አይገባም"፤"አይመጥናትም"፤ እከኩን ሊያወርሳት ካልሆነ በስተቀር የተባለው ለቲ ጅሬኛን መጀመሪያ አብሮ አደጓ እንደመሆኑ መጠን እንደ ጓደኝነት የተጀመረው ፍቅር በኋላም እስከ መጨረሻ በትዳር አብራው ለመኖር ወስናለች።

ሀዊ ይህንን የማህበረሰቡን ባህልና ወግ ትቃወምና ትጣስ እንጂ ሌላውን ህብረተሰቡ የተቀበለውን ወግና ልማድ ተቀብላ ተግባራዊ አድርጋለች። አንዱ ምሳሌ የሚሆነን ከጋብቻ በፊት ምንም አይነት ግንኙነት አልፈፀመችም። እንደማህበረሰቡ ወግና ልማድ ለመጋባት ጓደኛዋን እስከ መጨረሻው በታማኝነት ጠብቃለች። በማህበረሰቡ ወግና ልማድ መሰረት ሴት እና ወንድ አብረው መኖር የሚችሉት ከተጋቡ ብቻ መሆኑን ጠንቅቃ ስለምታውቅ ምንም እንኳን ሰርግ ለመሰረግ ሁኔታውም ባይፈቅድላቸውም እስከ ቀኑ ድረስ ሁለቱም ንፅህናቸውን ጠብቀው ለመቆየት በመወሰን ተግብራለች። ከማህበረሰቡ ባህልና ወግ ውጪ እንድትወጣ የሚያደርጓት ብዙ ነገሮች ቢፈራረቁባትም አንድም ጊዜ ያልተበገረች መከበር የሚገባውን የማህበረሰቡን ባህል አጥብቃ ያከበረች ጀግና ናት።

በራሴ ነገር ውስጥ ማንም አይገባም የሚል መፈክር ያነገበች የሮንም ከማህበረሰቡ ፈቃድና እውቅና ውጪ የራሷን ባል ሰለሞንን ከመረጠች በኋላ በማህበረሰቡ ወግና ባህል መሰረት ለቤተሠቦቿ ሽማግሌ እንዲልክ አስደርጋለች። በማህበረሰቡ ወግና ባህል መሰረት ወደ ሴቷ ቤት ሽማግሌ መላክ ያለበት ወንዱ መሆኑን ጠንቅቃ ስለምታውቅ ነው ሰለሞንን ሽማግሌ እንዲልክ ያስገደደችው።

"ልጅ ያቦካው ለእራት አይበቃም" በሚል ፈሊጥ በቤተሠቦቿ አስገዳጅነት ከ8ኛ ክፍል ትምህርቷን አቋርጣ ለማታውቀው ሰው ሲድሯት "እሺ" ብላ የተቀበለችው ሲንቶሊና ብቻ ናት። ሲንቶሊና በማህበረሰቡ ወግና ባህል መሰረት የቤተሠቿን ሃሳብ ሳትቃወም ከተገበረች በኋላ ህይወት እንዳሰበችው አልሆን ሲላት ትዳሯን ለቃ ከኮበለለች በኋላ ግን በራሷ ፍቃድ የራሷን ባል መርጣ አግብታለች። የራሷን ባል መርጣ ስታገባም የማህበረሰቡን ወግና ባህል ጠንቅቃ ያወቀችና የምታከብርም ሁና ተገኝታለች።

በአጠቃላይ ሲታዩ እነዚህ ሴቶች መከበር ያለበትን የማህበረሰቡን ወግና ባህል የሚያከብሩ፣ መከበር የለበትም የሚሉትን ደግሞ የሚቃወሙ አስተዋዮች፣ ቆራጦች፣ ለነገ የሚኖሩ

ለሆዳቸው ያላደሩ ጠንካሮች፣ ታማኞችና የሰናይ ምግባራት ባለቤቶች ናቸው። በዚህ ምግባራቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታወቁ፣ ቀና አመለካከት ያላቸው ሴቶች ናቸው።

### 3.4. ዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ከሌሎች ገፀባህሪያት ጋር ያላቸው ግንኙነት

እነዚህ ዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት አብሮአቸው ከተሳሰሉት ሌሎች ገፀባህሪያት በተለየ ሁኔታ እንዲታሰቡና አሁን ያላቸውን አስተሳሰብ፣ መረዳት፣ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተፅዕኖ ካደረሱባቸው ነገሮች መካከል አካባቢ፣ ትምህርት፣ ልምድ፣ ሃይማኖት፣ የቤተሠብ ሁኔታ፣ ተሰጥኦ፣ የደራሲው የግል ፍላጎት፣ ገቢ (income)፣ የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ። አንድ ገፀባህሪ አብረው ከተሳሉት ሌሎች ገፀባህሪያት ወጣ ብሎ እንዲታይና እንዲሰማ የሚያደርገው የራሱ የሆነ ምክንያት ሊኖረው ቢችልም አንዳንዴ በገሃዱ ዓለም ያለውን እውነታ ለማንፀባረቁ አልፎ አልፎ ደግሞ ደራሲያን ለፈለጉት ዓላማ ግብ መችነት ሲሉ እራሳቸው የፈለጉት ኑሮ እንዲኖሩ ሊያደርጉ ይችላሉ። ስለዚህ በእነዚህ ገፀባህሪያት ላይ ይሄኛው ነገር የበለጠ ተፅዕኖ ፈጥሮአል ብለን ለመናገር የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት አኗኃን ከሌሎች ገፀባህሪያት ጋር ጎን ለጎን ማየቱ አስፈላጊ ነው።

#### 3.4.1 ሀዊ እና አማረ

አማረ በሲዊዲን ሃገር የምህንድስና ትምህርት ተከታትሎ ከጨረሰ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ በመስራት ላይ የሚገኝ የጎንደር ተወላጅ ልጅ ነው።

> Amaareen of tuulaa Amaaraati "Inee Amaaree qabraarraa Gonderee" ofiin jedha. Saboota isaan kaan namatti hin hedu. Aadaan Afaan amantiifi biyyi gaariin kan saba isaa qofaa akka ta'etti dubbata (Hawwii, Fuula: 165)
>
> አማረ ትምክተኛ አማራ ነው። "እኔ ቀብራራው ጎንደሬ" እያለ ራሱን ይጠራል። ሌሎችን ብሔር ብሔረሰቦች እንደሰውም አይቆጥራቸውም። ጥሩ ባህል፣ ቋንቋ ሰውና ሃገር የብሔረሰቡ ብቻ እንደሆነ ይናገራል (ገፅ፡ 165)።

የአማራን ብሔር ወክለው የቀረበው አማረ በዘመኑ ካሉት ሰዎች አለ የሚባል "ምሁር" ቢሆንም በሰው ልጅ እኩልነት የማያምን በአንድ ብሔር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ባህል፣ የበላይነት የሚያምን ጠባብ ገፀባህሪ ነው።

አማረ እንደዚህ ያለ አመለካከት ሲኖረው ሀዊ ግን ጥሩ ቋንቋ፣ ባህል፣ ብሔር፣ ሃይማኖት የሚባል ከእግዚአብሔር ዘንድ ሳይሆን እኛው እዚችሁ ምድር ላይ የምንፈጥረው ጉዳይ ነው

ትላለች። እግዚአብሔር ሲፈጥረን "የሰው ልጅ" የሚል አንድ ስም ብቻ ሰጠን መናናቅና መናቆር ያመጣነው እኛው የሰው ልጆች ነን የሚል አስተሳሰብ አላት።

አማረ በሰዊድን ሃገር በቆየበት ጊዜ ከሀዊ ፍቅረኛ ለቲ ጅሬኛ ጋር አብሮ ስለነበሩ እሱ ቀድሞ በመምጣት ስራ ሲጀምር ለቲ ግን ትምህርቱን ስላልጨረሰ ወደ ሃገር ቤት አልተመለሰም። ይሄን አጋጣሚ ተጠቅሞ አማረ ለቲ እና ሀዊን ለማጣላት ያላደረገው ጥረት የለም። ነገር ግን ገና ከልጅነቷ ቀድማ "የበሰለች" የተባለላት ሀዊ የአማረን ወሬዎች አትቀበልም ነበር። "እኔ ለቲን እንደራሴ አምነዋለሁ" ትለው ነበር።

ኢንጂነር አማረ በሀዊ ላይ ከሚሸርበው ሴራ ውጪ በሄደበት ሁሉ የኦሮሞን ስም የሚያንቋሽሽ ነገር እንጂ አይጠቀምም። ነገር ግን ከደለሳ መርጋ ማለትም የሀዊ ፍቅረኛ የአጎት ልጅ ከሆነውና ለአማረ የቅርብ ጓደኛ የሚባለው ደላሳ ለአማረ ምክር ሰጥቶት ነበር። እናንተ የተማራችሁ ያወቃችሁ ስለሆናችሁ ያልተማሩት አባቶቻችሁ የሚሉት ለምን መልሳችሁ እንደበቀቀን ታስተጋባላችሁ? ሰው ከተማረ ማሰብ ያለበት እንደ ባለ አእምሮ ነው በማለት አማረን የመከረ ቢሆንም አመረ የተቀበለ አይመስልም። ለዚህ ነው ሀዊ የአማረን ሁኔታ ተረድታ ለሰው ልጅ የሚገባው ከሆነ አንድ ቃልም በቂ ነው የምትለው።

እዚህ ላይ የአማረንና የሀዊን የትምህርት ደረጃ ስንመለከት በጣም ደራራቃሉ። በአስተሳሰብ በኩል ደግሞ ሀዊ ከእርሱ የተሻለ ሃሳብ ስታነሳ እንመለከታለን። ከዚህ ተነስተን ትምህርት በአንድ ሰው ግላዊ መረዳት ወይም አመለካከት ላይ ከሚያመጣው ለውጥ ይልቅ የሰው ልጅ ይዞት የሚወለደው የመረዳት አቅም፣ የበለጠ ተፅዋ ሊያደርሱ ይችል ይሆን? ያሰኛል። በተመሳሳይ ሁኔታ በትምህርት በኩል ከገፉት አንዱ "ለሙ በንቲ" ከክፍለ ሀገር ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከፍተኛ ትምህርት ከጨረሰ በኋላ የባንክ ሰራተኛ የሆነ ወጣት ነው። ነገር ግን አባቱ ያወጣለትን ስም አፍሮበት 'ከለሙ በንቲ' ወደ 'ዓለሙ ባንቴ' ቀይሮ ሲኖር እንመለከታለን። ከዚህም የተነሳ ሲሞት አባቱ ውርስ አልባ ይሆናሉ። እነዚህንና መሰል ጉዳዮችን ስንመለከት እውነትም የሰው ልጅ ይዞት የሚወለደው የመረዳት አቅም ከየትኛውም የውጭ ተፅዕኖ የበለጠ ጉልበት አለው ያሰኛል።

3.4.2. ሀዊ እና ሌሎች

ሀዊ አዲስ አበባ ውስጥ ከምታውቃቸው ሴቶች ጋር ተከራይታ ስትኖር ድሮ በነቀምት ከተማ የሚታውቅ ልጅ ማርታን አግኝታ ልትቀርባት ስትፈልግ እሷ ግን ከሀዊ ጋር መተዋወቁን

አልፈለገችም። ምክንያቱም ማርታ የሌላትን ማንነት፣ ስብእና ተላብሳ መኖር የወሰነች ልጅ ናት። እንደዚህ አይነት አመለካከት ደግሞ ለሀዊ አይዋጥላትም።

..."Oromoo ta'uun koo yoo natti dammaqame namni natuffata, ulfina duratti hosteelicha keessatti qabu nadhabsiisa" jettee waan yaadduuf Hawwiin baay'ee itit gadditi (Hawwii, fuula: 149).

..."ኦሮሞ መሆኔ ከተነቃብኝ ሰው ይንቀኛል፣ በሆስቴሉ ውስጥ ያለኝን የበፊቱን ክብር ያሳጣኛል" ብላ ስለምታስብ ሀዊ በጣም አዝናባታለች።

ማርታ በሆስቴል ውስጥ ተከራይታ የምትኖር ብትሆንም አንድም ቀን "ከኦሮሞ ሀገር" መጣሁ የሚል አነጋገር ከአንደበቷ ወጥቶ የማያውቅ በማንነቷ የምታፍር ልጅ ናት። ከዚህ ሃሳቧ ተነስታ ሀዊ እንዲህ ስትል ተሰምታለች።

"Namni maaliif of tuffataa? Maaliif sabummaa isaatti qaana'aa? Balleessaa naamusaa nama qaanessu yoo hojjete qaana'a malee oromummaan isaa eenyummaa isaati (*Hawwii*, Fuula: 149).

ሰው ለምን ራሱን ይንቃል? ለምን በማንነቱ ያፍራል? የሚያሳፍር የሥነ ምግባር ሥራ ከሰሩ ያሳፍራል እንጂ ኦሮሞነቱ ማንነቱ ነው (ገፅ 149)።

"በማንነት እንዴት ይታፈራል?" የምትለው ሀዊ በልምድም ሆነ በትምህርት ደረጃ ከማርታ ታንሳለች። በትምህርት በኩል ማርታ ከሀዊ በፊት ናት። ብዙ ስቃይና ውጣ ውረዶችን በማሳለፍም እንዲሁ ትቀድማታለች። በአስተሳሰብ ግን ሀዊ ቀዳሚ ናት። አካባቢ ተፅዕኖ ፈጥሮባቸዋል እንዳንል ደግሞ ሁለቱም ያደጉት በአንድ ከተማ ውስጥ ነው። እንዲሁም አዲስ አበባ ውስጥም አንድ አይነት ህይወት እየመሩ የሚኖሩ ልጆች ናቸው። የሚለያያቸው ለህይወት ያላቸው ግላዊ አመለካከታቸው ነው ሊያስብል ይችላል።

የአቶ አያና ልጅ መሃንዲስ ጫላም ቢሆን የሀዊን ጠንካራ አስተሳሰብ መስክሯል። ሀዊ ስትታይ ከክፍለ ሀገር የመጣች ብትመስል ያመነችበትን ነገር ለመፈፀም ወደ ኋላ የማትል ጠንካራ ልጅ መሆኗን እሷን የግሉ ለማድረግ በሞከረበት ጊዜ ተገንዝቧል። ስለዚህ የሀዊ ቀና አመለካከት የሰናይ ምግባር ባለቤት መሆኗ ከተራ የሆስቴል ነዋሪዎች እስከ ትላልቅ ሰዎች ተመስክሮላታል። ለዚህ ደግሞ እንደምክንያትነት የሚጠቀሰው ገና ከመጀመሪያው በእድሜ

ከሚበልጧት ልጆች ቀድማ የበሰለች አስተዋይ ልጅ ነች የተባለች ነገር ለዚህ አመለካከቷ አስተዋፅኦ አበርክቷል። ይዛ የተወለደችውን አመለካከቷን እስከ መጨረሻው አንፀባርቀዋለች።

### 3.4.3. የሮን እና ሰለሞን

ሰለማን በጅማ ክፍለ ሀገር ሊሙ ሲንጡ ወረዳ ውስጥ አሉ ከሚባሉ ሀብታም የቡና ነጋዴ ቤተሠብ የተገኘ ልጅ ነው። ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ለማንነቱ ደንታ ቢስ የሆነ እና ትልቁ ዓላማው አድርጎ የተነሳው ደግሞ "ሀብት በየት ይገኛል?" የሚለውን እንጂ ለማንነቱና ለቤተሰቡም ክብር የማይጨነቅ ልጅ ነበር። በዚህ ፀባዩና አመለካከቱ ከአባቱ ጋር መስማማት ስላልቻለ አባቱ፣ "የእኔ ልጅ አይደለህም" ስላለው ከሚማርበት አጋሮ ከተማ ወደ ጅማ ከተማ ጠፍቶ ሄደ።

"Maqaa abbaan saa isaaf moggaasaan Suliimaan ture. Solomoon jedhee kan of maggaase isuma" (fuula:28).

"አባቱ ያወጡለት ስም ሱለማን ነበር። ሰለሞን ብሎ የለወጠው እራሱ ነው" (ገፅ 28)።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነበር በጅማ ከተማ ውስጥ ማንነቱን ቀይሮ በመኖር ላይ እያለ ከየሮን ጋር የተዋወቀው። ሰለሞን "ካለው ተወለድ ወይም ካለው ተጠጋ" (ገፅ፡28)። የሚል የህይወት ፍልስፍና አለው። ይህ አስተሳሰቡ ደግሞ ገና ከልጅነቱ በአዕምሮው ውስጥ ተቀርፆ ያደገ ሲሆን እስከ እለተ ሞቱም ድረስ ከዚህኛው አስተሳሰቡ ሳይፀዳ ነበር የሞተው። የየሮንንና የሰለሞን አኳኋን ስንመለከት ሁለቱም ከሀብታም ቤተሰብ የተገኙ ልጆች ናቸው። በልጅነታቸው የሚያገኙት ከመጠን ያለፈ እንክብካቤ ሰለሞንን ወዳልሆነ አመለካከት እንዲያመራ ሲያደርገው የሮን ላይ ግን አልሰራም። ሰለሞን ለወር የሚሰጠውን ብር በሳምንት ጨርሶ ከእናቱ ይቀበላል (ገፅ፣ 26)። በመጀመሪያ ይዞት ከተወለደው ግላዊ አመለካከቱ ጋር የሚያገኘው ገንዘብ፣ ያፈራዋቸው ጓደኞች (peer group) በሰለሞን ላይ ተፅዕኖ ፈጥረዋል። በየሮን አመለካከት ተፅዕኖ አድርጓል ብለን የምንናገረው ደግሞ በመጀመሪያ ይዛ የተወለደችው የመረዳት አቅም ብቻ ነው። ገና ከመጀመሪያውም አስተዋይ ልጅ ነበረች። (Khera, 2001) እንደሚለው በሰው ልጅ ግላዊ መረዳት ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ሊፈጥር የሚችለው ነገር ውስጣችን ያለው ነገር ነው ይላል።

እነዚህ ገፀባህሪያት ላይ ሁለት ነገሮች እንመለከታለን፣ ገቢ፣ አካባቢ፣ ጓደኛ (peer pressure) ሰለሞን መጀመሪያውም ይዞት የተወለደውን ግላዊ አቋሙን ሲያባብሱት በየሮን

ላይ ግን ብዙም ለውጥ አላመጣም። ምክንያቱም የሮን በጓደኞቿ ግፊት በሰለሞን ፍቅር ውስጥ ትግባ እንጂ መጀመሪያውም ይዛ የተወለደችውን አመለካከቷን አልቀየረችም። ለሰው አዛኝ፤ ቅን፣ ታማኝ፣ ሰዎችን በእኩል አይን የምትመለከት አስተዋይ ልጅ ናት። ይሄንን አመለካከቷን እያሳደገች የመጣችበት ሁኔታም እንመለከታለን።

"Nama sirritti hin beeknatti of kennuun badisa guddaarratti nama gata. Kan Solomoon fakkeenya gaarii naa ta'uu danda'a" (Fuula: 105).

"በደንብ ለሚያውቁት ሰው ራስን አሳልፎ መስጠት ለጥፋት ሊዳርግ ይችላል። የሰለሞን ጥሩ ምሳሌ ሊሆነኝ ይችላል" (ገፅ:105)።

ከዚህ እና በብዙ ቦታዎች የምታድርገውንና የምትናገረውን ጉዳዮች በማየት የሮን ይሄን አመለካከቷን በልምድ እያዳበረች መምጣቷን እንመለከታለን።

### 3.4.4. የሮን እና ሌሎች

የሮን መግቢያ መውጫ አጥታ በሴተኛ አዳሪነት ህይወት ላይ በተሰማራችበት ጊዜ ክብነሽና ብርቄ የሚባሉ ጎረቤቶች ነበሯት። ብርቄና ክብነሽ አገራቸውን ለቀው በሴተኛ አዳሪነት ስራ የተሰማሩት በተለያዩ ምክንያቶች ቢሆንም የሮን ወደ ጎረቤታቸው ከመምጣቷ በፊት ጥሩ ገበያ ነበራቸው። ነገር ግን የሮን ከመጣች በኋላ በመልኳና በተክለ ሰውነቷ ከእነርሱ ስለምትበልጥ ገበያቸው ስለቀነሰባቸው በየሮን ላይ ሲነሱ እንመለከታለን።

ከዚህም የተነሳ ጥንቆላ ቤት በመሄድ የሮንን ከገደልክልኝ በማለት ስለት ሲሳሉ እንመለከታቸዋለን (የሮን ሲፍ ሃዲስቱ፣ ገፅ: 95)።

እዚህ ላይ የሮን ለነዚህ ሴቶች ክፉ ስታስብም ሆነ የእነርሱን መጥፎነት ስታወራ አንመለከትም።

Birqeefi Kibbinesh yeroon yoggaa biiroo dhaqxee galtu. Galgalaa mana barumsaatii dhiisifattee yoggaa galtu, balbala saanirra dhaabbatanii ishee ilaalanii hinaaffadhaan gubatu (Yeroon Siif Haadhiistu, Fuula: 103).

ብርቄና ክብነሽ የሮን ቢሮ ሂዳ ስትመለስ፤ ማታም ከትምህርት ቤት አምሽታ ስትገባ፤ በራቸው ላይ ቆመው በማየት በቅናት ይቃጠላሉ (ገፅ:103)።

እነዚህ ሴቶች የሮንን ክፉኛ የጠሉ ሲሆን የሮን ግን ከመጀመሪያውም "ክፉን ማሸነፍ የሚቻለው በበጎ ነገር ነው" ስለምትል ለእነዚህ ሴቶች ጥሩ ውለታ በመዋል ከዚህ አስከፊ ህይወት ስታወጣቸው እንመለከታለን።

ቆንጂት ሰለሞን የሮንን ትቶ ያገባት ሴት ስትሆን እንደአጋጣሚ ሆኖ በዶ/ር የሮን እጅ ለመታከም ወደ ሆስፒታል እንደመጣች ነበር ከየሮን ጋር የተዋወቁት። የሮንም የእናትና የአባቷ ንብረት በቆንጅት እጅ መኖሩን እንዳወቀች ሃሳቧን አልቀየረችባትም።

"Qabeenyi Abbaafi haatishee horatan Qonjit harka akka jiru dhageessee hin aaree. Haala shee itti h in jijjiirre" (Yeroon Siif Haadhiistu, Fuula:133).

"እናትና አባቷ ያፈሩት ንብረት ቆንጅት እጅ መኖሩን ሰምታ አልተናደደችም። ፀባይዋንም አልቀየረችባትም" (ገፅ፡133) ።

እንዳውም የሮን ቆንጅትን ወደ ራሷ ቤት በመውሰድ ስትንከባከባት ስንመለከት ለሰው ልጅ ያላት ፍቅር ምን ያህል እንደሆነ ያሳያል።

የሮን እንዲህ ያለ ግላዊ መረዳት እንዲኖራት ተፅዕኖ የፈጠረባት ምንአልባትም ከሃይማኖቷ የተነሳ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም እነ ብርቄና ክብነሽም ሲሰድቧት እንዲህ ብላለች "እግዚአብሄር ይባርካችሁ! የእግዚአብሄር በረከት ያግኛችሁ" (የሮን ሲፍ ሃዲስቱ፣ ገፅ፡104)። በክርስትና ሃይማኖት ህግ መሠረት በተለይም በፕሮቴስታንት ሰው ሲረግማችሁ መርቁ፣ የሚጠሉዋችሁን ውደዱ፣ የእዛኔ የእግዚአብሄር ልጆች ትባላላችሁ የሚል በመፀሐፍ ቅዱስ ላይ ስላለ በዶ/ር የሮን ላይ ተፅዕኖ ፈጥሮባታል ለማለት ያስችላል።

### 3.4.5. ሲንቶሊናና ሌሎች

በመጀመሪያ ለሲንቶሊና ሁለተኛ ባል የሆነውን ዋሪዮን ስንመለከት በቦረና ክፍለ ሃገር የተወለደ ሆኖ ትምህርቱን ተምሮ በመጨረስ በመንግስት ሰራተኛነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው። በተጨማሪም የሹፍርና ሙያ ስላለው የንጉስ ኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ባለስልጣን ለሆኑት ለራስ ጌታውን ሹፌር ሆኖ ያገለግላል። ከሲንቶሊና ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቁትም በዚሁ በሹፍርና ስራውም ምክንያት ነበር። ዋሪዮ የተማረ ሰው እንደመሆኑ መጠን ውሎውም ከነገስታት ጋር ያገናኘዋል። ከዚህ የተነሳ ለፓለቲካውም ሆነ ለተለያዩ ነገሮች ቅርበት ያለው ሰው ነው። የኦሮሞን ባህል፣ ታሪክ እና ጥንት አመጣጥ ጠንቅቆ የሚያውቀው ዋሪዮ በደል

ሲደርስበት አሁኑኑ እርምጃ ለመውሰድ የሚጣደፍ፣ ለነፍሱ ደንታ የሌለው፣ "እንዴት እነካለሁ" ባይ ነው። ይህን አመለካከቱን የምንገነዘበው ደግሞ ራስ ጌታውን ከባለቤታቸው ተደብቀው ከሠራተኞቸው ሲንቶሊና የዋሪዮ እጮኛ ጋር በድብቅ መገናኘት መጀመራቸውን ከራሷ ሲንቶሊና በሰማበት ወቅት እንዲህ ብሏል፣ "እኔ ሌላ ነገር ቢያቅተኝ በራሱ መኪና ወስጄው ገደል መግባት አያቅተኝም" ብሏል (ገፅ።45)።

እዚህ ላይ ሲንቶሊና ግልፅ እና አስተዋይ መሆኗን እንመለከታለን። ዋሪዮ ራስ ጌታውንም እኔም እዚች ምድር ላይ አንኖርም ብሎ ሲዝት ነበረ ሲንቶሊና የተሻለ ሃሳብ በማምጣት ሃሳቡን ያስቀየረችው። በትምህርትም ሆነ በልምድ ዋሪዮ ከእርሷ የተሻለ ነበር። ነገር ግን በእርሷ ቀና አስተሳሰብ የሁለቱም ሰዎች ህይወት ተርፏል።

የሲንቶሊናና የራስ ጌታውን እንዲሁም የባለቤታቸው ንግስት ሊዲያን ሃሳብ ስንመለከት ሲንቶሊና ከእነዚህ ሰዎች የተሻለ ሃሳብ አፍላቂ፣ ቅን፣ ትዕግስተኛ ሁና እናገኛታለን። ሲንቶሊና በእነ ራስ ጌታውን ቤት ሠራተኛ ሆና በተቀጠረችበት ሰዓት እንኳ ለመጀመሪያ ባሏ የወለደችውን ልጇን፣ "የእኔ አይደለህም፣ የራስ ጌታውን ልጅ ነህ ብለሽ አሳድጊ" ስትባል "ነገ ሌላ ቀን ነው፤ እች ቀንና ጊዜ ልታልፍ ትችላለች" በማለት ነበር የልጇን ስምና ሃይማኖት እንዲሁም የራሷንም የግል ሃይማኖት በመተው በእነ ራስጌታውን ፍላጎት ስትመራ ምንም እንዳልሆነች ሰው በደስታ ህይወቷን የምትመራ ሴት ትመስል ነበር። በዚህ አስተሳሰቧ ደግሞ ተጠቃሚ ስትሆን እንመለከታታለን። ከመጀመሪያውም በሰው ቤት በጀመረችው ህይወት ስትሰቃይ ትቆይ እንጂ በኋላ ላይ ሃብት አላቸው ከሚባሉት ሰዎች ተርታ ተሰልፋለች። የተረጋጋ ህይወት መምራት ባትችልም የእኔ የምትለው ነገር የሌላት ሴት ባለ መኪናና ባለሆቴል ለመባል በቅታለች። ምንም በሌላት ጊዜ ራሷን ዝቅ አድርጋ በመኖሯ ለዚህ የበቃችው ሲንቶሊና ከህይወት ብዙ ልምድ ወስዳለች።

በትምህርት በኩል ሲንቶሊና እስከ 8ኛ ክፍል ብቻ ነው የተማረችው፤ ነገር ግን አመለካከቷን ስንመለከት አሉ ከሚባሉት የዘመኑ የሃገር ገኛ(ሮ)ዎች ትምህርት እና ሙያ ካላቸው ሰዎች በላይ ለሃገር ፣ ለወገን የሚበጅ ሃሳብ ስታነሳ እንመለከታታለን።

Isin foon keenya nyaattanii dhiiga keenya dhuguuf aangoo qabattan malee uummata baldhaa Itoophiyaaf yaaddanii miti. Graa keessanif qabsooftu malee uummataaf miti. Garuu maqaa uummata baldhaatiin daldaltu (Yoomi Laataa? Fuula:254).

እናንተ ስጋችን በልታችሁ ደማችን ለመጠጣት ስልጣን ያዛችሁ እንጂ ለሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አስባችሁ አይደለም ትግላችሁ ለሆዳችሁ ነው እንጂ ለህዝብ አይደለም። ነገር ግን በሰፊው ህዝብ ስም ትነግዳላችሁ (ገፅ፡254)።

ሲንቶሊና ይሄን ሃሳብ ያነሳችሁ ዝም ብላ አይደለም። የደርግ ባለስልጣናት ከመጠን ያለፈ ስቃይ ሲያደርሱባት የተናገረችው ነገር ነው። የእናንተ ትግል ለሆዳችሁ እንጂ ለሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አይደለም ስትል ምን ያህል ከዘመኑ ባለስልጣናት በበለጠ ለሀገርና ለወገን እንደምትቆረቆር ያመላክታል።

ይህ አቀራረፅ ደግሞ አንድም የሰው ልጅ ከተወለደ በኃላ ከሚያገኘው ልምድ እና ዕውቀት ይልቅ ይዞት የሚወለደው የአመለካከት አቅም እንደሚበልጥ አመለካች ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከደራሲው የግል ፍላጎት ሊመነጭ ይችላል። ሦስቱንም ዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያቶቹን ስንመለከታቸው ገና ከልጅነታቸው ጀምረው አስተዋይ፣ ጠንካራ፣ ለዛሬ የሚኖሩ ሳይሆን ለነገ ማንነታቸው የሚጨነቁ፣ ለወገኖቻቸው ነፃነት ሲሉ የራሳቸውን ምኞች ወደ ጎን የሚተው፣ እራሳቸው ቀልጠው ለሰው የሚያበሩ እንከን የማናወጣላቸው የሰናይ ምግባር ባለቤቶች ሆነው እንደተቀረፁ እንመለከታቸዋለን።

በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ለመጠቆም እንደተሞከረው የእነዚህ ሴቶች የትውልድ ሁኔታ ማለትም ብቸኛ ሆኖ መወለዳቸው፣ እርሱንም በስተርጅና እንዲሁም የሴቶቹ የችግር መንስኤ ተመሳሳይ መሆን ተደማምረው ደራሲው ሴቶችን በመጠቀም የተነሳለትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እነዚህን እንደቀረፃቸው መገመት ይቻላል። ለምሳሌ ያህል የሰለሞን እና የየሮንን የአስተዳደግ ሁኔታ፣ የቤተሠቦቻቸው የኑሮ ሁኔታ፣ ሃይማኖታቸውን እንዲሁም አካባቢያቸውን ስንመለከት በብዙ መልኩ ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን ይዘውት ከተወለዱት የግል አመለካከታቸው በስተቀር በገቢም ሆነ በጓደኞቻቸው ግፊት ወዘተ የሚመሳሰል ብዙ ታሪኮች አሏቸው። እንደዚሁም ሆኖ ለዓለም ያላቸው አመለካከት በጣም ይራራቃል። ይህ መለያየት የመጣው ይዞቱ ከተወለዱት የመረዳት አቅም ብቻ ነው? ያሰኛል። በዚህ እና በተለያዩ ሁኔታዎች እነዚህን ሴቶች ስንመለከታቸው ለሆነ ዓላማገግብ መችነት ሆን ተብለው የተቀረፁ ናቸው ልንል እንችላለን።

## 3.5. በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ የዋና ዋና ሴት ገፀባህሪያት ውክልና /Representation of major Female characters in Isayas Hordofa's Novel/s

> Some times characters may capture our minds and hearts because they are people we can relate to (Stanford, 1992:33).

ደራሲ የፈጠራ ችሎታውን በመጠቀም በአንድ ማህበረሰብ ወይም ሀገር ውስጥ ያለውን ክስተት ይገልፃል። ስለዚህም ስነፅሁፍ የሰውን ስብእና ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ከተወሰነ ነገር በመነሳት የሚገልፅ የፈጠራ ሥራ ነው። ለዚህም ነው ስነፅሁፍ ሐዘንና ደስታ፣ ፍቅርና ጥላቻ፣ ልደትና ሞት፣ ውድቀትና ዕድገት፣ ችግርና ድሎትን፣ ወዘተ. የሚገለጽበትና የአንድን ማህበረሰብ ማህበራዊ ገጽታ ጉልህ አድርጎ የሚያሳይ መስታወት እንደሆነ ተደርጎ የሚገለፀው።

ስነፅሁፍ የአንድ ማህበረሰብ አሻራ ማሳያ መንገድ ነው የሚለውን የኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ምስክር ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህን ልቦለዶች በምናነብበት ጊዜ ከመቶ አመታት በላይ ወደ ኋላ ተጉዘን የጥንቱን የኦሮሞ ህዝብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፓለቲካዊና ስነምግባራዊ ገጽታውን በአይነ ህሊናችን እንመለከታለን። በተለያዩ የኦሮሚያ ክልሎች ውስጥ የነበረው አስተዳደራዊ ጥቁምታዎች ምን እንደሚመስሉ እና በዛን ዘመን የነበረውን የኦሮሞ ህዝብ እምነትና አመለካከት እንዲሁም ለገኛዎች የነበረውን ፍቅር እና ጥላቻ በአጠቃላይ የዘመኑ መንፈስ ምን እንደነበረ ከታሪክ ጋር እያዋዙ የሚያቀርቡ ትልቅ የፈጠራ ሥራዎቹ ውስጥ ተስተውሏል። ለዚህም ነው የተለያዩ ምሁራን ስነጽሁፍ በዘመኑ የነበረውን እውነታ ታሪካዊ ሂደቶችንና ክስተቶችን በተለይም ማህበረሰቡ ሲያንፀባርቅ የኖረውን ነገር ሰንዶ የሚያስቀምጥ መሳሪያ ነው ሲሉ የሚደመጡት።

በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙት ሴቶች በልቦለድ አለም ውስጥ የኖሩ ታሪኩ የተተረከበትን ዘመን አስተሳሰብና ማህበራዊ ህይወት በውክልና ለማሳየት የተፈጠሩ ምናባዊ ህልውና ያገኙ ሴቶች ናቸው ስንል ይሄን ሃሳብ አስመልክተው፡-

> ገፀባህሪያት ልቦለዱ ከተቀነበበበት ቦታና ዘመን የፈለቁ የዚያው ቦታና ዘመን ሰዎች ወኪሎች ሲሆኑ በዘመኑ የነበረውን አስተሳሰብና አጠቃላይ አተያይ፣ ባህልና ማህበራዊ ልማድ፣ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሁኔታ ያንፀባርቃሉ። በማለት ገፀባህሪያት የዘመኑን መንፈስ ወክለው ሊቀርቡ እንደሚችሉ ያስረዳሉ (ዘሪሁን 2002፡ 160)።

በልቦለድ ዓለም ውስጥ የሚፈጠሩ ገፀባህሪያት በእውኑ ዓለም የሚኖሩትን ሰዎች ሃሳብ ብሎም አመለካከት፣ ርዕዮተ ዓለም ወክለው መቅረባቸውን አስመልክተው ዮሐንስ (1963፡74) እንደሚሉት፡

> ገፀባህሪያት እረቂቅ የሆኑ ሀሳቦች ጎልተው እንዲታዩን የሚፈጠሩ የምናብ ፍጡሮች ናቸው። ስለዚህ ገፀባህሪያት የአንድ ሰው ግልባጮች ሳይሆኑ የሚገልፀው የሃሳብ እምቅነት የሪዕዮተ ዓለም ብሎም ያንን ሁሉ የሚያዝ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎችን የሚወክሉ ናቸው በማለት ስለ ገፀባህሪያት ውክልና በግልፅ ያስቀምጣሉ።

ከዚህ ሃሳብ በመነሳት ገፀባህሪያት የአንድን ማህበረሰብ ብሎም የአንድን ሃገር ሃሳብ፣ አመለካከት (ideology) ወክለው ሊቀርቡ እንደሚችሉ እንገነዘባለን። ከዚህም ውጪ በመጀመሪያ ላይ የስታንዳርድ ጁድዝ አባባል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ገፀባህሪያት በእኛ አእምሮ ውስጥ ተቀርፀው በመቅረት ሁሌ እንድናስታውሳቸው ስለእነርሱ እንድናሰላስል እንድንጨነቅ ወይም እንድንደሰት የሚያደርጉን በእውኑ አለም ካለው ነገር ጋር ስለምናመሳስላቸው ነው በማለት ትገልፃለች። ኢሳያስ እነዚህን ሴቶች በዋናነት በሦስቱም ልቦለዶች ውስጥ የመረጠበት ምክንያት አንድም ከማህበረ ባህላዊ አመለካከት የተነሳ በሴቶቹ ላይ የሚፈፀምውን ግፍ እና ጭቆና ለማመላከት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሴቶቹ ላይ ሲደርስ የኖረው መከራ፣ ግፍ ፣ ጭቆናና ንቀት ወዘተ. በገዥዎች በኩል በኦሮሞ ህዝብ ላይ ከደረሰው ግፍ እና ጭቆና ኢ-ሰባአዊ አገዛዝ ጋር ስለሚመሳሰል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የእነዚህ ሴቶች ከመጠን ያለፈ ትግስትና ምክር ላሁኑ ትውልድ የራሱ ሆነ መልዕክት ስላለው እነዚህ ሴቶችን መምረጥ አስፈለገ። እነዚህ ሴቶች ብሄር ብሄረሰቦችን ለማለያየት፣ ለጠርነትና ለብጥብጥ ለማነሳሳት የተሳሉ ሳይሆን የመቻቻልን፣ አንድ የመሆንን፣ የእኩልነትን መንፈስ ለማስተማር የተቀረፁ ናቸው። እውነተኛ ነፃነት የሚገኘው የሰው ልጅ እኩል ነው "በእግዚአብሄር አምሳያ የተፈጠረ ነው" የሚለውን ሃሳብ በአእምሮው ውስጥ ሲኖር ነው የሚለውን ደጋግሞ የሚያነሱት እነዚህ ሴቶች ያለምክንያት አይደለም። "የማንም ሀይማኖት ከማንም፤ የማንም ብሔር ከማንም አይበልጥም እግዚአብሔር ሲፈጥረን አንድ አድርጎን ነው" የሚል ሀሳብ በአእምሮአቸው ይመላለሳል። አውጥተውም ተናግረዋል። የአማራን ብሄር የወከለው ኢንጂነር አማረ ትላልቅ ሆቴሎች ውስጥ ሳይቀር

"Melootiin le Tigiree

Goorgisiin le Amaaraa

Ye Gaallochuun Mexexxi

Amxuu Meettaa Biiraa (Hawwii, Fuula, 183)

መሎትን ለትግሬ

ጊዮርጊስን ለአማራ

የጋሎቹን መጠጥ

አምጡ ሜታ ቢራ (ሀዊ፣ ገፅ፡ 183)።

ብሎ ሲፎክር ሀዊ ደግነትን በተግባር አሳይተዋለች። እንዲሁም የሮንን ብንወስድ ተመሳሳይ ተግባር ፈፅማለች። የእነዚህ ሴቶች ጨቋኞና መከራ ጠንሳሾች ደግሞ የገዛ ዘመዶቻቸው መሆኑ ነገሩን ያወሳስበዋል። ከሳህለ ስላሴ(1813) ዘመነ መንግስት ጀምሮ ታሪክ እንደሚያስረዳን በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ ሁለት ወገኖች እንዳሉ ይወሳል። አንደኛው ወገን ዓላማ ያላቸው፣ ለታሪክ እንጂ ለሆዳቸው ያላደሩ፣ ለጠላት አልገዛም ባይ፣ በገዛ ሀገራቸው እና ቀዬያቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ የሚታዩ፣ በገዥዎች ዘንድ ቦታ የማይሰጣቸው፤ የተናቁ ሲሆኑ፤ ሁለተኞቹ ወገኖች ደግሞ ከጠላት ጋር ተመሳጥረው የሚኖሩ በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ተደልለው በገዛ ዘመዶቻቸው ላይ የሚነሱ፣ ማንነታቸውን በገዛ ራሳቸው አሳልፈው የሸጡ ከሃዲዎች ወይም 'ጎበናዎች' ናቸው።ይህን ሃሳብ ለማንሳት ያስደፈረን ነገር ከመጀመሪያውም በእነዚህ ሴቶች ላይ የጭካኔ መንፈስ ሲያደርሱ የኖሩት የገዥው መደብ አባላት ብቻ ሳይሆን የሴቶቹ መከራ የሚጀምረው ከገዛ ማህበራቸውም ጭምር መሆኑ ስንገነዘብ ነው። የኢሳያስ ሆርዶፋ ሴቶች አስተዋዮች፣ ቆራጦች፣ ለነገ ማንነታቸው የሚኖሩ፣ ለሆዳቸው ያላደሩ ጠንካሮች፣ ታማኞች፣ አፍቃሪዎች፣ ቀና አመለካከት ያላቸው የሰናይ ምግባራት ባለቤቶች እንደ ሆኑ በዚሁ ምዕራፍ ስር ተጠቁሟል። የእነዚህን ሴቶች ውክልና (representtation) ስናነሳ ደግሞ እነዚህ ሴቶች መላውን የኦሮሞ ማህበረሰብ ይወክላሉ ብለን በሙሉ አንደበት መናገር አንችልም። ምክንያቱም የእነዚህ ሴቶች ህይወት እንዲበላሽ ወይም ስቃይ ላይ እንዲወድቁ ከመጀመሪያውም መንገድ የከፈቱት የገዛ ዘመዶቻቸው ናቸው።

ሀዊ ከቤት ወጥታ ለዚህ ሁሉ ስቃይ እንድትዳረግ ዋነኛ ተዋናዮች ቤተሰቦቿ ናቸው። የሮንም ተመቻችታ ከምትኖርበት ከአባቷ ቤት ወጥታ ወደ አስከፊ የሴተኛ አዳሪነት ህይወት የተወሰደችው በገዛ ባሏ ምክንያት ነበር። ይህ የሚያመላክተው ደግሞ ከዱሮ ጀምሮ የኦሮሞ ማህበረሰብ በጨቋኙ የአማራ ግዛት ስር እንዲወድቅ መንገድ የከፈቱት በጥቅም የተደለሉ፣

ማንነታቸውን በጥቅም የለወጡ የገዛ የማህበረሰቡ አባላት እንደሆኑ በእውኑ ዓለም መዛግብት ላይ ተመዝግቦ የተቀመጠ ጉዳይ ነው።

> *On thing that should be known about the Amhara ruling system is that although they have been its Victims, the Oromo (the Oromo elites) participated both in the creation and perpetuation of the Amhara ruling system. The often mentioned* ***Gobena Dache,*** *the right wing of Menelik II, was one of those who hastened the incorporation of the Oromo and other southern nations and nationalities under the rule of Menelik (Hussein, 2006:269).*
>
> አንድ በግልፅ መታወቅ ያለበት ጉዳይ በአማራ አስተዳድር ስር የኦሮሞ ሰዎች ለአስተዳደሩ ጉልህሚና መጫወታቸውን ይጠቁማል።

ይህ ደግሞ ከታሪክ አኳያም ሲታይ በማህበረሰቡ ውስጥ በግልፅ የሚታወቅ እስከ ዛሬ ድረስ ጠባሳውን አኑሮ ያለፈ አስነዋሪ ስራ መሆኑ ይታወቃል። ከእነዚህ ሴቶች ጋር የተሳሉትን ገፀባህሪያት በምንመለከትበት ጊዜ ከዚህ ሀሳብ ጋር የሚሰምር ጉዳይ እንመለከታለን።ለአብነት ያህል የየሮን ባለቤት ሰለሞን በየሮን እና በገዛ ልጆቹ ላይ የወሰደውን እርምጃ ስንመለከት ከጎበናዎቹ ተርታ የሚያስልፍ ሥራ እንደሆነ እንመለከታለን።

Naahilaniin ammas xinnoo tarkaanfatee namticha ilaalee, "Sirriidha! Isadhaa!. Jedhe. Namtichi sun garuu nyaara saa walitti guuree fuulasaa irraa gargalchee qaruuraa biiraa dhugurra ijasaa dhaabe. ….

"Abbaa! Abbaa!" jechaa Naahilaniin itti deeme.

"Dhaqii abbaakee barbaadi" jedhee yoggaa harkasaa ol kaasu qodaa akaayii Naahilanii harkarraa lafatti kuffise (*Yeroo Siif Haadhiistu*, Fuula:81)

ናህላኒም ጥቂት ተራምዶ ሰውየውን ተመለከተ፣ "ትክክል! እሱ ነው!" አለ። ሰውየው ግን ፊቱን አጨማዶ ወደዛ በመዞር አይኑን በሚጠጣው ቢራ ላይ ተከለ። …

"አባ! አባ!" አለ ናህላኒ ወደሱ ተራምዶ።

"ሂድ አባትህን ፈልግ" ብሎ እጁን ሲያነሳ የናህላኒን ቆሎ ከእጁ ደፋው (ገፅ:81)።

ናህላኒ ሰለሞን ያለበት ቦታ የሄደው ሆነ ብሎ አይደለም። እየዞረ ቆሎ ስለሚሸጥ እንዳጋጣሚ አባቱን በማየቱ ተደስተዋል አባ አባ ሲለው ነበር ሂድና አባትህን ፈልግ ያለው። ሰለሞን በአደባባይ ልጁን ልጄ አይደለህም ብሎ በመካድ ብቻ አላበቃም የልጁንም መተዳደሪያ "ቆሎ" ደፍቶበታል። ይህ ድርጊቱ ደግሞ የገዛ ማህበረሰባቸውን ማንነት በመካድ የሌላቸውን ማንነት ተላብሰው ከሚኖሩት የኦሮሞ ከሃዲዎች ጋር ያመሳስለዋል።

ይሄን ሃሳብ አስመልክቶ (Gudina, 2000) በመጥቀስ (Hussein, 2006:268) ላይ እንዳስቀመጠው::

> *The Oromo generals of the late 19th &20th century cleared the way for the Amhara Kings to become Emperors While they concurrently reduced the states of their own people to gabbars (serfs) alienated from the land of their ancestors.* በማለት ለገገርው መደብ መንገድ የከፈቱ የኦሮሞ ማህበረሰብ አባለት እንደሆኑ ይጠቁማል።

ከዚህ የተነሳ የኦሮሞ ማህበረሰብ በራሱ መሬት ላይ እንደባሪያ ተቆጥሮ ሰርቶ ለሚኒሊክ መስጠት እጣ ፈንታው ሆነ ይላል።

እነዚህ ሴቶች ከቤት የወጡበት ምክንያት ስንመለከት አንድም ባርነትን ለመሸሽ፣ የራሳቸውን ማንነት ፍለጋ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሌሎችን ፍላጎት ለሟሟላት ሲሉ የመከራን ፅዋ የቀመሱ ናቸው። ሀዊ የራሷን ፍላጎት ለሟሟላት ትውጣ እንጂ "እኔንስ እንዴት ታደርግኛለሽ?" እኔን ለማን ትተሽ ነው የሚታገቢው? ያላትን የለቲን ቃል ስምታ ለእርሱ ፍላጎት መሳካትም ጭምር እርሱ በመከራት መንገድ ከቤት ወጥታለች። የሮን አባገሮ ከባሏ የተሻለ ለማግባትም ሆነ የተሻለ ኑሮ ለመኖር የተመቻቸ መንገድ አግኝታ ነበር። ነገር ግን "ለእኔ የሚመቸኝ ነገር ለልጆቼ ላይሆን ይችላል፣ እኔ ሃብታም አግብቼ ሃብታም ሁኜ መኖር እችላለሁ ግን ልጆቼን ለማን ትቼ?" በሚል ለልጆቿ ሲትል የራሷን ፍላጎት ገድባለች። ሲንቶሊና ህዝባቸውንና ወገኖቻቸውን ነፃ ለማውጣት ብለው ጫካ ለጫካ እና በሰው ሃገር ውስጥ መከራቸውን የሚያዩትን ለመርዳት ስትል ቤቷ "የወንበዴዎች መናኸሪያ" ተብሎ በመፈረጁ እስከ ሞት ፍርድ የተፈረደባት ነገር ግን እነርሱን ከመርዳት አንድም ቀን ራሷን ያልቆጠበች ጀግና ሁና ነው የተሳለችው።

እነዚህ የመንፈስና የስጋ ነፃነት ለማግኘት ቆርጠው የተነሱት ሴቶች የሚናገሩበት አንደበት ቢያጡም፣ የራሳቸውን ማንነት ቢነጠቁም፣ ተገዝተው በባርነት የምኖሩ፣ እንደፈለጉ መሆን የማይችሉ፣ የፈለጉትን የመምረጥና በራሳቸው ቋንቋ ተናግረው ለመብታቸው ለመከራከር መብት የተነፈጉ፣ ቢናገሩም የሚሰማቸው ሰው የሌላቸው ከዚህም አልፎ ለተናገሩት ነገር

የሚጠየቁ በአጠቃላይ ማንነታቸውን የማወቅ ዕድል የተነፈጉ ቢሆኑም የፈለጉትን ዓላማ ለማሳካት ወደኋላ የማይሉ ውስጣዊ ጥንካሬ ያላቸው ናቸው። ከዚህም የተነሳ በሌላ ወገን አስተሳሰብና እና አመለካከት እንዲመሩ ሲደረጉ፣ ፀጥ ለጥ ብለው እንዲገዙ የሚገደዱ፣ የእኛ የሚሉት ነገር የሌላቸው፣ ሌላው ቀርቶ በገዛ አካላቸውና ልጆቻቸው ላይ እንኳ ሳይቀር መብት የሌላቸው ነገር ግን ነገ ሌላ ቀን ነው በማለት የዛሬን ችግር በትዕግስ የሚያልፉ፣ ህይወታቸውን በተስፋ የሚገፉ፣ ለአላማቸው መሳካት እስከ ሞት ድረስ የታመኑ ጀግኖች ሆነው ነው የተቀረፁት። "ዛሬ የጠፋውን ማንነታቸውን ነገ እናገኘዋለን" ብለው ለነገ የሚኖሩ ባለተስፋዎች ናቸው። ይሄ ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ከአማራ ግዛት ስር ለመላቀቅ ሲያደርግ ከኖረው ትግል ጋር ያመሳስላቸዋል። ከዚህም በመነሳት ነው እነዚህ ሴቶች የኦሮሞን ማህበረሰብ ወክለው የቀረቡ ናቸው ብለን የምንናገረው።

"Haayiluun itti aansees Eessu dhalooti kee?" jedhee gaafateen "Wallagga." Jette. Innis "owu!." Yee Wallaggaa gaallaa yee Jootee Warqi newu," biyya jedhamudhaa? Jedhe, Hawwiinis "eeyyee!" jette (Hawwii, Fuula"133).

"ኃይሉም በመቀጠል ትውልድ ቦታሽ የት ነው?" ብሎ ጠየቃት "ወለጋ" አለች። እሱም "አ! የወለጋ ጋላ የጆቴ ወርቅ ነው" የሚባል ሀገር ነው? አለ፤ ሀዊም "አዎ!" አለች (ገፅ፡133)።

እዚህ ላይ ሀዊ አይደለም ወይም አይባልም ብላ ለመናገር አትችልም፤ ምክንያቱም ብትናገርም የምትለውጠው ነገር የላትም። እንዲሁም ሊደርስባት የሚችለውን ችግር በመገመት ነገሩን የተቀበለች መስላለች። ነገር ግን በውስጧ እነዚህ ትምክህተኞች አንዱን የኦሮሞ ሀገር በማሞገስ ሌላኛውን በመናቅ ኦሮሞ እርስ በርሱ እንዲናናቅና አንድነት እንዲያጣ ሆነ ብለው እንደሚያደርጉት ገብቷታል። ነገር ግን ለመናገር ሁኔታው አልፈቀደላትም።

ሴቶቹ የተናቁ፣ እንደሰው ሳይሆን እንደ እንስሳና እቃ የሚቆጠሩ፣ ከቁብም የማይገቡ፣ በራሳቸው ቋንቋ ለመናገር መብት የሌላቸው፣ በማንኛውም ሰው የሚደፈሩ፣ በገዛ ሃገራቸውና ቀዬያቸው የባለቤትነት መብታቸው ተገፎ ለሰው ተቀጥረው የሚሰሩ፣ በራሳቸው ስም ሳይሆን በሌላ ተቀፅላ ስም ብቻ የሚታወቁ መሆናቸው ቀደም ብሎ በዚሁ ምዕራፍ ተጠቅሷል። ይህ ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ያለፈበትን መንገድ የሚያስታውሰን ነገር እንደሆነ በተለያዩ ምሁራን ተጠቅሷል።

> .. under the abyssinian ruling system the Oromo suffered not only political and economic deprivations, but also symbolic and cultural segregations (Hussein, 2006:260).

በማለት የኦሮሞ ህዝብ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ችግር ብቻ እንዳልነበረው በመግለፅ የማንነት ጥያቄም ችግር እንደነበረው ይገልፃል። የኦሮሞ ህዝብ ራሱን "ኦሮሞ" ብሎ የሚጠራ ሲሆን በአማራ ግዛት ስር ግን ይሄን ስም እንኳ በማጣት በማይወደው ተቀፅላ ስም ሲጠራ እንደኖረ ይታወቃል። እነዚህም ሴቶች በተለይ ሀዊ [ጋሎ] ተብላ ስትጠራ እንደኖረች ከልቦለዱ ታሪክ እንረዳለን። ይሄን ስም ሀዊ ይገልፀኛል ብላ አልተቀበለችም። ይህ ደግሞ ከማህበረሰቡ ጋር ያመሳስላታል።

ሲንቶሲናን ስንመለከታትም ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ለልጇቿ የኦሮምኛ ስም ስታወጣ በራስ ጌታውን ባለቤት "እናንተ እስካሁንም አልሰለጠናችሁም" ተብላለች። የኦሮምኛ ስም ማውጣት የአለመሰልጠን ምልክት እንደሆነ በግልፅ የሚናገሩት ንግስት ሊዲያ ናቸው። ከነዚህ ሴቶች መረዳት አንደሚቻለው እንደነዚህ ሴቶች ሁሉ የኦሮሞ ህዝብም በማንነቱ ተንቆ፣ ከሰው በታች ተቆጥሮ እንደኖረ ታሪክ ይናገራል።

ባለፉት የአስተዳደር ጊዜያት የኦሮሞ ህዝብ የተገለለ የተጨቆነና ዝቅተኛ ቦታ እንደሚሰጠው የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡-

> ቴዎድሮስ ዘመናዊ የእጅ ጥበብ የሰለጠኑ ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች ለማፍራት የነበረው እቅድ እምብዛም አልተሳካለትም። በሚሊዮናዊያኑ የሚሰለጥኑት <u>ከህብረተሰቡ በሃይማኖት፣ በብሄረሰብ ወይም በኑሮ ደረጃ የተገለሉት ክፍሎች (ለምሳሌ ሙስሊሞች፣ ፈላሾች፣ የኦሮሞ የጦር ምርከኞች)</u> መሆናቸው ነገሩ ወትሮም ከነበረው የእጅ ሞያን ለተናቁ የህብረተሰብ ክፍሎች ከመተው ባህል ብዙ ራቅ እንዳላለ ያሳያል (ባህሩ ዘውዴ፣ 2003፡35)። (አፅንኦቱ የራሴ)

እዚህ ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው በአንድ ሃገር ብሎም ማህበረሰብ ውስጥ የሚናቁ፣ ቦታ የማይሰጣቸው ህዝቦች፣ ማህበረሰቦች፣ ባህሎች እምነቶች መኖራቸውን እንገነዘባለን። የኦሮሞ ማህበረሰብ ከእነዚህ ተርታ እንደሚሰለፍም ተብራርቷል። እነዚህም ሴቶች ስንመለከታቸው የሰው ልጆች ናቸው ብሎ የሚያዝንላቸውና የሚያከብራቸው አልታየም። እንደ አንድ የሰው

ልጅ ተፈጥሮ ውበት ቢኖራቸውም ውበታቸው ለተለያዩ ፆታዊ ትንኮሳ ከመዳረጋቸው ውጪ የጠቀማቸው ነገር የለም።

*Menelik's incorporation of Oromo land in to the Abyssinian Empire (Ethiopia later on) undermined Oromo identity by attacking its institutions and symbols. Oromo political and religious institutions were suppressed and their offices ceased to exist (Mekuria, 1996:55).*

የኦሮሞን ማህበረሰብ የአማራን ባህል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ እንዲወስድ በተደረገበት ሰአት መገደድ ብቻም ሳይሆን ለማንነቱ ዋጋ እንዳልተሰጠው እንመለከታለን።

እነዚህ ሴቶች ማንነታቸውን በሚያንቋሽሽ ተቀፅላ ስም መጠራት እንደማይፈልጉ ሁሉ የኦሮሞ ህዝብ በዚህ ስም ላይ ያለውን ጥላቻ የውጭ አጥኚዎች ሳይቀሩ በብዙ ምሁራን ተጠቁሟል።

The Word "Galla" whose linguistic origins is yet uncertain is a pejorative port rayal used to stamp abadge of inferiority on the Oromo. The Oromo donot like to be called "Galla". This is the name the Amhara rulers used to Wage a psychological war against the Oromo. As a term, the word Galla carries an over tone of race and slavery, and the imputation of lack of civilization (Sorenson, 1993:60) በመጥቀስ Hussein በ 'Nordic Journal of African Studies 15 (3):261፡ (2006) ላይ እንዳስቀመጠው። በዚህ ስም መጠራት እንደማይፈልጉ ነገር ግን ምንም አይነት አማራጭ ስለሌላቸው ዝም ብለው የተቀበሉ እነዚህ ሴቶች በትክክል የኦሮሞን ማህበረሰብ/ህዝብ/ አመለካከት፣ አስተሳሰብ እንዲወክሉ የተደረጉ ናቸው።

ከዚህም ሌላ እነዚህ ሴቶች የኦሮሞን ህዝብ ወክለው የተሳሉ ናቸው ብለን እምንናገረው ሴቶቹ የሚከተሉትን ሃይማኖት በመመልከት ነው። የሴቶቹን ሃይማኖት በምንመለከትበት ጊዜ ሦስቱም ሴቶች የተለያየ ሃይማኖት ይከተላሉ። ይሄ ደግሞ ከኦሮሞ ህዝብ እምነት ጋር ያመሳስላቸዋል። የኦሮሞ ህዝብ በድሮ ጊዜ የሚከተለው ሃይማኖት አንድ ቢሆንም ከጊዜ በኋላ ግን ከተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ በሃይማኖት መለያየት እንደጀመረ ካለው እውነታ አንፃር ሲታይ በግልፅ የሚታወቅ ነገር ነው።

ለዚህ ደግሞ ሲንቶሊና ጥሩ ምሳሌ ትሆናለች። ሳትወድ በግድ የክርስትና እምነት እንድትቀበል ስትገደድ እንመለከታለን።

> *The Oromo Practice three religions Islam, Christianity and Waaqeffanna (belief in waaq or sky God). Waaqeffannaa is the Oromo version of the African traditional religion (Hussein, 2004:104).*

ሲንቶሊና የ "Waaqeffannaa" ሃይማኖት ተከታይ ነበረች፤ ነገር ግን በራሷ ስምና በሃይማኖቷ እንዳትቀጥል ስትደረግ እንመለከታለን። ምክንያቱም ሲንቶሊና በሰው ቤት ተቀጥራ ስለምትሰራ የአሰሪዎቿን ፍላጎት ከማሟላት ውጭ የራሷን ፍላጎት መፈፀም አትችልም፤ መብትም የላትም። እነርሱ እንደፈለጉ እንጂ እርሷ እንደፈለገች መሆን አትችልም። የኦሮሞ ህዝብም በአማራ ቀኝ ግዛት ስር ከወደቀበት ጊዜ አንስቶ ያጋጠመው አንዱ ችግር ይሄ ነው። ማንነቱን የማወቅ እድል ተነፈገ፣[2] የራሱን ሃይማኖት፣ የራሱን ቋንቋ አጣ፣ የራሱን መሬት ተነፍጎ በባርነት የኖረበት ጊዜ እንዳለ ከማንም የተሰወረ አይደለም።

> *"... the Oromo lost their cultural, political, religious and economic freedom following their fall under the Amhara conquest at the turn of the 20th century" (Hussein, 2006:266).*

የእነዚህ ሴቶች ማንነት ተነጥቆ በባርነት የሚኖሩ ያልሰለጠኑ፣ ስልጣኔ ያልነካካቸው፣ ከዚህ የተነሳ ዝቅተኛ ቦታ የሚሰጣቸው ሆነው ነው የተሳሉት። (Hassen, 1990:2) በመጥቀስ Hussein, 2006:263 ላይ እንደጠቆመው፡-

"...the Oromo's were arbitrarily degraded to a lower stage of material, as people who needed the 'civilizing mission' of their Abyssinian neighbours."

የኦሮሞ ማህበረሰብ ዝቅተኛ ቦታ እንደሚሰጠውና ስልጣኔ የሚያስፈልገው ተደርጎ የሚወሰድ መሆናቸውን ያስቀምጣሉ።

ከዚህ እንደምንረዳው ለሴቶቹ የተሰጠው ቦታና ክብር ከኦሮሞ ህዝብ እኩል መሆኑን እንገነዘባለን። የራስ ጌታውን ባለቤት የንግስት ሊዲያና የኢንጂነር አማረን ሀሳብ ብንወስድ በትክክል ከዚህ ሃሳብ ጋር ይሄዳል። የኦሮሞ ህዝብ ያገኘውን ቦታ፣ ክብር ስንመለከት ቀኝ

---

[2] Before the expansion of Islam and Christianity the Oromo had their own traditional African religion called Waaqeffannaa, the beleif in Waaq (the supreme God). Currently the major religious are Islam and Christianity (Jeylan, Wolyie Hussein) a cultural Represntation of Women in the Oromo Society: African Study Monographs, 25(3):103-147, Octobe 2004.

ተገዝቶ የሚኖር የእኔ የሚለው ነገር እንደሌለው እንመለከታለን። ከዚህ ሁሉ ሃሳብ በመነሳት ነው የእነዚህ ሴቶች የኦሮሞን ማህበረሰብ እንዲወክሉ ተደርገው የተሳሉ ናቸው የምንለው።

የእነዚህ ሴቶች የትውልድ ሁኔታ ስንመለከት አንድም ብቸኛ ሆኖ የተወለዱ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ በፀሎትና በምልጃ እሱንም እንደ አብርሃም ልጅ እንደ ይስሃቅ በስተርጅና የተገኙ ብርቅዬ ልጆች ናቸው። ይህ የሚየሳየን ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ እንደነዚህ ሴቶች የሚያስብ፣ ንፁህ ልብ ያለው፣ ጠንካራ፣ ለሆዱ ያላደረ፣ ለነገ ታሪኩና ለሌሎች አላማ መሳካት ሲል የራሱን ምቾት የሚተው በሰዎች እኩልነት የሚያምኑ ሰዎች በብዛት አለመወለዳቸውን ያለው ከገዥ ጋር በማበር የራሱን ወገን የሚያስጠቃ፣ የሆድ አምላኮች መሆናቸውን ለማመላከት ሆን ተብለው የተቀረፁ ይመስላሉ። እነዚህ ሴቶች ተጨቁነውም "በሰው ልጅ አንድነትና እኩልነት እናምናለን" በማለት የአንድነትና የእኩልነትን መንፈስ የሚረጩ ጠንካሮች ሆነው የተሳሉ ናቸው። አንድም ጊዜ ስለልዩነትና መለያየት የማያነሱ፣ ያለፈው አልፏል ከዚህ በኋላ እንደዚህ አይነት መናናቅና መጠላላት እንዲሁም የእርስ በርስ ጦርነቶች ይቁሙ የሚል መፈክር አንግበው ለማህበረሰባቸውና ለሀገሪቱ ህዝቦች የማስተማርን አላማ አንግበው የተነሱ ይመስላሉ።

"Utuu kana booda lolli waraanaa uummatoota gidduutti hin ka'u ta'ee silaa attam gaarii turee? Yoomi Laataa? Uummatooti hundi nagaafi tasgabbii kanaan kan jiraatanii? Yoomi Laataa? Gammachuun kun utuu hin jijjiiramiin, utuu hin qabanaa'iin barabaraan kan itti fufuu?" jedhu (*Yoomi Laataa*?, Fuula:276).

ከዚህ በኋላ በህዝቦች መካከል ጦርነት ባይነሳ እንዴት መልካም ነበር? መቼ ይሆን? ሁሉም ህዝቦች በዚህ ሰላምና መረጋጋት ውስጥ የሚኖሩት? መቼ ይሆን ይሄ ደስታ ሳይቀየርና ሳይቀዘቅዝ ለዘለአለም የሚቀጥለው?" አለ (ገጽ፡ 276)።

ይሄን ሃሳብ የሚያነሳው ጋዜጠኛ ኤልያስ በሲንቶሊና ቤት በተዘጋጀው ድግስ ላይ ነበር። ሲንቶሊናም ደስታዋ ወደር አጥቶ የምትይዘውና የምትጨብጠውን አጥታለች። ምክንያቱም በተለያየ ምክንያት የተበተነው ቤተሰብ በሰላም እንደዚህ አንድ ላይ ይገናኛል ብላ ስላላሰበችም ነው። እንደዚህ ሰላም የሰፈነበት፣ ሁሉም የሚዋደድ፣የሚከባበርበት ዘመን የሚናፍቁ ሰላም ወዳዶች ሰላም የሚመኙ ሰዎች ተሰብስበው የሚያወሩት ነገር ነው። ከዚህ ሃሳብ ተነስተን ነው እነዚህ ገፀ ባህሪያት የአንድነትና የእኩልነትን የሰላምን መንፈስ የሚሰብኩ ናቸው የምንለው።

ዋና ሊባሉ የሚችሉ በብዛት ከነዚህ ሴቶች ጋር የተሳሉትን ሌሎች ገፀባህሪያትን የተመለከትን እንደሆነ በብዛት ለሆዳቸው ያደሩ፣ ለገንዘብ ብለው የገዛ ልጆቻቸውን እንኳ የሚከዱ ገፀባህሪያትን እናገኛለን። የሴቶቹ እንደ ተለኮሰ ሻማ ለሰው የሚያበሩ እንዲሁም የሌሎች ገፀባህሪያት ለሆዳቸው ማደርን ጉዳይ ስንመለከት በማህረሰቡ ውስጥ የሚንፀባረቀውን እውነታ የሚያመላክት እንደሆነ እንገነዘባለን።

የሰስቱንም ሴቶች ከትውልዳቸው ጀምሮ እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ ድረስ ያሳለፉትን ውጣ ውረድ፣ የአመለካከታቸው (ideology) መመሳሰል፣ ከተለያዩ የኦሮሚያ ክልሎች ከመምጣታቸው ጋር ተደማምረው በትክክል የኦሮሞን ህዝብ የሚወክሉ፣ በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ገድላቸው ሲነሳ የሚኖሩትን ጀግኖች የሚወክሉ መሆናቸውን እንረዳለን። በሌላ በኩል ደግሞ ስቃይና እንግልት የከበዳት ሀዊ በስተመጨረሻ ለእሯኛዋ የስንብት ደብዳቤ ከፃፈች በኋላ በሃሳቧ ውስጥ የሚመላለሱ ጉዳዮችን በግጥም መልክ ስትደረድረው እንመለከታለን። ይህ ደግሞ የእሷ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን ለነፃነት ብሎ የመከራን ፅዋ እየቀመሱ የኖሩትን የኦሮሞ ህዝብ ሃሳብ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

*Yaa addunyaa nana sin taajjabe*
*Si abdadheen abdii sirraa dhabe*
*Meeqaaf carraa laattee*
*Bilisa isaan baastee?*
*Meeqammoo hacuuctee*
*Gabrummaatti hambistee?*
*Ilmaan namaa wal caal chiftee*
*Yaa addunyaa sin taajjabe*
*Ejjennoo kee beekuun dadhabe*
(Hawwii, Fuula: 204-205).

አንቺ ዓለም ታዘብኩሽ
ተማምኜብሽ ተስፋ አጣሁብሽ
ለስንቱ እድል ሰጥተሽ
ነፃ አወጣሻቸው?
ስንቱን ደግሞ ጨቁነሽ
በባርነት አስቀረሻቸው?
የኑሮን ሚዛን አዛብተሽ?
የሰውን ልጆች አበላልጠሽ
አንቺ ዓለም ታዘብኩሽ

አቋምሽን ማወቅ ተሳነኝ (ገፅ 204-205)።

እዚህ ላይ ሀዊ ይሄን ሃሳብ ያነሳቸው እራሷን ለማጥፋት በአንድ እጇ መርዝ ይዛ ነው። "በቃ ይቺ ዓለም ለእኔ አልሆነችልኝም"፤ ከዚህ በላይ እሷ ብትሸከመኝም እኔ ደግሞ በእርሷ ላይ ለመኖር አልፈቅድም ብላ ከወሰነች በኋላ ነው ወይ ይህች ዓለም፣ ስንቱን ነፃ አወጣሽ? ለስንቱ እድል ሰጠሽ፣ ስንቱን በባርነት አስቀረሽ? ለስንቱ ፀሐይ አወጣሽ? ለስንቱ ጨለማ ሆንሽባቸው? ብላ ስትናገር ለራሷ የተናገረች ነገር እንዳልሆነ እንመለከታለን። እሷ የምታወራው በባርነት ስላሉት፣ ነፃ ለመውጣት እድል የተነፈጉትን ሰዎች ነው። ምክንያቱም ለራሷ ነፃ መውጣት የወሰነችው ነገር አላት። ሞትም ቢሆን ነፃነት ነውና መርጠዋለች። ነገር ግን ተጨንቃ የምትናገረው ተጨቁነው፣ ተገዝተው ስለሚኖሩት ሰዎች ነው። እሷ ለመሞት ከወሰነች በኋላ ለምን ይሄን ሀሳብ አነሳች ብለን ራሳችንን ስንጠይቅ ይህ ድምፅ የእሷ ድምፅ ሳይሆን በዛን ዘመን የነበሩት የኦሮሞ ጀግኖች ድምፅ መሆኑን እንገነዘባለን።

> ዮናስ አድማሱ እንደሚሉት አሁን አሁን እየተነሱ ያሉት ፀሐፊዎች የስነፅሁፍ ሥራዎቻቸውን የሚያውሉት የማህበራቸውን፣ የባህላቸውን ጉድፍ ከመንቀስ ጀምሮ መላውን ሥርዓተ ማህበር እስከመተቸትና እስከመቃወም ድረስ ላሉ ተግባራት እንደሚያውሉ ይናገራሉ። ወደኛ ዘመን እየቀረብን ስንመጣ የምናገኛቸው ፀሐፊዎች የአንድን የባህል ገፅታ ወስደው በዚያ አማካይነት ምክርና ተግሳፅን የሚያቀርቡ ሳይሆኑ፣ ህብረተሠቡ የተዋቀረበት ሥርዓት፣ የሚመራባቸው ወጎች፣ ልማዶችና ህጎች ትክክል አለመሆናቸውን መርምረው፣ ተችተው መሠረታዊ (ሥር ነቀል) ለውጥ ማስፈለጉን የሚሰብኩ ቀስቃሾች ናቸው(1992፡114)።

በኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ውስጥ ላቅ ያሉ ውስብስብ ሃሳቦችንና እሴቶችን የሚወክሉት ሴቶቹ ናቸው። እነዚህ ሴቶች የኦሮሞን ህዝብ በመወከል ለማህበረሰቡ ምክር አዘል ጥቁምታዎችን አስተላልፈዋል። ሴቶቹ በትምህርት፣ አንድነት በመፍጠርና በመግባባት ነፃነት ሊመጣ እንደሚችል መልዕክታቸውን ወደ ማህበረሰቡ አድርሰዋል። ይሄን ደግሞ ከየሮንና ከልጆቿ እንዲሁም ከሀዊ እጮኛ እንድንማር አድርገውናል።

Maal godhu nu Oromootatu tokkummaa dhabuu keenyatu akkas nu godhe. Minilik miti Goobanaafi gantoota mootota Oromoo bara sanaa tokko tokkotu harka keessan jalatti nugalche. Oromotatu gamtaa cimaa dhabe malee isin

hayyama keenya malee lafa biyya keenyaarra ejjechuu hin dandeessan ture (*Hawwii*, Fuula:130).

*ምን ያደርጋል እኛ ኦሮሞዎች አንድነት ማጣታችን ነው እንደዚህ ያደረገን። ምኒልክ አይደለም ጎበናና በዛን ዘመን የነበሩ አንዳንድ ከሃዲ የኦሮሞ ባለስልጣናት ናቸው በእጃችሁ ስር ያስገባን። የጠበቀ አንድነት በማጣታችን እንጂ እናንተ ያለእኛ ፍቃድ በእኛ መሬት ላይ መርገጥም አትችሉም ነበር* (ገፅ፡130)።

*እኛ ኦሮሞዎች አንድነት ቢኖረን፣ መግባባት በመሃላችን ቢኖር ኖሮ በማንም አንናቅም፣ በራሳችን ሃገርና መሬት ላይ በቋንቋችን እንደፈለግን መሆን እንችል ነበር ትላለች ሀዊ። ይህ ደግሞ የሚያመላክተው አንድነት፣ መግባባት እና እውቀት ለነፃነታችን ወሳኝነት አለው ማለት እንደሆነ ግልፅ ነው።*

የልቦለዶቹም አንድምታ ርእዮተ ዓለማዊ ነው፤ ግቡም የእያንዳንዱን ሰው ግለሰባዊ ደህንነትና መብት፣ እንዲሁም የክልሉን ማህበራዊና ፓለቲካዊ እጣ ፋንታ የተሻለ ለማድረግ የሚያስችለውን የሰዎችን ፓለቲካዊ ንቃት ማጠናከር፣ የታሪክ አቅጣጫዎችንና ማህበራዊ ኃላፊነቶችን ማመላከት ነው። ማህበራዊ ፋይዳውም ማረምና ማስገንዘብ የሚመለከታቸውን ማህበራዊ ክፍሎችን መለወጥ ነው። ብርሃኑ ገበየሁ *ፍቅር እስከመቃብር* ላይ "ልቦለድ እንደ ርዕዮተዓለም መገለጫ" በሚል ርዕስ ስር እንዳሳዩት ኢሳያስ ይህንን ትልቅ ቁም ነገር በሴቶቹ አመካኝቶ ማስተላለፍ የቻሉት ጋብቻንና ታሪክን፣ የልቦለዶቻቸው መተጋጊያ (frame work) በማድረግ ሲሆን፣ ሦስቱም ልቦለዶች ከ1800ዎቹ ገደማ እስከ 1980ዎቹ የመጀመሪያ አጋማሽ በነበሩት ተከታታይ የታሪክ ዘመናት የተከሰቱ ማህበራዊ፣ ፓለቲካዊ እውነታዎችን በመሳላቸው ታሪካዊ ገፅታቸው የጎላ ነው ማለት እንችላለን።

እነዚህ ሴቶች በክፋ ሥራ ፣ በአመፅ፣ በጦርነትና ክፋት ማህበረ ባህላዊ ለውጥ ወይም ነፃነት እንደማይገኝ፣ በጥቂት ግለሰቦችና ቡድኖች አመፅ ነፃነትና ለውጥ ሊመጣ እንደማይችል ከሲንቶሊና የመጀመሪያ ባል ህይወት መማር ይቻላል። በወጣትነት እድሜው ከሸፈተ በኋላ አርጂተው ወደ ቤቱ ተመለሰ። አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ በስተርጅናው ጫካ ገባ፣ ነገር ግን ቤተሠቦቹን ከመጉዳትና ለተረጅነት ከመዳረግ ውጪ ምንም አይነት ለውጥ አላመጣም። ለውጥ የሚመጣው የተማረው የኦሮሞ ህዝብ ብሎም ወጣት አንድ ሆኖ በሰላማዊ መንገድ ለማንነቱ ሲሟገት እንደሆነ ከሀዊ እሎኛ እና ከየሮን ልጆች እንዲሁም ከራሷ ከየሮን ህይወት ይቻላል። ብሔር ብሔረሰቦችን ሳያከፋፍሉ በእኩል ዓይን እያዩ ተገቢውን እንክብካቤ

ሲያደርጉላቸው ስንመለከት እውነትም አንድነትን ለማስረፅ ሆን ተብለው የተቀረፁ ናቸው ያሰኛል።

ደራሲው ማንነታቸውን አሳልፈው በገንዘብ በመሸጥ ከጠላት ጋር በማበር ህዝባቸውን ሲያስቃዩ የኖሩትንና የገኘሮውን መደብ ወክለው በኦሮሞ ህዝብ ላይ የግፍ አገዛዝ ሲያንፀባርቁ በኖሩት ገፀባህሪያት ላይ ቅድመ ጥላቻ ያደረበት ይመስላል። ምክንያቱም በዚህ አኳኋን የሚፈረጁትን ገፀባህሪያት መጨረሻቸውን በአሰቃቂ ሞት ሲቀጣቸውና ተመልሰው በሴቶቹ እጅ እንዲገቡና እነርሱን ለሚኖ እንዲኖሩ በማድረግ ወገናዊነትን አሳይቷል። ለምሳሌ ያህል የየሮን ባል ከሁለተኛ ባለቤቱ ጋር ካለመስማማት የተነሳ እሷን በሽጉጥ ከመታ በኋላ ታስሮ ከእስር ቤት ሲወጣ ምንም የሚገባበት ቤት እና የሚተዳደርበት ንብረት ስለሌለው የጉልበት ሥራ እየሰራ እያለ አንድ ቀን ድሮ "የእኔ ልጅ አይደለህም" ያለውን ለገዛ ልጁ ሻንጣ ተሸክሞ ቤት ከደረሰ በኋላ የድሮ ባለቤቱን የሮንን ዶክተር ሁና በማየቱ ድሮ ያጠፋው ጥፋቱ ተሰምቶት ከዚያ ወጥቶ በመንገድ ላይ በመኪና ተገጭቶ ይሞታል። የገኘሮውን መደብ ወኪለው የቀረበው ኢንጂነር አማረም የራሱን መኪና ይዞ ሲሄድ ሌላ መኪና ወጥቶበት ሁለት እግሮቹ ተቆርጠው ግራ እጁም እዚያው ይወድቃል። አንድ አይኑም ጠፍቶ እርሱ መሆኑ ራሱ ያሳስታል። አሰቃቂ ሞት ቀመሰ። ሀዊ ግን ሆስፒታል ከገባች ወዲህ የተዘረጋ እግሮቿን ስትሰበስብ ታይታለች። እንዲሁም በሲንቶሊና ላይ የግፍ አገዛዝ ሲያንፀባሪቁ የኖሩት ቀኝ አዝማች ግዛቸው አንገታቸው በገጀራ ተቆርጦው ድንገተኛ ሞት ሲሞቱ እንመለከታለን ። ራስ ጌታውንም መግቢያና መውጫ ሲያጡ ሰው ከሚገድለኝ በሚል ኢትዮጵያን አንድ የማድረግ ጠኔ የተጠናወተው እንደ ቴዎድሮስ የራሳቸውን ሽጉጥ ጠጥተው አለፉ። የእነዚህን ገኘሮዎችና የኅበናዎቹን ሁኔታ በልቦለዶቹ ውስጥ ስንመለከት መጨረሻቸው ያላማረ ሆኖ አግኝቻቸዋለሁ። ይህ ደግሞ የደራሲው ወገናዊነት የተንፀባረቀበት ድርጊት ነው ለማለት ያስችላል።

በአጠቃላይ የኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶች ካለፈው የሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ስለሆነ ታሪክ ቀመስነታቸው ጎልቶ ይታያል። በይበልጥ መሰረታቸውን በአፄ ሚኒሊክ የበለጠ ደግሞ በአፄ ኃይለ ስላሴ ዘመን ላይ በመመርኮዝ እስካለንበት ዘመን የሚዘልቀው የልቦለዶቹ ታሪክ በእነዚህ ጊዜያት የኦሮሞ ማህበረሰብ ያሳለፈውን ውጣ ውረዶች በወካይ ገጸ ባህሪያት አማካኝነት በመጠቆም በዚያውም የተነሱለትን አላማ ለማሳካት የማጠናከርን፣ የማስተማርን፣ የማሳየትንና የመቻቻልን መንፈስ እንዲሁም የአንድነትን ሃያልነት የሚሰብኩ ሃሳቦችን ያዘሉ ልቦለዶች ናቸው።

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

ደራሲያን ወካይ ገፀባህሪያት ለፈለጉት ዓላማ ግብ መችነት ተጠንቅቀው በሚመርጡበት ጊዜ አበይት ስብእናዎችን እያላበሱ ማቅረብ የተለመደ ነገር ነው። በዘመናዊ ስነፅሁፍ ውስጥም ሲንፀባረቅ ይስተዋላል። በኦሮምኛ ስነፅሁፍ ውስጥም "ብዙ ቴክኒካዊ ጉዳዮቻቸው ዳብረው መቅረብ ችለዋል" ብለን በሙሉ አንደበት መናገር ባይቻልም መታየት የጀመረው ብልጭታ ግን ይበል የሚያሰኝ ነገር ነው።

ጋዜጠኛና ደራሲ ኢሳያስ ሆርዶፋ በተያያዥ ሥራቸው ውስጥ ለሚዲያው ቅርበት ስለነበራቸው የማህበረሰቡንም ሆነ በሀገሪቱ ውስጥ የሚከናወኑ ጉዳዮችን ፈጥነው የመረዳትና የማወቅ ዕድላቸው የሰፋ ነበር። ከዚህም የተነሳ የፓለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ማህበረባህላዊ ጉዳዮች ጠንቅቀው ስለሚያውቁ እነዚህ ሴቶችን እንደወካይ ገፀባህሪ በመቅረፅ ያቀረቡት የፈጠራ ሥራቸው ተሳክቶላቸዋል ለማለት ይቻላል።። ምክንያቱም ደራሲዎች ለማስተላለፍ የፈለጉትን ቁም ነገር ግብ እንዲመታላቸው ወካይ ገፀባህሪ መረጣ ላይ ጊዜያቸውን እንደሚያጠፉ ይታወቃል። ለዚህም ይመስላል በሀዊ የጀመሩት ኢሳያስ ሆርዶፋ በሌሎች ልቦለዶቻቸውም ውስጥ ሴቶችን እንደ ወካይ ገፀባህሪ መጠቀማቸውን ቀጥለውበታል።

እነዚህን ሴቶች ስንመለከታቸው የሚያነሱት ነገር ከማህበረሰቡ ጋር ይያያዝ እንጂ በይበልጥ ስለ ማንነት (identity) ጥያቄ ነው። ስለ ማህበረሰቡ ቋንቋ፣ ባህል፣ ምንነትና ማንነት የሚያነሱ ናቸው። የሴቶቹ ማህበረባህላዊ ደረጃ ከወንዶቹ አኳያ ሲታይም በጣም ዝቅ ያለ ሲሆን አባቶች "የሴት ልጅ ትምህርት ከምን ያደርሳል" ከሚለው የተሳሳተ አባባሎቻቸው ጀምረው ሌሎች ለሴቶች ቦታ የማይሰጠውን አባባል በመከተል በሴቶቹ ላይ ይተገብሩታል። ሴቶቹ በራሳቸው ላይ ከፍ ያለ እምነት እና ግምት ቢኖራቸውም መግቢያ መውጫ ስለሌላቸው የተባሉትን ብቻ ለመፈፀም ይገደዳሉ። አንዳንዶች ደግሞ ከዚያ ውጪ ሲወጡ የሚደርስባቸው መከራና እንግልት የከፋ ነው። ሆኖም እነዚህ ሴቶች የማህበረሰቡን ባህል ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ መከበር አለበት ብለው የሚያምኑትን የሚያከብሩ መከበር የለበትም ብለው ያመኑትን ደግሞ የማያከብሩ ጀግኖች ሁነው የተሳሉ ናቸው። ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በቀጥታ ለመቃወም መብት ስላልተሰጣቸው ያላቸው ብቸኛ አማራጭ ከአካባቢውና ከማህበረሰቡ መሰወር ብቻ ነው። ለዚህም ነው ሰስቱም ሴቶች መሸሸግያቸውን አዲስ አበባ የሚያደርጉት። ሀዊ ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ከወላጆቿ ጠፍታ አዲስ አበባ ገባች። የሮን በትዳር

ላይ ባጋጣማት ችግር ወደ አዲስ አበባ መጣች። ሲንቶሊናም በተመሳሳይ ሁኔታ የትውልድ ቦታዋን በመተው አዲስ አበባ ገብታለች። ስለዚህ የእነዚህ ሴቶች መሸሸግያቸውን አዲስ አበባ ያድርጉ እንጂ አወጣጣቸው አንድም ማህበረ ባህላዊ ተፅዕኖዎችን ለመሸሽ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ነፃነት ፍለጋ ነው።

እነዚህ ሴቶች ለራሳቸውና ለወገኖቻቸው ነፃ መውጣት ሲሉ የመከራን ፅዋ የቀመሱ እንደ ተለኮሰ ሻማ በመሆን ራሳቸውን ለሌላ ሰው ሲሉ የሚሰው፣ የራሳቸውን ፍላጎት የማያስቀድሙ፤ ልበ ሙሉ ጠንካሮችና የሰናይ ምግባራት ባለቤቶች ሆነው የተሳሉ ናቸው። ከዚህም የተነሳ በውስጣዊና ውጫዊ ስብእናቸው ይመሳሰላሉ። ሶስቱም ቆንጆ ሴቶች ናቸው። በውስጣዊ ስብእናቸውም ጠንካሮች ናቸው። እንዲሁም በአመለካከታቸው (ideology) የሚመሳሰሉ ናቸው። የሚለያያቸው ነገር ቢኖር ከተለያየ የኦሮሚያ ክልሎች መምጣታቸውና የተለያየ የኑሮ ደረጃ ካላቸው ቤተሠቦች መወለዳቸው እንዲሁም ከሚከተሉት ሃይማኖት በስተቀር ሴቶቹን በመልክም ሆነ፣ በተክለሰውነታቸው፣ ለሰው ልጅ ካላቸው አመለካከት ተነስተን እንዳያውም እነዚህ ሴቶች አንድ ናቸው ለማለት ያስደፍራል። ከዚህም ውጪ ለቤተሠቦቻቸው ብቸኛ ልጆች እርሱንም በስተርጅና የመገኘታቸው ጉዳይ ተደማምረው "ይህች ልጅ በተለያዩ ጊዜ ብቅ እያለች የምትናገር፣ ሃሳቧን የምትገልፅ አንዲት ልጅ ብቻ ትሆን እንዴ?" ያሰኛል።

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ሴቶች በዘመኑ ለነበሩት ወጣት የኦሮሞ ተወላጆች የማንነት ጥያቄ ለማመላከት እና የኦሮሞ ማህበረሰብ የሳለፈውን ውጣ ውረድ ለማሳየት ሲሆን በነዚህ ሴቶች ዘመን ውስጥ የነበረው የተማረው የኦሮሞ ወጣት ትውልድ በማንነቱ የሚያፍር እንደ እነ "ለሙ በንቲ" በኋላ "አለሙ ባንቴ" እና ማርታ ያሉ ወጣቶች ውስጥ እራሳቸውን ሆነው የሚኖሩትን የዘመኑን ጥቂት ወጣት ወክለው የተሳሉ ናቸው። ከሳህለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ እስከ ዘመነ ደርግ ድረስ በኦሮምኛ ቋንቋ መገልገልና "እኔ ኦሮሞ ነኝ" ብሎ እራስን ማሳወቅ እንደ አለመሰልጠን ተደርጎ ይታሰብ እንደነበር ከልቦለዱ ታሪክ መረዳት ተችሏል።

እነዚህ ሴቶች ግን በእነዚህ አስቸጋሪ ዘመናት ውስጥ በማንነታቸውና በምንነታቸው የማያፍሩ ቆራጥ የኦሮሞ ጀግኖችን ወክለው ስለመቅረባቸው ተደርሷበታል። ለቆራጥነታቸውና ለዚህ ዕኑ ብርታታቸው ደግሞ ይዘውት የተወለዱት ግላዊ መረዳት፣ አካባቢ፣ልምድና ትምህርት ተፅእኖ እንደፈጠሩባቸው ይገመታል።

እነዚህ ገፀባህሪያት በኖሩበት ዘመናት በይበልጥም ከዘመነ አፄ ሚኒሊክ እስከ ዘመነ ደርግ ድረስ በአማርኛ ቋንቋ መናገር እና በአማርኛ ስም መጠራት የስልጣኔ ምልክት ተደርጎ ይወሰድ ስለነበር በዘመኑ የነበሩት የኦሮሞ ተወላጆችም በዚህ ተፅእኖ ስር ሲወድቁ ታይተዋል። እነዚህ ሴቶች ግን ይህን ፈተና ሲያልፉና ሲያሸንፉ እንመለከታቸዋለን። ከዚህ በመነሳት ደራሲው እነዚህን ሴቶች አንድም ከዓባዊው አመለካከት የተነሳ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን አድሎ ለማመላከት የቀረፃቸው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶቹ የቀመሱት ከኦሮሞ ማህበረሰብ ታሪክ ጋር ስለሚመሳሰል ለሁለት ትላልቅ ዓላማ እንደቀረፃቸው ተደርሶበታል።

በዚሁ ንዑስ ምዕራፍ ስር ለመመልከት እንደተሞከረው አንዱና ዋነኛው ጉዳይ በፍካሬ ነጥረው የሚወጣ የሴቶቹ ውክልና (representation) ነው። ውክልና ሲባል ብዙ ትርጓሜና ትንታኔ ያለው ቃል መሆኑ በምዕራፍ ሁለት ተጠቁሟል። ከዚህ ሃሳብ ተነስተን እነዚህ ሴቶች የኦሮሞን ማህበረሰብ ወክለው የቀረቡ ናቸው ብለን በሙሉ አንደበት የተናገርነው በዛን ዘመን በገሃዱ አለም ከነበረው እውነታና በልቦለዶቹ ውስጥ የተፈፀሙትን ድርጊቶች ዋቢ በማድረግ ነው።

ከመጀመሪያው የእነዚህ ሴቶች ብቸኛ ሆኖ መገኘት፣ የማህበረባህላቸው አክባሪ መሆናቸው፣ ነገር ግን ለመብታቸው ለመከራከር አንደበት ማጣታቸው እና ከተናገሩ ደግሞ ስቃይ እና እንግልት፣ ከገዛ ቤተሠቦቻቸውና ዘመዶቻቸው መለየት የሚጠብቃቸው መሆኑን ስንመለከት እነዚህ ሴቶች የኦሮሞ ማህበረሰብ በአማራ አገዛዝ ስር በነበረበት ጊዜ ያሳለፈውን አስከፊ ጊዜ ለማንፀባረቅ ሆን ተብለው የተቀረፁ ናቸው ለማለት አስችሎናል። የእነዚህ ሴቶች መከራ ጠንሳሾች ደግሞ ገና ከመጀመሪያው ከገዛ የቅርብ ዘመዶቻቸው መሆኑ ደግሞ በማህበረሰቡ ውሰጥ ሲንፀባረቅ የነበረውን የጎበናዎቹን ድርጊት ያስታውሰናል።

እነዚህ ሴቶች የራሳቸውንም መብት አጥተውም እያሉ የሚያነሱት ግን የሰውን ልጅ እኩልነት፣ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር አንድ አድርጎ እንደሆነ የሚሰብኩ ቆራጦች፣ ለአላማቸው ሲሉ እስከ ህይወት መስዋዕትነት የሚደርሱ ጀግኖች ሆነው ነው የተሳሉት። ከዚህ በመነሳት ነው እነዚህ ሴቶች ለሆዳቸውና ለጥቅም ያልተደለሉ፣ ለነገ ማንነታቸው የሚኖሩ የኦሮሞ ማህበረሰብን ወክለው የቀረቡ ናቸው ብለን ለመናገር ያስደፈረን።

ከዚህም ውጪ እነዚህ ሴቶች የሚታወቁት በስማቸውና በማንነታቸው ሳይሆን የእነርሱን ማንነት በማይገልፅ ተቀፅላ ስም ብቻ ሲጠሩ እንመለከታለን። በተለይ ሀዊ፣ አማረ ዘንድ

አንድም ጊዜ ሀዊ ተብላ ስትጠራ አናገኝም፤ [ጋሎ] በሚል ተቀፅላ ስም ትታወቃለች። የአማራን ብሔር ወክለው የቀረበው ኢንጂነር አማረ በታሪኩ ውስጥ በተፈጠረው መቼት "ከእጁ እየበላ፣ እሷ እየመገበችው፣ አብሮ እየኖሩ" ነገር ግን በስሟ ሲጠራት አንድም ቀን አልተሰማም፤ አልታየምም። ሲንቶሊናም፣ "ይቺን የመሰለች ልጅ! እንዴት በዚህ አስጠሊታ ስም ትጨራለሽ?"፣ እየተባለች ነገር ግን ሁለቱም ማምለጫ መንገድ ስለሌላቸው ዝም ብለው የተቀበሉ መስለው ጽምፃቸውን አጥፍተው ተቀምጠዋል፤ ቢናገሩም የሚለወጡት ነገር ስለሌላቸው። ይሄ ደግሞ ከኦሮሞ ማህበረሰብ ታሪክ ጋር ያመሳስላቸዋል። ኦሮሞ "ኦሮምነቱ" ጠፍቶ [ጋላ] የሚል ተቀፅላ ስም በአማራ ገዥዎች ተለጥፎበት ለብዙ አመታት ተሸክሞ እንደኖረ ያለ ሀቅ ነው።

ይሄን የተለጠፈበትን ስም ለማጥፋትም ሆነ "በዚህ አልጠራም፤ አይገልፀኝም" ብሎ ለመከራከርም መብት የሌለው መሆኑ በገሃዱ ዓላም ሲንፀባረቅ የኖረና ከማንም ያልተደበቀ እውነት ነው። ለዚህም ነው እነዚህ ሴቶች የኦሮሞን ማህበረሰብ አመለካከት፣ አስተሳሰብ እንዲሁም ያሳለፈውን ውጣ ውረድ እንዲወክሉ ተደርገው የተሳሉ ናቸው የምንለው።

ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ የልቦለዶቹ ደራሲ የገዥውን መደብ እና ጎበናዎቹን (ከሃዲዎቹን) ወክለው በቀረቡት ገፀባህሪያት ላይ ቅድመ ጥላቻ ያደረበት ይመስላል። ምክንያቱም የአማራን ብሔር ወኪለው በቀረበው ኢንጂነር አማረ ገና በለጋ እድሜው በመኪና አደጋ አንድ እጁ ሲቆረጥና አንድ አይኑ ስጠፋ እንመለከታለን። በጎበናዎቹ ተርታ የሚሰለፈው በዘሩ ኦሮሞ የሆነው የጅማው ሰለሞን፣ የየሮን ባል፣ እንዲሁ በመኪና አደጋ ህይወቱ ሲያልፍ ይታያል።

በሲንቶሊና ላይ የግፍ አገዛዝ ሲያራምዱ የኖሩት ቀኝ አዝማች ግዛቸውም ራቂታቸውን እያሉ በገጀራ አንገታቸው ተቆርጦ አሳፋሪ ሞት ሲሞቱ እንመለከታለን። ራስ ጌታውንም ቢሆኑ መውጫ መግቢያ አጥተው እንደ ተዎድሮስ በራሳቸው ሽጉጥ ህይወታቸው አለፈ። ነገር ግን ከመከራና ስቃይ ብዛት የተነሳ መርዝ ጠጥታ ሆስፒታል የገባቻው ሀዊ ደግሞ የተዘረጋ እግሮቿን ስትሰበስብ ታይታለች። ከዚህ ተነስተን ደራሲው በእነዚህ ገፀባህሪያት ላይ አስከፊ ሞት ሲፈርድባቸው እነ የሮንን ደግሞ መለኮታዊ ሀይል በታከለበት መልክ ወደ ክብር ሲያሳድጋቸው በመመልከታችን ወገናዊነትን አንፀባሪቋል ለማለት ያስደፍራል።

በአጠቃላይ ሲታይ የኢሳያስ ሆርዶፋ ልቦለዶችያለፈውን የኦሮሞ ህዝብ ታሪክ ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ ሰንዶ በማስቀመጥ ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው። እንዲሁም ያለፈውን

ታሪክ ይዘን ዛሬ ያለነው ትውልድ ለበቀል መነሳሳት እንደሌለብንና እኛም እንደ አንድ ኢትዮጵያዊነታችን ከተለያዩ የኢትዮጵያ ብሄርብሄረሰቦች ጋር በሰላምና በፍቅር መኖር እንድንችል የምመክሩ ምክር አዘል ቁም ነገሮችን የሚያስተላልፉ ናቸው። የሚያሳስቡት ነገር ደግሞ "ኢትዮጵያዊነታችን ኦሮሞነታችንን ሊያስረሳን ወይም ሊያስክደን አይገባም" የሚል ቁም ነገር ጠቁመው የሚያልፉ ናቸው።

## ዋቢ ፅሁፎች


Ahimad Abdii. (2011/2003). "Xiinxala Gooban Galeessa Asoosama Yoomi Laataa? Keessatti" Faakiltii Qo'annoo Afaantaa Koollejjii Hawwaasummaafi Hiyuumaanitii, Muummee Afan Oromoo, WQ DBA; Yuunivarsiitii Finfinnee.

Alhott, M. (1960). *Novelists on the Novel*. London: routledge and Kegan Paul.

Asafaa Tafarraa Dibaabaa. (2009). *EELA*: Seenaa Oguma Oromoo (History of Oromo Literature). Finfinnee, Oromiyaa: Far-East trading PLC.

Ashcroft, B. Gareth Griffiths and Helen Tiffin. (1989). *The Empire Writes Bank*: Theory and Paractice in post –colonial Liteatures London: Routledge.

_____. (2004). The post-colonial, Studies Reader. London and New York: Routledge.

Atkins, K. (2008). *Narrative Identity and Moral Identity*: A practical perspective; New York: London: Routledge.

Basch, F. (1975). *Relative Cratures: Women in the Soceity and the Novel*. NewYork Schocken.

Biiroo Aadaafi Tuurizimii Oromoiyaa (BATO). (1998). *Seenaa Oromoo Hanga Jaarraa 16<sup>fa</sup>*. Berhanena Selam Printing enterprise: Finfinnee.

Cavallaro, Dani. (2001). *Critical and Cultural Theory*. London and New Bruns Wick: New Jersey: Athlone Press.

Collins, S. (1992). *Approaching Literature*. London's Sydney Auckland: Hodder and Stoughton.

Deggamanyi Konchii Tolaa. (2009/2001). "Xiinxala Mala. Barreeffama Asoosamoota Hawwiifi Yeroon Siif Haadhiistuu." Muummee Afaanotaafi Hog-barruu Otoophiyaatti Sagantaa Afaaniifi Hog-barruu Oromoo Barreeffama Qorannoo Digirii Baachilarii Aartii guuttachuuf dhiyaate; Yuunivarsiitii Finfinnee.

Dirribii Damusee. (2009). *Ilaalcha Oromoo Barroo Amantaa*: Sirna Bulchiinsaafi Seenaa Oromoo: Mana maxxansaa D.G. Finfinnee.

Ellman, M. (1968). *Thinking about Women*. New York: Harcourt Brace, Javano Vicha.

Endalew Mola (2011). "Teachers Perception of Speaking Skill, Speaking Instruction and Students perception of Speaking." MA. Thesis DTEFL: AAU.

Ferguson, M.A. (2nd ed). (1977). *Images of Women in Literature.* Boston: Houghton Mifflin Company.

Frank, Lkinda S. (1985). " 'Bird at the Window': The Representation of Women In Canadian Fiction". A Thesis Submitted to the School of Graduate Studies in partial Fulfilment of the Requirements for the Degree Master of Arts: MC Master University.

Gemechu Megersa. (eds). (1996). "Oromumma: Tradition, Consciosness and Identity". In PTW. Baxter, J. Hultin and A Trivlzi. *Being and Becoming Oromo*: Historical and Anthroplogical Enquiries, Uppsala: Nordiska African institute.

Gibaldi, J.(6th ed,). (2003). *MLA Handbook for Writers of Research Papers.* New York: The Modern Language Association of America.

Ginbaar Nagaraa. (2010). *Seenaa Abishee Garbaafi Gootota Oromoo Biroo.* Adaamaa.

Hall, Stuart, (eds). (1977). *Representation: Cultural Representations and signifying practices.* London: open university Press.

Halls, C. and Gardner, L. (1989). *Theories of Personality.* John wiley and sons, inc. Canada.

Harvey, W.J. (1965). *Character and the Novel.* London: Chatto and Windus; ltd.

Hussein, J.W. (2004). "*A Cultural Representation of Women in Oromo Society.*" African Study Mono Graphs 25(3):103-147.

________. (2006). "A critical Review of the Political and Stereotypical Portrayals of the Oromo in the Ethiopian Historiography" African Study Monographs 15(3): 256-276.

Isaayyaas Hordofaa. (1995). *Hawwii.* Finfinnee: Itoophiyaa.

______ . (2000). *Yeroonsiif Haadhiistu.* Finfinnee: Itoophiyaa.

______ . (2002). *Yoomi Laataa?* Finfinnee: Itoophiyaa.

Janeway, E. (1974). *Between Myth and Morning: Women Awakening.* New York: William Morrow and Co.

Katz, N. and Nancy, M. (1975). *Women of the Third World: Twenty Stories Set in Africa, Asia and Latin America.* London: the Camelot press Ltd, Southampton.

Khera, Shiv. (eds.). (2002). *You Can win: Winners Don't do different things; They do things Differently*. Rajiv Beri: Macmillan India Ltd.

Kowaleski, Elizabeth. (eds.). (1997). *Encyclopedia of Feminist Literary Theory.* New York; Wallace Garland Publishing inc;.

Mekonin Feqadu (2005). "Images of Women's in the Fictions of Selected African Women Writers: A Comparative Black Feminist Study." M.A. Thesis. DFLL A.A.U.

Mekonnen Zegeye. (2000). "Images of Women and Plot Structure in First Four Novels of Fikiremarkos Desta." M.A. Thesis DFLL. A.A.U.

Mekuria Bulcha. (1994). "The Langauge Policies of Ethiopia Regimes and the Hisotry of written Afaan Oromo: 1844-1994." *The Journal of Ormo Studies*. Vol.2, No.2, Middle Genness State University.

_________. (1996). "The Survival and Reconstruction of Oromo national Identity. In Uppsala. Nonrdiskal African Institutes: P.T.W. Baxten J.

Melakneh Mengistu. (2010). *Post Colonialism and Mainstream Anglophone African Novel*. PhD. Diss: USA; VDM Publishing House ltd.

Mohammed Hassen. (eds). (1996). *The Development of Oromo Nationalism*. In: P.T.W. Baxter J. Hultin and A Triulizi Being and Becoming Oromo: Historical and Anthroplogical Enquiries: Pp 67-80 lawencaille NJ: The Redsea Press.

Mulumebet Zenebe. (1996). "A comparative Analysis of Images of Men and Women in the Works of Some Ethiopia Women Writers." M.A. Thesis DFLL; AAU.

Nenola, Aili. (eds.). (1993). *Folklore and the Genderized World or Twelve Points from A Feminist Perspective* (source: **Folklore Concepts and Definations).**

Peter, Zola W. (2010). "The Depiction of Female Characters by Male Writers in Selected ISIXHOSA Drama Works" Submitted in Fulfilment of the Requirements for the Degree of Doctor Litterum: Faculty of Arts: Nelson Mandela Meteropolitan University.

Ramadaan Mahaammad. (2002). "Haala Fayyadama Bifoota Yoomessaa Asoosamoota Hawwiifi Yeroon Siif Haadhiistu keessatti." Kutaa Qooqilee Itoophiyaafi Hog-barruu: Sagantaa

Afaan Oromoofi Hog-barruu. Barreeffama Qorannoo Digirii Baachilarii Aartii; Yuunivarsiitii Addis Ababaa.

Ruth, Sheila. (4th eds.). (1998). *Issues in Feminism: An Introduction to Women's Studies.* Mountain View ; CA May Field Publishing company.

Stanford, J.A. (2nd ed). (1992). *Responding to Literature*. London: May Field Publishing Company.

The American Heritage Dictionary of English Language (4th ed.). (2004). Houghton: Mifflin Company.

Wellek R. and Austire, W. (1956). *Theory of Literature*. New York: Harcoure, Brance and World, inc.

Zerihun Asfaw. (1997). "Women in the Works of Ethiopian Short Story Writers." 13th proceeding of International Conference on Ethiopian Studies, Kyota, Japan.

ርዕዮት አለሙ። (2004)። *የኢህአዴግ ቀይ እስክሪብቶ።* አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

ባሕሩ ዘውዴ። (2003)። *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983።* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ አዲስ አበባ።

ብርሃኑ ገበየሁ፤ (1991)፤ "ልቦለድ እንደ ርእዮተ ዓለም መገለጫ"፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የሥነ ፅሁፍ መጽሔት፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ቁጥር 10፤ ገጽ 41-76።

ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ። (1959)። *ታሪክ ዘመን፤ ዘዳግማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ሊሚትድ፣ ቁ. 6060።

አዲሱ ዘገዬ፤ (2000)፤ "እንስታዊ የሥነ ፅሁፍ ሂስ ከ1984-1997 ዓ.ም በታተሙ የሴቶች የግጥም መፃህፍት ውስጥ"፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ በኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ለኤ.ምኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አ.አ.ዩ።

አለም እሸቱ።(3ተኛ እትም)። (1997)። *መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

የአማርኛ መዝገበ ቃላት። (2001)። *የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል።* አዲስ አበባ ዩኒቨረሲቲ።

ሬሁን አስፋው። (2002)። *የስነጽሁፍ መሰረታውያን።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

______፤ (1985)፤ *"የበዓሉ ግርማ ሴቶች አምስት ሃይለኞች"፤* የአጭር ልቦለድ ኪነጥበብ ጥቂት ገፅታዎች እና ሌሎች 11 ስነጽሁፋዊ መጣጥፎች፣ የኢትየጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አ.አ.ዩ፣ ተባዝቶ የተጠረዘ።

_______፤ (1985ዓ.ም)፤ *"የኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍ ሁኔታ(1950-1985) አጭር ቅኝት"፤* አዲስ አበባ፣ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅትና የብሪትሽ ካውንስል ባዘጋጁት ነፃ የመፃሕፍት ገበያ ኮንፈረንስ የቀረበ፣ ተባዝቶ የተጠረዘ።

______፤ (1988)፤ "መልክዓ ሴት በአማርኛ አጭር ልቦለድ በሶስት ደራሲያን ናሙናነት"፤ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለዘጠነኛ አመታዊ ጉባኤ የቀረበ፣ አ.አ.ዩ።

ዮናስ አድማሱ፤ (1992)፤ "አስረኛንከዋ?፤ ሀዲስ አለማየሁና የማህበራዊ ሂስ ስልታቸው፤" የኢትየጵያ ቋንቋዎችና የሥነ ፅሁፍ መጽሔት፤ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ቁጥር 10፤ ገጽ፣ 77-119።

ዮሐንስ አድማሱ፤ (1963)፤ "የኢትዮጵያ ደራሲያን የህብረተሰቡን ትክክለኛ፤ መሠረታዊ ፍላጎት የመግለፅ ግዴታ አለባቸው"፤ አዲስ አበባ፣ ተባዝቶ የተጠረዘ።

ጥላሁን ተሊላ፤ (1998)፤ "የኦሮምኛ ስነፅሁፍ ፈር"፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ትምህርት፣ ለኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።